## ኢትዮጵያ፡- የ2016 የሰብዓዊ መብት ሪፖርት
## አጭር ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ በፌዴራላዊ ሥርዓት የምትመራ አገር ነች፡፡ አራት ብሔርን መሰረት ያደረጉ ፓርቲዎች ጥምረት የሆነዉ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ)፤ መንግስታዊ ስልጣንን ተቆጣጥሯል፡፡ በግንቦት 2007 ምርጫ፤ ኢሕአዴግና አጋር ፓርቲዎች ያሉትን 547 የፓርላማ መቀመጫዎች ሙሉ በሙሉ በማሸነፍ በተከታታይ ለአምስተኛ ጊዜ የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን እንዲቆናጠጡ አስችሏቸዋል፡፡ በመስከረም 2008 ዓ.ም. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኃይለማርያም ደሳለኝን በጠቅላይ ሚኒስትርነት መረጣቸው፡፡ መንግሥት የጣለው ገደብ ገለልተኛ አካላት ምርጫውን እንዳይታዘቡ በእጅጉ ገድቧል፡፡ ምርጫውን እንዲታዘብ የተፈቀደለት ብቸኛው ዓለም አቀፍ ተቋም ወይም ድርጅት የአፍሪካ ሕብረት ሲሆን፤ እርሱም ምርጫው የተረጋጋ፣ ሰላማዊና ተአማኒ ነው በማለት ገልጾታል፡፡ አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምርጫው ከመካሄዱ በፊት ለነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ሁኔታዎች አልተመቻቹም ብለዋል፡፡ መንግሥት ኢ-ፍትሃዊ ስልቶችን በመጠቀም፤ የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎችንና ደጋፊዎቻቸውን በማስፈራራት፣ ከምርጫው በኋላም ሆነ በፊት የኃይል እርምጃዎችን ወስዶ የስድስት ሰዎችን ህይወት ለህልፈት መዳረጉን ሪፖርቶች ጠቁመዋል፡፡

ሲቪል ባለስልጣናት አንዳንድ ጊዜ የፀጥታ ሃይሎችን ለመቆጣጠር ባለመቻል፤ በገጠር አከባቢዎች የፖሊስ አካላትና የአከባቢ ሚሊሺያዎች በራሳቸው እርምጃ ሲወስዱ ተስተዉለዋል፡፡

የፀጥታ ሃይሎች ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ አመቱን ሙሉ ከመጠን ያለፈ ሃይል ሲጠቀሙ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩትን ገድለዋል፤ ሌሎች ብዙዎችን አቁስለዋል፡፡ ሰላማዊ ሰልፎቹ የተካሄዱት በብዛት በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ነበር፡፡ በአመቱ መጨረሻ ከ10,000 የሚበልጡ ሰዎች በቁጥጥር ስር እንደሚገኙ ታምኗል፡፡ ቁጥሩ መስከረም 28 መንግሥት ባወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታሰሩትን ይጨምራል፡፡ አብዛኞዎቹ ለፍርድ አልቀረቡም፤ የህግ የምክር አገልግሎት አላገኙም ወይም በወንጀል አልተከሰሱም፡፡

መንግስት ያቋቋመው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ)ሰኔ 3 ቀን ለፓርላማው ስላጠናቀረው ሪፖርት አጭር ማብራሪያ አቅርቧል፡፡ ኢሰመኮ በኦሮሚያ 28 የፀጥታ ሃይል አባላትንና የመንግስት ሃላፊዎችን ጨምሮ 173 ሰዎች መሞታቸውን ሲያረጋግጥ፤ የፀጥታ አካላት ተመጣጣኝ እርምጃ ወስደዋል ብሏል፡፡ በሌላ በኩል ኢሰመኮ የአማራ ክልል ልዩ የፀጥታ ሃይል በቅማንት ማህበረሰብ ላይ ከልክ ያለፈ የሃይል እርምጃ መውሰዱን አረጋግጧል፡፡ መንግስታዊ ያልሆነው Human Rights Watch (HRW) በነሐሴ 7 መግለጫው የፀጥታ ሃይሎች በግምት 500 የተቃውሞ ሰልፈኞችን መግደሉን አትቷል፡፡ በጥቅምት ወር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኦሮሚያ ክልል ብቻ የሟቾች ቁጥር “ከ500 ሊበልጥ ይችላል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡ የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ለኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ያቀረበው የይለፍ ፈቃድ በመንግስት ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ ብዙ ሰዎችን ለህልፈት በዳረገው የመስከረም 22ቱ የብሾፍቱ ሃይማኖታዊ ስነስርዓት በኋላ ቡድኖች የንብረት ውድመት አድርሰዋል፡፡ ጥቅምት 29 ባወጣው ርፖርት አለም አቀፉ መንግስታዊ ያለሆነው ድርጅት አምነስቲ ኢንተርናሽናል ከህዳር 2008 ጀምሮ ከ800 በላይ ሰዎች ለህልፈት እንደተዳረጉ ገልጿል፡፡

የፀጥታ ሃይሎች ከመጠን ያለፈ ሃይል መጠቀም እና  ሰላማዊ ሰልፈኞችን በዘፈቀደ ማሰር፤ ፖለቲካዊ ይዘት ያለቸው ክሶች እንዲሁም ቀጣይነት ያለዉ ክልከላ በሲቪል እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚደርሱ  ዋነኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ነበሩ፡፡

ሌሎች የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች የዘፈቀደ ግድያዎችን፤ ስወራን፤ ማሰቃየትንና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸዉ፤ ኢ-ሰብዓዊ ወይም ሰብዓዊ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት፤ እጅግ የከፋ አንዳንዴም ለሕይወት አስጊ የሆነ የማረሚያ ቤት ሁኔታ፤ በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል እና ማሰር፤ ያለ ክስ ማሰር እና ከፍርድ ሒደት በፊት ለተራዘመ ጊዜ አስሮ ማቆየት፤ ደካማ፣ የተጨናነቀ እና በፖለቲካ ተጽዕኖ ስር የወደቀ ፍርድ ቤት፣ ሕገ-ወጥ ፍተሻን ጨምሮ የዜጎችን ግላዊ መብቶች መጣስ፣ በሰፈራ መርሃግብር አፈጻጸም ወቅት የህዝብ ተሳትፎና ምክክር እንዲሁም የመረጃ አቅርቦት ያለመኖር፤ የንግግር ነጻነትን ጨምሮ የሲቪል ነፃነቶች ክልከላ፤ የኢንተርኔት ነጻነት፤ አካዳሚያዊና ባህላዊ ሁነቶች፤ የመሰባሰብ ነጻነት፤ የመደራጀት፤ እና ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ነጻነት እጦት፤ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጣልቃ የመግባት ሁኔታዎች፤ ዜጎች መንግስታቸውን መቀየር የሚችሉበትን አቅም መገደብ፤ በፖሊስ፣ በአስተዳደር ኃላፊዎች እና በፍርድ ቤቶች የሚፈጸም ሙስና፤ በሲቪል ማህበራት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተጣሉ እገዳዎች፤ አመጽ እና በሴቶች ላይ የሚደርስ ማህበራዊ መድልኦ፤ የሴት ልጅ ግርዛት፤ የሕጻናት መብት ጥሰት፤ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፤ በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርስ ማህበራዊ መገለል፤ ጾታንና ወሲባዊ ዝንባሌን መሰረት ያደረጉ እንዲሁም ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በደማቸው የሚገኝ ሰዎችን የማግለል፤ ጎሳን መሰረት ያደረገ አመጽን ጨምሮ ሕዝባዊ አመጽ፤ የንብረት ውድመት፤ የፀጥታ ሃይል አባላት ግድያ፤ የሠራተኛ መብቶችን መገደብ፤ የግዳጅ ሥራ፤ እንዲሁም ሕፃናትን በግዳጅ ማሠራትን ጨምሮ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ያካትታሉ፡፡

አጥፊዎችን ሕግ ፊት ያለማቅረብ ችግር ነበር፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ካልሆነ በስተቀር፣ መንግስት ከሙስና ውጪ ጥፋት የፈጸሙ ባለስልጣናት ላይ ክስ የመመስረትም ሆነ የመቅጣት እርምጃ አልወሰደም፡፡

## ክፍል አንድ - የሰው ልጅን ክብር መጠበቅ፣ ከሚከተሉት ነጻ የመሆን መብቶችን ጨምሮ፣

### ሀ. በዘፈቀደ ሕይወት ማጥፋት፤ ከሕግ ውጪ ወይም ፖለቲካን መሰረት ያደረገግድያ

መንግስትና ወኪሎቹ በዘፈቀደ እና ከሕግ ውጪ ግድያዎችን እንደፈፀሙ በርካታ ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡ የፀጥታ አካላት አመቱን ሙሉ በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ከመጠን ያለፈ ሃይል በመጠቀም በሙቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችንም ገድለዋል፡፡ ሰላማዊ ሰልፎቹ በአብዛኛው በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ነበሩ፡፡ በኦሮሚያ 33 ወረዳዎችን ከህዳር 2008 እስከ የካቲት 13፤ ቀን 2008 የገመገመው ገለልተኛው  የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ መጋቢት 5 የወጣዉ ዘገባ ከሙቶ በላይ ህገ ወጥ ግድያዎችን ይፋ አድርጓል፡፡ መንግስት ያቋቋመዉ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮምሽን ሰኔ 3 ቀን በኦሮሚያ ክልል የፀጥታ ሃይሎች ተመጣጣኝ የሆነ ሃይል ተጠቅመዋል በሚል ለፓርላማዉ ባቀረበው ሪፖርት እንዳረጋገጠው በክልሉ 28 የፀጥታ ሃይሎችን እና የመንግስት ሃላፊዎችን ጨምሮ በድምሩ 173 ሰዎች ሕይወት ጠፍቷል፡፡ በሌላ በኩል የአማራ ክልል ልዩ ሃይል በክልሉ ባሉ የቅማንት ማህበረሰብ አባላት ላይ ከመጠን ያለፈ ሃይል መጠቀሙን ሪፖርቱ አብራርቷል፡፡ ነገር ግን ኢሰመኮ ሪፖርቱን ለህዝብ ይፋ አላደረገም፡፡ HRW ነሐሴ 7 ባወጣው መግለጫው ከ500 በላይ ሰላማዊ ሰልፈኞች መገደላቸዉን አስታውቋል፡፡

ሐምሌ 30 እና ነሐሴ 1 በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ትላልቅ ከተሞች ሰላማዊ ሰልፎች የተካሄዱ ሲሆን በምላሹም የፀጥታ ሃይሎች  ሙቶ የሚሆኑ ሰልፈኞችን ገድለዋል፡፡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የመንግስት ሃይሎች በኦሮሚያ ክልልከ90 በላይ ሰላማዊ ሰልፈኞችን እንደገደሉ ገልፀዋል፡፡  የአማራ ክልል መንግስትም ሰባት ሰዎች መሞታቸውን ይፋ ቢያደርግም፤ ሌሎች ምንጮች ግን በክልሉ የሟቾች ቁጥር ከ50 በላይ እንደሚደርስ አስታውቀዋል፡፡

## ለ. የሰዎች መሰወር

ሰላማዊ ሰልፎችን ተከትሎ መንግስት በወሰደው እርምጃ ግለሰቦች በፀጥታ ሃይሎች ተይዘው ተሰውረዋል፡፡ HRW በሰኔ ወር ሪፖርቱ የኦሮሚያ ሰልፎችን ተከትሎ መንግስት በወሰደው እርምጃ፤ ህፃናትን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ጠፍተዋል ሲል ገልጿል፡፡ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የእስረኞች አያያዝ ደካማ በመሆኑ አንዳንድ የእስረኛ ቤተሰቦች የታሰሩ ቤተሰቦቻቸውን ማግኘት አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

## ሐ. ማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብአዊ፣ ወይም ሰብአዊ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት

ህገ-መንግሥቱ እና ህጉ እንዲህ ያሉ ተግባራትን (ማሰቃየትን እና ማንገላታትን) የሚከለክሉ ቢሆንም፤ የጸጥታ ኃይሎች በእስር ላይ ያሉ ሰዎችን እንዳሰቃዩ አልያም በደል እንዳደረሱባቸው ሪፖርቶች አመልክተዋል፡፡ HRW በሰኔ ወር ባወጣው ሪፖርት የፀጥታ ሃይሎች  ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ህጻናትን ጨምሮ እስረኞችን መደብደባቸውን ይፋ አድርጓል፡፡ የፀጥታ ሃይሉ አባላት ዱላ፤ የፕላስቲክ ቆመጥ እና አለንጋ በመጠቀም ነው ድብደባ የፈጸሙት፡፡ እንደ ሪፖርቱ ከሆነ፤ ብዙ ተማሪዎች እጃቸው ወደ ኋላ ታስሮ መሰቀላቸቀውን እና መገረፋቸውን፤ አራቱ ደግሞ በኤሌክትሪክ እግራቸውን በማንዘር እንዳሰቃዩዋቸው እንዲሁም ሌሎች ሁለት ደግሞ ብልታቸዉ ላይ ግኡዝ ነገር በማንጠልጠል እንዳሰቃዩዋቸው ተናግረዋል፡፡ ብዙ ሴት ታሳሪዎች ደግሞ በፀጥታ አካላት እንደተደፈሩ ገልፀዋል፡፡ ሪፖርቱ አክሎም “በ HRW ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የታሰሩ ብዙ ግለሰቦች የእስር ቆይታቸው ስቃይ የተሞላበት እንደሆነ አብራርተዋል” ሲል ገልጿል፡፡

በማዕከላዊ፤ በይፋ የሚታወቁና የማይታወቁ እስር ቤቶች፤ በፖሊስ ጣቢያዎች እና በቅሊንጦ ፌዴራል ማረሚያ ቤት ውስጥ ታሳሪዎች በግፍ እንደተያዙ ተዘግቧል፡፡ አዲስ አበባ የሚገኘው በብዛት ታዋቂ ፖለቲከኞች በሚታሰሩበት ማዕከላዊ  ወንጀል ምርምራ ዋና መሥሪያ ቤት፣ መርማሪ ፖሊሶች ታሳሪዎች የእምነት ቃል እንድሰጡ ለማድረግ አካላዊና ሥነልቦናዊ በደል እንደሚያሳድሩባቸው ዘገባዎች ያመለክታሉ፡፡ ከታሳሪዎች መረጃን ለማውጣጣትና ጥፋታቸዉን እንዲያምኑ ለማድረግ የፖሊስ መርማሪዎች ድብደባና በኤሌክትሪክ ንዝረት ስቃይ እንዳደረሱባቸዉ ተገልጿል፡፡ HRW በማዕከላዊ እስር ቤት ማሰቃየትን ጨምሮ የግፍ ጥቃቶች እንደነበሩም ዘግቧል፡፡ በ2005 ዘገባዉ፤ HRW በማእከላዊ ድብደባዎች፣ አስጨናቂ አያያዞች ማለትም የታሳሪዎችን እጅ ከኮርኒስ ጋር አስሮ ማንጠልጠል፣ ለረዥም ጊዜ በካቴና አስሮ ማቆየት፣ ታሳሪዎች ላይ ውሃ ማፍሰስ፣ የቃል ማስፈራሪያዎች እና ለብቻ ማሰር እንደሚፈጸሙ ገልጧል፡፡ አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጣም ውስን የሆነ ፈቃድ ቢሰጣቸውም፤ ባለሥልጣናት የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ቢሮን እንዳይጎበኙ እንደተከለከሉ ናቸው፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በዓመቱ (ከታህሳስ 10 ወዲህ) ባወጣዉ ዘገባው በኢትዮጵያውያን ሰላም አስከባሪዎች በአመቱ ውስጥ ፈጽመውታል የተባለ አንድ ጾታዊ ጥቃትን የሚመለከት እና የግፍ ይዞታ የክስ ጥቆማ እንደደረሰው አስታውቋል፡፡ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የደቡብ ሱዳን ተልዕኮ የተሰማሩ ወታደሮች ላይ ያነጣጠረው ክስ በኢትዮጵያ መንግስት ማጣራት የተደረገበት ሲሆን በተጨባጭ ማስረጃ ያልተደገፈ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

## የማረሚያ ቤቶች እና የማቆያ ማዕከላት ሁኔታ

ማረሚያ ቤቶች እና የቅድመ-ክስ ሒደት ማቆያ ማዕከላት ይዞታ በአስከፊ ደረጃ ላይ የሚገኝ እና በአንዳንድ ሁኔታዎችም ለሕይወት አስጊ እንደሆነ ነው፡፡ በማቆያ ማዕከላት፡ በወታደራዊ ካምፖችና በፖሊስ ጣቢያዎች ባለስልጣናት በእስረኞች ላይ ድብደባ እንደሚፈጽሙና ስቃይ እንደሚያደርሱ የሚገልጹ ሪፖርቶችም ቀርበዋል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ድብደባውን ተከትሎ እስረኞች በቂ የሕክምናና ክትትል አይደረግላቸውም፡፡ እስረኞች በእሳት ተቃጥለው ለሞት ተዳርገዋል፡፡

አገሪቱ ስድስት የፌደራል እና 120 የክልል ማረሚያ ቤቶች ነበሯት፡፡ መስከረም 28 በታወጀዉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፤ መንግስት የአዋሽ፤ ዝዋይ እና ዲላ ማቆያ ጣቢያዎችን ይፋ ሲያደርግ፤ ተጠርጣሪዎች በአዲስ አበባም በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች ሊቆዩ እንደሚችሉ አስታዉቋል፡፡ ዴዴሳ፣ ብር ሸለቆ፣ ጦላይ፣ ሆርማት፣ ብላቴ፣ ታጠቅ፣ ጂጂጋ፣ ሆለታ እና ሰንቀሌ የሚገኙትን ጨምሮ በመላ አገሪቱ በርካታ ይፋዊ ያልሆኑ የማቆያ ማዕከላት አሉ፡፡ መንግስት ለሰላማዊ ሰልፎች በሰጠው ምላሽ፤ ሰዎች በወታደራዊ ካምፖች፤ በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤቶች እና በመንግስት የተያዙ ጊዜያዊ ማቆያ ቦታዎች ላይ ታስረዋል፡፡

አንድ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሌሎች እስር ቤቶች በእጅጉ የሚሻሉ ሞዴል እስር ቤቶችን በአዳማ፣ በመቀሌ፣በደብረብርሃን፤ በደራሼ እና በአዋሳ ከተሞች እገዛ አድርጓል፡፡
ቅድመ ክስ ፖሊስ ጣቢያዎች ውሰጥ በሚገኙ ማቆያዎች የሚታሰሩ ሲሆን፤ በነዚህ ማቆያ ማዕከላት ያለው አያያዝም ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ በፖሊስ ጣቢያዎች የቅድመ ክስ እስር ሂደትን በተመለከተ በወጡ ሪፖርቶች መሰረት በማቆያ ቤቶቹ የንጽሕና መጓደል፣ እንዲሁም ፖሊስ በእስር ላይ ባሉ ሰዎች ላይ ድብደባ እንደሚፈጽም ያመለክታሉ፡፡

**<u>አካላዊ ይዞታ፡-</u>** ወጣት አጥፊዎች አልፎ አልፎ ከአዋቂዎች ጋር የሚታሰሩ ሲሆን፣ በአንዳንድ የማረሚያ ጣቢያዎች ሴቶችንና ወንዶችን ቀላቅሎ የማሰር ሁኔታ የተስተዋለ ቢሆንም በአጠቃላይ ወንድ እና ሴት ታራሚዎች የተለያየ ቦታ ይታሰራሉ፡፡

በማረሚያ ቤቶች በተለይ በመኝታ ቦታዎች አስከፊ የሆነ መጨናነቅ  የተለመደ ነው፡፡ የገንዘቡ መጠን ከቦታ ቦታ ልዩነት የነበረው ቢሆንም መንግሥት ለአንድ እሥረኛ ለምግብ፣ ለውሃ እና ለጤና እንክብካቤ በቀን ዘጠኝ ብር ገደማ መድቧል፡፡ ብዙ እስረኞች ይህን ከመንግሥት የተመደበላቸውን ገንዘብ የቤተሰብ አባላት በሚያቀብሏቸው የዕለት ምግብ ወይም በአካባቢው ካሉ ሻጮች በሚገዙት ምግብ ይደጉማሉ፡፡ በሌሎች ዘገባዎች ባለስልጣናት አንዳንድ ታሳሪዎች ከቤተሰቦቻቸው የሚመጣላቸውን ምግብ እንዳይቀበሉ እንዳስገድዋቸዉ ተመልክቷል፡፡በፌደራል ማረሚያ ቤቶች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት አስተማማኝ አይደለም፡፡ በክልል ማረሚያ ቤቶች የሕክምና አገልግሎት የለም በሚባል ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የዉሃ እጥረት የንጽህና ጉድትን ያስከተለ ሲሆን አብዛኛዎቹ ማረሚያ ቤቶችም የመፀዳጃ ቦታ ችግር አለባቸው፡፡ ብዙ እስረኞች  ከባድ የጤና ችግሮች ያጋጠማቸው ቢሆነም የሚያገኙት ህክምና በቂ አልነበረም፡፡ የማረሚያ ቤት ሃላፊዎች አንዳንድ ታራሚዎች  የህክምና ክብካቤ እንዳያገኙ ክልከላ እንዳደረጉባቸው ዘገባዎች ይጠቁማሉ፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በ2004 ዓ.ም. ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው በአገሪቱ በተለያዩ እስር ቤቶች ከሚገኙ እስረኞች 62 በመቶ የሚሆኑት የአእምሮ ጤና መታወክ የገጠማቸው ሲሆን፤ ለብቻ መታሰር፣ የእስር ቤቶች መጨናነቅ እና በቂ የጤና ክብካቤ አለማግኘት በምክንያትነት ተጠቅሰዋል፡፡

በሰኔ ወር የተለቀቀውና ለኦሮሞ ሰልፈኞች መንግስት የሰጠዉን ምላሽ የተመለከተዉ የHRW ዘገባ፤ ታሳሪዎች የእስር ቤቶች መጨናነቅን፤ የምግብ እና ውሃ አቅርቦት እጥረትን፤ በወታደራዊ ካምፖች ጭምር ለብቻ እስርን እንዳስተዋሉ ማስታወቃቸውን ይገልጻል፡፡ ዘገባው ባብዛኛው ሴቶችና ወንዶች በተመሳሳይ ክፍሎች እንደማይታሰሩና፤ ህጻናት ግን ከአዋቂዎች ጋር እንደሚታሰሩ ያትታል፡፡

በታህሳስ 2007 በጎንደር፤ በየካቲት ll በአምቦ፤ በነሐሴ 26 በደብረታቦር እንዲሁም በነሐሴ 28 በቅሊንጦ ማረሚያ ቤቶች ቃጠሎ የደረሰ ሲሆን በቅሊንጦ በተነሳው የእሳት ቃጠሎ የ23 ታራሚዎች ህይወት ጠፍቷል፡፡

የእስረኞች ጠያቂዎች እና ሌሎች ምንጮች እንደገለጹት የፖለቲካ እስረኞች ከሌሎች እስረኞች አንጻር እጅግ የከፋ የእስር አያያዝን ይጋፈጣሉ፡፡ ተገቢ የህክምና አገልግሎት እጦት፤ መጽሐፍትን ለማንበብ ወይም ቴሌቪዥን ለመከታተል አለመቻል እና የአካል እንቅስቃሴ ክልከላ የፖለቲካ ታሳሪዎችን በሚመለከት ከሚቀርቡ ቅሬታዎች ዉስጥ ይካተታሉ፡፡ እነኚህ ቅሬታዎች በፍርድ ቤት የተነሱበት አንድ አጋጣሚ ላይ፤ ዳኞች ቅሬታዎቹን ቀድሞውኑ አሻፈረኝ ብሎ ሳይቀበላቸው ለቀረው የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር እንዲታዩ መልሰዋቸዋል፡፡

**<u>አስተዳደር፡-</u>** እስርን በሚመለከት ግልጽ አሠራር ካለመኖሩ የተነሳ፤ መዝገብ በበቂ ሁኔታ መያዝና አለመያዙን ለማረጋገጥ ያስቸግራል፡፡ ታሳሪዎች በማረሚያ ቤት ጠባቂዎች በደል ሲደርስባቸው ለማረሚያ ቤቱ አስተዳደር አቤቱታ ማቅረብ እንደማይችሉ ሪፖርቶች አመልክተዋል፡፡ ማረሚያ ቤቶቹ ለሚነሱ ቅሬታዎች ምላሽ የሚሰጡ የዕንባ ጠባቂ ባለሙያዎች የሏቸውም በአንዳንድ እስር ቤቶች ለእስረኞች አገልግሎት የሚሰጡ የሕግ ድጋፍ ማዕከላት የነበሩ ሲሆን በተለይም በክልል የሚገኙ የህግ ድጋፍ ማዕከላት ከዳኞች፣ከማረሚያ ቤቶችና ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር መልካም ግንኙነት ነበራቸው፡፡ የማረሚያ ቤት ኃላፊዎች የታሳሪዎችን አቤቱታዎች ሳንሱር ሳያደርጉ ለፍርድ ቤቶች እንዲያቀርቡ ፈቅደዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች አንዳንዴ እንዲህ ዓይነት አቤቱታዎችን ሳይቀበሉ ቀርተዋል፡፡

የታሳሪዎች የመጎብኘት መብት በህግ የተደነገገ ነው፡፡ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ መሠረት አንድ ጠበቃ በቀን ማግኘት የሚችለው አንድ ደንበኛውን ብቻ ሲሆን፤ ይህም የሚፈቀደው ረቡዕና ዓርብ ብቻ ነው፡፡ በሽብር ድርጊት የተከሰሱ እስረኞች ቤተሰቦች ታሳሪዎችን እንዳያገኙ ባለሥልጣናት ከልክለዋል፡፡ ተከሳሾችም ከጠበቆቻቸው ወይም ከፓርቲዎቻቸው ተወካዮች ጋር እንዳይገናኙ መደረጋቸው ሪፖርት ተደርጓል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፖሊሶች በቅድመ ክስ እስር ላይ ያሉ ታሳሪዎች ቤተሰቦቻቸውን እና የህግ አማካሪዎቻቸውን ጭምር  እንዳይጎበኙ ያግዳሉ፡፡

በቅሊንጦ የፌደራል ማረሚያ ነሐሴ 28 የተነሳውን የእሳት ቃጠሎ ተከትሎ ከቅርብ ቤተሰቦች በስተቀር የእስረኞች ጥየቃ ታግዶ እንደነበር የእስረኞች ጠበቆች አመልክተዋል፡፡ የፍርድ ሂደቱን፤ ፖለቲካ ጉዳዮችን፤ የግፍ አያያዞችን የሚመለከቱ ውይይቶች በጉብኝት ወቅት ተከልክለው ነበር፡፡ ይህ ክልከላ በቅሊንጦ፤ ሸዋ ሮቢት እና ዝዋይ ማረሚያ ቤቶች ተስተውሏል፡፡ እነኚህ ክልከላዎች በፖለቲካ እስረኞች ላይም ተፈጻሚ ነበሩ፡፡

እስረኞች እምነታቸውን በነፃነት እንዲያራምዱ ቢፈቀድላቸውም፣ እንደ ማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ፈቃድ ሁኔታው ከማረሚያ ቤት ማረሚያ ቤት አንዳንዴም በአንድ ማረሚያ ቤት ውስጥ ባሉ ክፍሎች መካከል ይለያያል፡፡ እስረኞች በማረሚያ ቤት ውስጥ ተገቢ የፀሎት ስፍራ እንደተከለከሉ የተናገሩባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ እስረኞች ፣ ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ጊዜ፣ ስለ እስር ቤቱ ሁኔታ ወይም ስለ አያያዛቸው ክሱን ለሚሰማው ዳኛ አቤቱታ እንዲያቀርቡ ተፈቅዶላቸዋል፡፡

**የገለልተኛ አካል ክትትል፡-** በዓመቱ ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ እንደመደበኛ የስራው አካልበሀገሪቷ ውስጥ የሚገኙትን ማረሚያ ቤቶች ጎብኝቷል፡፡ መንግሥት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ማረሚያ ቤቶችን እንዳይጎበኙ ከልክሏል፡፡

የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ሶስተኛ ወገን በሌለበት እስረኞችን እንዲጎበኙ የክልል ባለስልጣናት ፈቅደው የነበረ ሲሆንበመስከረም ወር እነኚህ ፈቃዶች በእጅጉ እንዲቀንሱ ተደርገዋል፡፡ የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች እና የቤተሰብ አባላት ታራሚዎችን፤በተለይም ይፋ ባልሆኑ ሥፍራዎች የታሰሩትን እንዳያገኙ የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች መከልከላቸው ተነግሯል፡፡ በመንግሥት የተቋቋመው፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለትና ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ የሆነው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የፌዴራል እና የክልል ማረሚያ ቤቶችን በመጎብኘት፤ በስፋት ይፈጸማሉ ስለሚባሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎችንና እስረኞችን አነጋግሯል፡፡ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት በመላ ሃገሪቱ የተለያዩ ማረሚያ እና የማቆያ ማዕከላትን የመጎብኘት ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡

***መሻሻሎች፡-*** *መንግስት ሁለት አዳዲስ ማረሚያ ቤቶችን ገንብቷል፡፡*

***መ. በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል ወይም ማሠር***

ምንም እንኳ የአገሪቱ ህገ-መንግሥት እና ህጉ በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል እና ማሠርን ቢከለክሉም፤ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የተካተቱት መመሪያዎች ግን የህግ አስከባሪ አካላት ግለሰቦችን ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ስር ማዋልና ማሰር እንዲችሉ ፈቅዷል፡፡ ህዝባዊ ሰላማዊ ሰልፎችን ተከትሎ በመላ አገሪቱ ፖሊስና የጸጥታ ኃይሎች በሽዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር እንዳዋሉ እና እንዳሰሩ የሚጠቁሙ በርካታ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡ የፀጥታ ሃይሎች ሰልፈኞችን፤ ፕሮፌሰሮችን፤ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን፤ ሙዚቀኞችን፤ ነጋዴዎችን፤ የጤና ባለሙያዎችን፤ ጋዜጠኞችን፤ ህጻናትን እና ሌሎችን በዘፈቀደ አስረዋል፡፡ ሰላማዊ ሰልፎችን ተከትሎ የፀጥታ አካላት ቤት ለቤት እየተዘዋወሩ በቁጥጥር ስር የማዋልና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትንና ደጋፊዎቻቸውን አመፅ ቀስቅሳችኋል በሚል ሰበብ በዘፈቀደ አስረዋል፡፡

***የፖሊስ እና የፀጥታ መዋቅር ሚና***

የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲሆን፤ ፓርላማዉ በበላይነት ይቆጣጠራቸዋል፡፡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ተጠሪነቱ ለፓርላማው ነው፡፡ ይህ የተጠሪነት ተዋረድ የላላ ነው፡፡ የአገሪቱ ዘጠኝ ክልሎች እያንዳንዳቸው ለክልሉ ሲቪል ባለሥልጣናት (አስተዳደር) ተጠሪ የሆነ የክልል ወይም ልዩ የፖሊስ ኃይል አላቸው፡፡ በመላ አገሪቱ የሚገኙ የአካባቢ ሚሊሻዎች ከክልልና ከፌደራል ፖሊስ እንዲሁም ከአገሪቱ ሠራዊት ጋር ልል በሆነ ቅንጅት ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች እነኝህ ሚሊሻዎች የገዢው ፓርቲ ተቀጥላ ሆነው ይሠራሉ፡፡ ለህዝባዊ ተቃውሞዎቹ አጸፋ በመስጠት በኩል ሰራዊቱ ትልቅ ሚና ነበረው፡፡ ሰራዊቱ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የተሰጡ ግዳጀችን እንዲወጣ ህገመንግስቱ ይፈቅዳል፡፡

በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ሃይል የተጠቀሙትንና ግድያ የፈጸሙትን ጨምሮ በህግ ተጠያቂነት አለመኖር አሳሳቢ ችግር ነበር፡፡ በፌዴራል ፖሊስ የተፈፀሙ የህግ ጥሰቶችን ለማጣራት የሚደረጉ ውስጣዊ አሰራሮች አይታወቁም፡፡ በመንግስት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የፀጥታ ሃይሎች በኦሮሚያ ክልል ተመጣጣኝ የሆነ ሃይል ተጠቅመዋል በሚል የተቃዉሞ ሰልፎችን የተመለከተ ዘገባ ሰኔ 3 ቀን ለፓርላማው ባቀረበበት ወቅት፤ በክልሉ 28 የፀጥታ አካላትን እና ባለስልጣናትን ጨምሮ 173 ሰዎች እንደሞቱ አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል የአማራ ክልል ልዩ የፀጥታ አካላት በክልሉ ባሉ የቅማንት ማህበረሰብ አባላት ላይ ከመጠን ያለፈ ሃይል መጠቀሙን ሪፖርቱ አረጋግጧል፡፡ ኢሰመኮ ሪፖርቱን ለህዝብ ይፋ አላደረገም፡፡ መንግሥት በዘፈቀደ ማሰርን እና በሰላማዊ ሰዎች ላይ ድብደባ መፈፀምን

በመሳሰሉ በፀጥታ ኃይሎች የተፈፀሙ የሙብት ጥሰቶች ላይ ያካሄዳቸውን ምርመራዎች ውጤት በይፋ የሚገልጽበት ሁኔታ እጅግ ውሱን ነው፡፡

መንግሥት ለፖሊስ እና ለመከላከያ ሠራዊት አባላት በሰብአዊ መብት ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ለመስጠት የሚያደርገውን ድጋፍ ቀጥሏል፡፡ መንግሥት በሕገ-መንግሥቱ እንዲሁም በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎችና እና ስምምነቶች ዙሪያ ተጨማሪ ትምህርቶችን በማካተት በሰብአዊ መብት ላይ የሚሰጠውን ሥልጠና እና ሥርዓተ-ትምህርት ለማሻሻልና በበቂ ባለሙያዎች እንዲሰጥ ለሚያደርገው ጥረት ከአንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ ሙብት ኮሚሽን የሚደረጉ ድጋፎችን መቀበል ቀጥሏል፡፡

## በቁጥጥር ሥር የማዋል ስነስርዓት እና በእሥር ላይ ያሉ ሰዎች አያያዝ

ህገ-መንግሥቱ እና ያገሪቱ ህግ በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሰዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ አልያም እንደየአካባቢው ሁኔታና የመገናኛ አውታሮች እንደ ሚፈቅዱት ከተያዙ በኋላ ወዲያውኑ ፍርድ ቤት ሊቀርቡና ክስ ሊመሠረትባቸው እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ወደ ፍርድ ቤት በሚደረግ ጉዞ የሚፈጀው ጊዜ በ48 ሰዓት የማቆያ ጊዜ ዉስጥ አይካተትም፡፡ ከበድ ያለ ጥፋት በመፈፀም የተጠረጠሩ ሰዎች የፍርድ ቤት ይሁንታ ሲገኝ ክስ ሳይመሠረትባቸው ለ14 ቀናት፣ እንዲሁም የምርምራ ሂደቱ ካልተጠናቀቀ፣ ለተጨማሪ ሌላ 14 ቀናት በእሥር ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ የጸጥታ ሃላፊዎች በተጠርጣሪዎች ላይ ክስ ሳይመሰርቱ ከ14 ቀናት በላይ የምርመራ ጊዜ መጠየቅ እንዲችሉ ፍርድ ቤቶች ሲፈቅዱ ነበር፡፡ ፀረ-ሽብርተኝነትአዋጁ ፖሊስ የሽብር ድርጊት ፈጽመዋል ብሎ የጠረጠራቸውን ሰዎች ያለዋስትና አስሮ እንዲያቆይ እና ምርመራ እንዲያደርግ ይፈቅዳል፡፡

ሕጉ በይፋ ከሚታወቅ ማረሚያ ቤት ውጪ እስረኞች እንዳይታሰሩ ቢከለክልም፤ የአካባቢ ሚሊሻዎች እንዲሁም መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ሕግ አስከባሪ አካላት በይፋ የማይታወቁ በርካታ ቦታዎችን ለማሰሪያነት ተጠቅመዋል፡፡ ለተቀሰቀሱት ተቃውሞዎች ምላሽም መንግስት ሰወችን በወታደራዊ ተቋማት አስሯል፡፡

ህጉ የዋስ መብት ፈቅዷል፡፡ ነገር ግን በሽብርተኝነት፣በነፍስ ማጥፋት፣ በአገር ክህደት እና በሙስና ለተከሰሱ ሰዎች የዋስትና ሙብት አይፈቀድላቸውም፡፡ በአብዛኛው የመንግሥት አካላት ለዋስትና የሚጠይቁት የገንዘብ መጠን በ500 እና በ10,000 ብር መካከል ሲሆን፣ ይህም ከአብዛኃኞቹ ዜጎች የመክፈል አቅም በላይ ነው፡፡ የመክፈል አቅም ለሌላቸው ተከሳሾች መንግስት ተከላካይ ጠበቃ ያቆምላቸዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ጉዳዩ ወደፍርድ ቤት ሲሄድብቻ ነው፡፡ ባለስልጣናት አንዳንድ ተጠርጣሪዎችን በቅድመ ፍርድ ሂደት በእሥር ላይ ሳሉ፣ ከሕግ አማካሪ ጋርእንዲገናኙ እጅግ ውሱን በሆነ ደረጃ ፈቅደዋል ወይም ከነጭራሹ ከልክለዋል፡፡ ከዚህ ሌላ በተጠርጣሪዎች የጤንነት ሁኔታ ላይ ሙሉ መረጃ አልሰጡም፤ ቤተሰብም እንዲጠይቃቸው አልፈቀዱም፡፡ ባለስልጣናት አንዳንድ እስረኞችን ለሳምንታት ፈጽሞ ከሰው ጋር እንዳይገናኙ መደረጋቸውን የሚጠቁሙ ሪፖርቶች ነበሩ፡፡ ፤ ሲቪሎችም በውል ለማይታወቅ ጊዜ በቤት ውስጥ የቁም እስር እንዲቆዩ ተደርገዋል፡፡

ህገመንግስቱ፤ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ባለስልጣናት የታሳሪዎችን ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ እንዲያደርጉ ቢደነግግም፤ በተግባር ግን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የታሰሩ ሰዎች ስም የተገለጸው በጥቅሉ ነው፡፡ የታሳሪዎች ስም ባብዛኛዉ በ30 ቀናት ዉስጥ ያልተገለጸ ሲሆን፤ ግለሰቦችም የታሳሪዎችን ስም ዝርዝር የያዘዉን ማህደር ማግኘት አዳጋች ሆኖባቸዋል፡፡

**<u>በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል፡-</u>** ሰላማዊ ሰልፈኞችን፤ ጋዜጠኞችን፤ እና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ጨምሮ ባለሥልጣናት በተደጋጋሚ ያለ ፍርድ ቤት ማዘዣ ሰዎችን አስረዋል፡፡ ለሰላማዊ ሰልፎች በአጸፋዉ የፀጥታ ሃይሎች በሺዎች የሚቆጠሩ የዘፈቀደ እስር መፈጸማቸዉን ዘገባዎች አመልክተዋል፡፡ የ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ የመጋቢት 5 ዘገባ 84 ሰዎች በህገወጥ መንገድ እንደታሰሩና፤ ከነዚህም ውስጥ አራቱ ወዲያዉኑ እንደተፈቱ አትቷል፡፡

በየካቲት 29፣ ባለስልጣናት 20 የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን በማሰር፤ በሀሰት ወሬ ህዝቡን ለአመጽ ቀስቅሳችኋል፤ ህገወጥ ሰልፍ ወጥታችኋል፤ እና ህዝቡ ለፀረ-ሽብር ህጉ ተገዥ እንዳይሆን አነሳስታችኋል በሚል በወንጀል ከሷቸዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሐምሌ 25 ባስቻለዉ ችሎት፣ ዘጠኝ ተማሪዎችን በነፃ በመልቀቅ፣ ጉዳያቸዉ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ሲታይ ለነበሩት ቀሪዎቹ 11 ተማሪዎች ላይ የቀረቡ ክሶችን ቀንሶላቸዋል፡፡

መንግስት ጋዜጠኞችንና ሌሎች መንግስትን በመቃወም ሀሳባቸዉን የሚገልጹ ሰዎችን በዘፈቀደ ማሰሩን ቀጥሎበታል (ክፍል 2.ሀን ይመልከቱ) ፡፡ የካቲት 24 የፌደራል ፖሊስ አንድ የዉጭ ሀገር ዜና አቀባይ፤ አንድ የግል ጋዜጠኛ እና አንድ አስተርጓሚያቸውን አዋሽ አቅራቢያ ይዘዋቸዉ ለአጭር ጊዜ በእስር አቆይተዋቸዋል፡፡ ፖሊስ ተንቀሳቃሽ ስልኮቻቸዉንና መታወቂያቸዉን በመቀማት ወደ አዲስ አበባ መልሰዋቸዋል፡፡ ስለታሰሩበት ጉዳይ ምንም ማብራሪያ ሳይሰጣቸዉ የካቲት 25 ቀን ከእስር ተለቀዋል፡፡

በህዳር 2008 ዓ.ም. ፖሊስ የቀድሞ የሰማያዊ ፓርቲ ቃል አቀባይ የሆኑትን አቶ ዮናታን ተስፋዬን በቁጥጥር ስር አውሎ አስረዋቸዋል፡፡ በሚያዝያ 26 የፌደራል አቃቤ ህግ የፀረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 4 ጠቅሶ አቶ ዮናታንን ሀሰተኛ የፌስ ቡክ ተጠቃሚ ስም በመጠቀም ለሽብር አነሳስተሀል በሚል ከሷል፡፡ በፍርድ ሂደት ክሱ ተሻሽሎ አነስተኛ የእስር ጊዜ በሚጠይቀዉ በአንቀጽ 6 በተቀመጠዉ ሽብርተኝነትን በማበረታታት በሚል ተቀይሯል፡፡ የዮናታን የፍርድ ሂደት በዓመቱ መጨረሻም ቀጥሏል፡፡

በመጋቢት 2008 ከናይሮቢ ጉዞአቸዉ ወቅት በቦሌ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተይዘው ለእስር የተዳረጉ ሦስት ሰዎችን በሚመለከት ለዉጦች ታይተዋል፡፡ በህዳር አጋማሽ ላይ ፍርድ ቤት በአሞት አገዋ አክዎይ ላይ የቀረበዉን ክስ ወደ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ዝቅ ሲያደርግ፤ በአሼኔ አስቲን ትቶይክ እና ጀማል አማር ሆጄሌ ላይ የቀረበዉን ክስ በማንሳት ከእስር እንዲለቀቁ ተደርጓል፡፡

**<u>ቅድመ-ክስ እሥር፡-</u>** አንዳንድ እሥረኞች ክስ ሳይመሠረትባቸው እና ፍርድ ቤትም ሳይቀርቡ ለበርካታ ዓመታት መታሠራቸውን ተናግረዋል፡፡ በቅድመ ክስ እስር ላይ ያሉ ታሳሪዎች ብዛት ወይም በእስር የቆዩበት አማካይ የጊዜ ርዝመት ምን ያህል እንደሆነ የሚገልጽ መረጃ አልተገኘም፡፡ በአብዛኛው የፍርድ ሂደት መጓተት የሚከሰተው በተራዘሙ የህግ ሥነ-ሥርዓቶች፣ በታሳሪዎች ብዛት፣ በፍትህ ሥርዓቱ የቅልጥፍና ማነስ ችግር እና በሰው ኃይል እጥረት ሳቢያ ነው፡፡ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የተካተቱ ድንጋጌዎች የመንግስት ሃላፊዎች አንድን ሰዉ ያለፍርድ ቤት ማዘዣ አዋጁ እስኪነሳ ድረስ ማሰር እንዲችሉ ይፈቅዳል፡፡

**<u>የታሳሪዎች ስለእስሩ ህጋዊነት በፍርድ ቤት መሟገት መቻል፡-</u>** ህጉ ታሳሪዎች ስለታሰሩበት ጉዳይ እንድነገራቸው ይፈቅዳል፡፡ ህጉ በወንጀል የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች ይግባኝንም ይፈቅዳል፡፡ በዓመቱ ዉስጥ አንድም ሰው በህገወጥ መንገድ ታስሯል የሚል የፍርድ ቤት ዉሳኔ አልተዘገበም፡፡ በህገ ወጥ መንገድ የታሰሩ ሰዎች ካሳ እንዲሰጣቸዉ ህጉ አይደነግግም፡፡

**<u>ምህረት፡-</u>** ለረዥም ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ለእስረኞች ምህረት የማድረግ ልማድ መሠረት መንግሥት በመስከረም ወር እንደ አቡበከር አህመድ መሐመድ እና ሌሎች

የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን የመሳሰሉ በፀረ-ሽብር ህጉ መነሻነት ለታሰሩ ከ12,000 በላይ ታራሚዎች ምህረት አድርጓል፡፡ ከነዚህም መካከል 757ቱ ከፌደራል ማረሚያ ቤቶች በምህረት የተለቀቁ ሲሆን ከ11,000 በላይ የሚሆኑት በክልል ማረሚያ ቤቶች ምህረት ተደርጎላቸዋል፡፡

***ሠ. ፍትሃዊ የፍርድ ሂደት መነፈግ***

ህጉ ነፃ እና ገለልተኛ የዳኝነት ሥርዓትን ደንግጓል፡፡ ምንም እንኳ የፍትህ ብሔር ፍርድ ቤቶች በተሻለ ነፃነት ቢንቀሳቀሱም፣ የወንጀል ፍርድ ቤቶች ግን ደካማ፣ ከአቅማቸው በላይ የሥራ ጫና ያለባቸው እና በፖለቲካ ተጽዕኖ ስር ያሉ ናቸው፡፡ ህገመንግስቱ ለሃይማኖታዊ እና ለባህላዊ ወይም ልማዳዊ ፍርድ ቤቶች እውቅና ይሰጣል፡፡

**የፍርድ ሂደት**

በህጉ መሠረት፣ የተከሰሱ ሰዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ግልጽ እና ፍትሃዊ በሆነ ሂደት የመዳኘት እና ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍርድ የማግኘት፣ ጥፋተኝነታቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ ንፁህ ተደርጎ የመታሰብ፣ በመረጡት የሕግ አማካሪ (ጠበቃ) የመወከል፣ እንዲሁም ይግባኝ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ ሕጉ ለተከሳሾች በራስ ላይ ያለመመስከር መብት ከመስጠት በተጨማሪ የመከላከያ ምስክሮችን እና ማስረጃዎቻቸውን የማቅረብ፣ ለዐቃቤ ሕግ ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ፣ እንዲሁም በመንግሥት እጅ የሚገኙ ማስረጃዎችን የማግኘት መብት ይሰጣል፡፡ ነገር ግን በአብዛኛዉ ታሳሪዎች የእነዚህ ሁሉ መብቶች ተጠቃሚ ሲሆኑ በተግባር አይታይም፡፡ በዚህ ምክንያት የተከሳሽ ጠበቆች አንዳንድ ጊዜ በቂ መከላከያ ለማቅረብ ሳይዘጋጁ ይቀርባሉ፡፡ ተከሳሾች ሁልጊዜ ጥፋተኝነታቸዉ በፍርደ ቤት እስካልተረጋገጠ ድረስ ንፁህ እንደሆኑ የመታሰብ፤ ከጠበቃቸውየመገናኘት፤ ከክስ ጀምሮ እስከ ይግባኝ ወቅታዊና ነፃ የትርጉም አገልግሎት የማግኘት፤ እንዲሁም በመንግሥት እጅ የሚገኙ ማስረጃዎችን የማግኘት መብት በአብዛኛው አልነበራቸውም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ተከሳሾች ክስ የመስማት ሂደቱ እስኪጀመር ድረስ ስለቀረበባቸው ክስ ይዘት አያውቁም ነበር፡፡ ታሳሪዎች በእስር ቆይታቸዉ ወቅት ለማውጣጣት እና የእምነት ቃል እንዲሰጡ ለማድረግ ስቃይና ግፍ ይፈጸምባቸው እንደነበር ርፖርቶች ወጥተዋል፡፡

የፌዴራሉ ተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት ጠበቃ የማቆም አቅም ለሌላቸው ሰዎች በነፃ አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን በጠበቆች እጥረት ምክንያት የአገልግሎቱ አድማሱ እና ጥራቱ ውስን ከመሆኑ ሌላ በአንዳንድ አጋጣሚዎች አንድ ጠበቃ ከ100 የሚበልጡ ጉዳዮችን እና በአንድ ጊዜ ሌሎች የግል ደንበኞችን ያስተናግዳሉ፡፡ በዋነኝነትም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ በርካታ ነፃ የህግ ምክር አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት ለደንበኞች የህግ ምክር ሰጥተዋል፡፡ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች እንደ ህግ ተማሪዎች እና መምህራን ያሉ በጎ ፈቃደኞች በነጻ ባለጉዳዮችን ወክለው ፍርድ ቤት እንዲቆሙ በህግ ተፈቅዷል፡፡

በገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ብዙ ዜጎች በመደበኛ የዳኝነት ሥርዓት የመዳኘት ተደራሽነት ውስን በመሆኑ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአትን ይጠቀማሉ፡፡ በህጉ መሰረት ተሟጋቾች ጉዳያቸው በባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤት መታየት ከመጀመሩ በፊት ተከራካሪዎቹ እንዲህ ባለው ፍርድ ቤት ለመዳኘት የግድ መስማማት አለባቸው፤ ከተከራካሪ ወገኖች ማንኛቸውም በማንኛውም ጊዜ ለመደበኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ የሸሪዓ (እስላማዊ) ፍርድ ቤቶች ሙስሊሞችን የሚመለከቱ ሃይማኖታዊ እና ቤተሰባዊ ጉዳዮችን ሊዳኙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የፍርድ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ተከራካሪ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ለመዳኘት መስማማት አለባቸው፡፡ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከመንግስት የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን፤ በአብዛኛው ሙስሊሞች በሚኖሩባቸው በሶማሌ እና በአፋር ክልሎች ለሚነሱ በርካታ ጉዳዮች ዳኝነት ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም እንደ ሽምግልና ያሉ ሌሎች ባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች አገልግሎት መስጠታቸውን ቀጥለዋል፡፡ አንዳንድ ሴቶች በልማዱ መሠረት ሴቶች በሽምግልና ላይ

ስለማይሳተፉ እና በገጠር አካባቢም የከፋ የጾታ መድልዎ በመኖሩ በባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት ነፃ እና ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት ዕድላቸው አነስተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## የፖለቲካ እስረኞች እና በቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎች

በዓመቱ መጨረሻ የፖለቲካ እስረኞች እና በቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎች ቁጥር በውል አይታወቅም ነበር፡፡ መንግስት ጋዜጠኞችን እና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላትን በቁጥጥር ሥር አውሏል፡፡

ፖሊስ በህግ እውቅና ያለውን  የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) ምክትል ሊቀመንበር አቶ በቀለ ገርባን እና ሌሎች 21 ሰዎችን በህዳር እና ታህሳስ 2008 ዓ.ም. በቁጥጥር ስር አዉሏል፡፡ በሚያዝያ 14 አቃቤ ህግ በፀረ-ሽብር ህጉክስ መስርቶባቸዋል፡፡ የመንግስት ሃላፊዎች አቶ በቀለን እና ሌሎችን በቂ የህክምና ክብካቤ እንዳያገኙ፤ በጠያቂዎች እንዳይጎበኙና ከጠበቆቻቸው ጋር እንዳይገናኙ በመከልከልየግፍ አያያዝ ሰለባ እንዳደረጓቸው ተዘግቧል፡፡ የፍርድ ሂደቱ በዓመቱ መጨረሻም ቀጥሏል፡፡

በአመቱ ፖሊስ ህዳር 20 በቁጥጥር ስር የዋሉትን መረራ ጉዲናን ጨምሮ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችንና አባላትን በቁጥጥር ሥር አውሏል (ስለምርጫ እና ፖለቲካ ተሳትፎ፤ ስለፖለቲካ ፓርቲዎች እና ፖለቲካ ተሳትፎ፤ ክፍል 3 ይመልከቱ) ፡፡

ፖሊስ በ2006 በቁጥጥር ሥር ስላዋላቸዉ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና ሌሎች 10 ግለሰቦችን በተመለከተ ለዉጦች ተዘግበዋል፡፡ በግንቦት 2 የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዘላለም ወርቃገኘሁ ላይ የአምስት ዓመት ከአራት ወር የእስር ጊዜ ሲወስን፤ ተስፋዬ ተፈሪን በሦስት ዓመት ከ 11 ወር፤ ሰሎሞን ግርማን በሦስት ዓመት ከሰባት ወር እስራት ቀጥቷል፡፡ በተመሳሳይ መዝገብ የነበሩ ሌሎች ሁለት ተከሳሾች፤ ዮናታን ወልዴ እና ባህሩ ደጉ ነጻ ተብለው ሚያዝያ 7  ተለቀዋል፡፡  በሌላ በኩል፤ አቃቤ ህግ፤ በነሐሴ 2007 የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነጻ ባሰናበታቸዉ በእነ ሐብታሙ አያለዉ፤ የሽዋስ አሰፋ፤ ዳንኤል ሺበሺ፤ አብርሃ ደስታ እና አብረሐም ሰሎሞን ላይ ይግባኝ ጠይቋል፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ህዳር 22 ባስቻለዉ ችሎት በእነ ሐብታሙ አያለዉ፤ የሽዋስ አሰፋ እና አብረሃም ሰሎሞን ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፈዉን ዉሳኔ ያጸና ሲሆን፤ የዳኒኤል ሺበሺ እና አብረሃ ደስታን ጉዳይ ወደከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመልሶ እንዲታይ ወስኗል፡፡

የዞን 9 ጦማሪያን ቡድን አባላትን በሚመለከት ለውጦች ነበሩ፡፡ በጥቅምት 2007 የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ናትናኤል ፈለቀን፤ አጥናፍ ብርሃኔን፤ አቤል ዋቤላንና ሶሊያና ሽመልስ ገብረሚካኤልን (በሌሉበት) በነፃ ያሰናበታቸዉ ሲሆን፤ በፍቃዱ ሃይሉ ላይ የቀረቡ ክሶችን ቀንሷል፡፡ በነፃ ስንብቱ ዉሳኔ ላይ የአቃቤ ህግ ይግባኝ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀጠለ ሲሆን፤ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የበፍቃዱ ሃይሉን የፍርድ ሂደት መስማት እንደቀጠለ ነው፡፡ በመስከረም 23 ናትናኤል ፈለቀ በድጋሚ በቁጥጥር ስር  ከዋለ በኋላ  በዋስ ተለቆ፤ በሬስቶራንት ውስጥ በግል በተደረገ የንግግር ልውውጥ መንግስትን የተመለከተ ጠንካራ ትችቶችን ሰንዝረሃል በሚል መነሻነት "በሃሰተኛ ወሬ ህዝቡን አነሳስተሀል" የሚል ክስ ቀርቦበታል፡፡ ህዳር 1 የመንግስት ሃላፊዎች በፈቃዱ ሃይሉን በድጋሚ አስረውት የነበረ ሲሆን ታህሳስ 11 ክስ ሳይቀርብበት በነፃ ተለቋል፡፡

## የዳኝነት ሥነ ሥርዓት እና የመፍትሔ  እርምጃዎች

ሕጉ ዜጎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙባቸው ለፍርድ ቤቶች አቤቱታ እንዲያቀርቡ መብት ይሰጣል፤ ሆኖም በዓመቱ ውስጥ እንዲህ ያሉ ጉዳዮች አልቀረቡም፡፡

ረ. በግል ነጻነት፣ በቤተሰብ፣ በመኖሪያ ቤት ወይም በመልዕክት ልውውጥ ላይ የዘፈቀደ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ጣልቃ-ገብነት

ህጉ ባጠቃላይ የመንግሥት አካላት የግለሰብ ንብረትን ለመፈተሽ የፍርድ ቤት ማዘዣ ይዘው እንዲቀርቡ የሚያዝ ቢሆንም፤ ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በኋላ፤ የፍርድ ቤት ማዘዣው እንዲቀር ተደርጓል፡፡ በአዋጁ ላይ በተደረገ ማሻሻያ፤ የፀጥታ አካላት፤ ፍተሻ ከማካሄዳቸዉ በፊት የሚፈትሹበትን ምክንያት፤ ህጋዊ የመታወቂያ ካርድ እና ከአከባቢዉ ማህበረሰብ የተወከለ ታዛቢ ይዘዉ መቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁንና አንድ ተጠርጣሪ ወደ አንድ ቅጥር ግቢ ሲገባ አልያም ወንጀል የተፈፀመባቸውን መሣሪዎች በአንድ ግለሰብ ቅጥር ግቢ ውስጥ የጣለ እንደሆነና ፖሊስ በመከታተል ላይ ላለው ትኩስ ወንጀል የፍርድ ቤት ማዘዣ ሳያስፈልገው ፖሊስ ፍተሻውን ማከናወን ይችላል፡፡ በተለይም የተፈፀመው ወንጀል ከሦስት ዓመት በላይ በእስር የሚያስቀጣ ሲሆንና ፖሊስ የሚፈልገው መረጃ የፍርድ ቤት ማዘዣ እስኪገኝ የሚጠፋ ነው ብሎ ሲያምን፤ወይም በተባለው ቅጥር ግቢ ውስጥ መደበቁ ከተረጋገጠ ፖሊስ ፍተሻውን ያለፍርድ ቤት ማዘዣ ማካሄድ ይፈቀድለታል፡፡ ከዚህም ሌላ የፀረ-ሽብር ህጉ የፌዴራል ፖሊስ ዳይሬክተር ጄነራል ወይም ተወካያቸው ሲፈቅዱ፤አልያም አንድ የፖሊስ አባል የሽብር ጥቃት ስለመፈፀሙ በቂ ጥርጣሬ ካለውና ፍተሻው በፍጥነት መካሄድ እንደሚኖርበት ካመነበት ይኸው እንዲፈፀም ይፈቅዳል፡፡

የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች እና ጋዜጠኞች የስልክ ጠለፋ እና ሌሎች በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የታገዙ ስለላዎች እና ክትትል እንደሚካሄዱባቸው ጥርጣሬ እንዳላቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡ ከዚህ ሌላ የመንግሥት ወኪሎች እንደሆኑ የሚጠረጥሯቸው ሰዎች የአገሪቱ ፓርላማ በሽብርተኝነት የፈረጃቸው ድርጅቶች ተወካዮች እንደሆኑ አስመስለው ለተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎች ስልክ በመደወል እና የገንዘብ ዕርዳታ ለማድረግ እንደሚፈልጉ በመግለጽ በሕገ ወጥ ድርጊቶች እንዲሳተፉ እንደገፋፏቸው ገልጸዋል፡፡

መንግሥት ያነጣጠራቸው ግለሰቦችን እንቅስቃሴ ተከታትለው ሪፖርት እንዲያደርጉ ገንዘብ የሚከፈላቸው መረጃ አቀባዮችን የማሰማራት ስልትን በሰፋት ተጠቅሟል የሚሉ ሪፖርቶች አሉ፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፤ ጋዜጠኞች፤ እና አትሌቶች የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች እና የሚሊሽያ አባላት፣ ሳይፈቀድላቸው መኖሪያ ቤታቸውና ቢሮዋቸዉ ድረስ ዘልቀው መግባታቸውንና የቤተሰቦቻቸዉን አባላት ማስፈራራታቸውን ሪፖርት አድርገዋል፡፡ ይህም ያለማዘዣ መግባትንና ፍተሻ ማድረግን ያካትታል፡፡

የመንግስት ሀላፊዎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ከሥራ እንዳባረሯቸውና፤ አንዳንዴ የኢህአዴግ አባል ያልሆኑት ደግሞ ከቀበሌያቸው "የድጋፍ ደብዳቤ" የሚያገኙበት መንገድ አዳጋች እንደነበር ተዘግቧል፡፡ (ክፍል 3 የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የፖለቲካ ተሳትፎን ይመልከቱ)

የፀጥታ ኃይሎች በመንግሥት የሚፈለጉ ሰዎችን ቤተሰቦች በቁጥጥር ሥር ማዋል እንደቀጠሉ ነው፡፡

የፌደራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት በአፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፣ ጋምቤላ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ እና ሶማሌ ክልሎች የተፋጠነ ልማት በተለምዶ አጠራር «የሰፈራ» ዕቅዶችን፤ መተግበር ቀጥለዋል፡፡ ዕቅዶቹ በተበታተነ አኳኋን የሚኖሩ የገጠር ሕዝቦችን ለተደጋጋሚ ድርቅ ከተጋለጡ ደረቅ አልያም ከፊል-ደረቅ አካባቢዎች አንስቶ በክልል መንግሥታት ወደተዘጋጁና ለውሃ፤ አገልግሎቶች እና ለመሠረተ ልማት ቅርብ ወደሆነ አንድ አካባቢ ማስፈርን ያካትታሉ፡፡ የፈጣን ልማት መርሀግብር ዓላማዎችም የጤና አገልግሎት፣ የትምህርት እና የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን የመሳሰሉ የመንግሥት አገልግሎቶችን አቅርቦት ማሻሻል፣ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከተፈጥሯዊ አደጋዎች እና ጥቃቶች መከላከል፣ እንዲሁም አካባቢን ክፉኛ የሚጎዱ አሉታዊ የዘልማድ አስተራረስን መለወጥ ናቸው ተብለው ተገልፀዋል፡፡ አንዳንድ ታዛቢዎች ግን፣ መርሀ ግብሩ ለንግድ የሚውል ሰፊ የእርሻ መሬት በሊዝ ለማከራየት የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የታለመ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ መንግሥት መርሀ ግብሩ በሙሉ በፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ

እንደሚፈፀም ገልጿል፡፡ መርሀ ግብሩን መንግሥት በ2007/2008 በጀት አመት የማቆም ዕቅድ ቢይዝም፤ቀጣይነት እንዲኖረው ሌላ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

ዓለም አቀፍ ለጋሾች ከ2003 ዓ.ም. ጀምሮ በሰፈራ መንደሮች ካደረጓቸው ከ18 ጊዜ በላይ ጉብኝቶች በመነሳት፤ በዚህ መርሀ ግብር የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዳላገኙ ሪፖርት አድርገዋል፡፡ ነገር ግን በቂ መሠረተ ልማቶች አለመሟላት ና በቂ ያልሆነ ካሳ የመሳሰሉ ችግሮች መኖራቸውን ተመልክተዋል፡፡ ማህበረሰቦች እና ቤተሰቦች የምግብ እርዳታ፣ የምግብ፤ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶች እንዲሁም መሬት እንደሚያገኙ ባለሥልጣናት በሰጧቸው ማረጋገጫ ላይ ተመሥርተው ለመሥፈር ቢስማሙም፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች በአዲሱ የሰፈራ ጣቢያ በቂ መሰረታዊ አገልግሎቶች እና መጠለያ ሳይዘጋጅላቸው ከመኖሪያ ቀያቸው የተንቀሳቀሱ ማህበረሰቦች ነበሩ፡፡ ከተከታታይ ጉብኝቶች ለመገንዘብ እንደተቻለዉም፤ መንግስት ከተጎጂ ማህበረሰብ አባላት ጋር ለመምከር ያደረገዉ ጥረት እጅግ አናሳ ከመሆኑም በላይ፤ ተነሺ የማህበረሰብ አባላት ያለበቂ መረጃ ከመሬት ይዞታቸዉ እንደሚነሱ ተመልክቷል፡፡

## ክፍል 2፡ የሲቪል መብቶች ከበሬታ፤

### *ሀ. የመናገር እና የፕሬስ ነፃነት*

የመናገር እና የፕሬስ ነጻነት በህገ-መንግሥቱ እና በህግ የተደነገጉ ቢሆንም፤ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌዎች በእነኚህ መብቶች ላይ ገደብ አስቀምጠዋል፡፡ ባለስልጣናት ጋዜጠኞችን እና መንግሥትን ይተቻሉ ብለው ያሰቧቸውን ሰዎች በማዋከብ፤ በቁጥጥር ሥር በማዋል፣በማሰር ብሎም በመወንጀል፤ በስራዎቻቸው ላይ የራስ-በራስ ሳንሱር እንዲሰፋፉ አድርገዋል፡፡

<u>የመናገርና ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት፡</u> የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ፤ የንግግር እና ሀሳብን የመግለጽ ነጻነትን ጨምሮ ገለልተኛ ድምጾችን ለእስርና ለስወራ የዳረጉ ሌሎች ብዙ ክልከላዎችን አካቷል፤ የትኛውንም በድብቅም ይሁን በይፋ የሚደረግ አመጽንና ብጥብጥን የሚጋብዝ (የአዋጁ ትርጉም በኦሮሞ አመጽ ምልክትነት የሚታወቀዉን ሁለት እጆችን ከራስ በላይ ከፍ አድርጎ መጠላለፍን ያካትታል) ቅስቀሳ፤ በሽብርተኝነት ከተፈረጁ ማንኛዉም የሽብር ቡድኖች ወይም ጸረ-ሰላም ሃይሎች ጋር የሚደረግን ማንኛዉንም ዓይነት ግንኙነት፤ ጽሑፎችን መያዝና ማሰራጨት፤ የሽብር ቡድኖችን ዓርማ መያዝ እና ማስተዋወቅ፤ በሃይማኖት ተቋማት ፍርሃትን ወይም ግጭትን የሚያጭሩ መልዕክቶችን ማስተላለፍ፤ በማንነት ወይም ብሔር ላይ ያነጣጠረ ግጭት ቀስቃሽ ንግግር እና ከዉጭ ሀገር መንግስት ጋር የሀገርን ሉዓላዊነት እና ፀጥታ የሚጎዳ መረጃን መለዋወጥ ይከለክላል፡፡ ማንኛዉም የፖለቲካ ፓርቲ ኢ-ህገመንግስታዊ የሆነና ሉዓላዊነትን እና ፀጥታን የሚጎዳ ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳይሰጥ ያግዳል፡፡ እነዚህ ክልከላዎች የተነሳ ግለሰቦች ራሳቸዉን ሳንሱር እንዲያደርጉ ሆነዋል፡፡

ባለሥልጣናት መንግሥትን የሚተቹ ሰዎችን በቁጥጥር ሥር አውለዋል፤ አስረዋል ብሎም አስፈራርተዋል፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መንግሥት ተቺ ግለሰቦችን እንደሚያሰቃያቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡መንግሥት በማስፈራራት፤ ጋዜጠኞችን፤ በድረገጽ አማካይነት መንግስትን የሚተቹትን እና የሚቃወሙትን በእስር በማቆየት፤ የተቃዋሚ ፖለቲካ ቡድኖችን እንቅስቃሴ በመከታተልና ጣልቃ በመግባት የሚሰነዘርበትን ትችት ለማፈን ሙከራ አድርጓል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በጸጥታ ኃይሎች የተፈጸመባቸውን የመብት ጥሰት ከተናገሩ ባለስልጣናት የቂም በቀል እርምጃ ይወስዱብናል ብለው ይፈራሉ፡፡ በአደባባይ ወይም በግል መንግስትን የሚተቹ ሰዎችን ሐሰተኛ ወሬ በማሰራጨት ህዝብን ለአመጽ ስለማነሳሳት የሚደነግገዉን ህግ ጥሰዋል በማለት ሃላፊዎች በቁጥጥር ስር አውለው አስረዋቸዋል፡፡

**የፕሬስ እና ሚዲያ ነፃነት፡-** የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ፣ የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን (ኢሳት) እና ኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ (ኦኤምኤን) እንዳይደመጥ፣ እንዳይታይ ወይም ከተጠቀሱ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች እንዳይዘገቡ እገዳ ጥሏል፡፡

የግሉ ሚዲያ ጋዜጠኞች የመንግሥትን ማተሚያ ድርጅት መጠቀም አስቸጋሪ መሆኑን ሪፖርት አድርገዋል፡፡ የግል ማተሚያ ቤቶች ተደራሽነት የለም በሚባል ደረጃ በጣም ውሱን ነበር፡፡

በአዲስ አበባ በድምሩ 70,711 ሳምንታዊ ስርጭት የነበራቸዉ 9 የግል ጋዜጦች እና መጽሄቶች ይገኛሉ፡፡ በድምሩ 21,500 ቅጅዎችን በየወሩ እና በሳምንት ሁለቴ በአማርኛ እና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚሰራጩ አራት የግል መጽሔቶች  አሉ፡፡ የመንግሥት ጋዜጦች በሳምንት 85,500 ቅጂዎች ያሰራጫሉ፡፡ መንግሥት ከሚያሳትማቸው ዕለታዊ የአማርኛ እና የእንግሊዝኛ ጋዜጦች፣እንዲሁም በየዕለቱ ከሚታተመው የግል የእንግሊዝኛ ጋዜጣ *ዴይሊ ሞኒተር* በስተቀር፣ አብዛኞቹ ጋዜጦች በየሳምንቱ ወይም በሳምንት ሁለት ጊዜ የሚታተሙ ናቸው፡፡ *አዲስ ስታንዳርድ* መጽሔት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በታወጀ ጥቂት ጊዜ ውስጥ ህትመቱን በጊዜያዊነት እንዲቋረጥ አድርጓል፡፡

መንግሥት የሚቆጣጠራቸው መገናኛ ብዙሃን የመንግሥትንና የገዢውን ፓርቲ ኢሕአዴግን አቋም ያንጸባርቃሉ፡፡ ሬዲዮን ጨምሮ ለአብዛኛው ሕዝብ ዋነኛ የዜና ምንጭ የሆነውና አገር አቀፍ ሥርጭት ያለው ብቸኛ የቴሌቪዥን ጣቢያ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ነው፡፡ በዋና ከተማይቱ  ስድስት የግል የኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች የሚገኙ ሲሆን፣ በትግራይ ክልል አንድ የግል ሬዲዮ ጣቢያ እንዲሁም በክልሎች ቢያንስ 19 የማኅበረሰብ ራዲዮ ጣቢያዎች ፕሮግራሞቻቸውን ያሰራጫሉ፡፡ በመንግሥት ይዞታ ሥር ያለው የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን፣ በአገሪቱ ሰፊ የስርጭት ሽፋን ያለው ሲሆን፣ ከገዢው ፓርቲ ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚነገርለት ሬዲዮ ፋና ተከታዩን ቦታ ይይዛል፡፡

መንግሥት በየጊዜው ከውጭ አገራት የሚተላለፉ ስርጭቶችን አፍኗል፡፡ ህጉ የፖለቲካ እና የሃይማኖት ድርጅቶች እንዲሁም የውጭ አገር ዜጎች የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን ባለቤትነትን ይከለክላል፡፡

**ሁከት እና ወከባ፡-** መንግሥት ጋዜጠኞችን ማሠር፣ ማዋከብ እና ክስ በበስረቱን ቀጥሏል፡፡ ከታህሳስ አጋማሽ ወዲህ ቢያንስ 12 ጋዘጤኞች በእስር ይገኛሉ፡፡

በታህሳስ 2007 ፖሊስ በኦሮሚያ ቴለቪዥን በዜና አቅራቢነት እና ከፍተኛ ሪፖርተርነት ሲያገለግል የነበረዉን ፍቃዱ ሚርካናን አስሮ የነበረ ሲሆን፣ ሚያዝያ ላይ ከእስር ተፈቷል፡፡

በታህሳስ 2007፣ የመንግሥት ሃላፊዎች የተቃዋሚ ልሳን የሆነዉን የድረገጽ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ጌታቸዉ ሺፈራዉን አስረዋል፡፡ ግንቦት 11 የሽብር ክስ የቀረበበት ጋዜጠኛዉ፣ የፍርድ ሂደቱ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ቀጥሏል፡፡

የካቲት 2007 ዓ.ም. በቁጥጥር ስር ዉለዉ በሽብርተኝነት ወንጀል ክስ የቀረበባቸዉ ሁለት የቢላል ራዲዮ ጋዜጠኞች የክስ ሂደት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀጥሏል፡፡

**ቅድመ-ህትመት ምርመራ (ሳንሱር) ወይም በይዘት ላይ የተጣሉ ገደቦች፡-** መንግሥት በሚያደርሰው ወከባ የተነሳ ጋዜጠኞች ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች ላይ ከመዘገብ ተቆጥበዋል፡፡ በርካታ የግል ጋዜጦች በመንግሥት መደበኛ ያልሆነ የኤዲቶሪያል ቁጥጥር ይደረግባቸው እንደነበር አመልክተዋል፣ ለዚህም ከመንግሥት ባለሥልጣናት የተዘጋጁ ጽሑፎችን አትመው እንዲያወጡ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ እና ታትመው የወጡ መንግሥትን የሚተቹ ጽሑፎችን አስመልክቶ ከመንግሥት ባለሥልጣናት የሚደርሷቸውን የስልክ ጥሪዎች

ጠቅሰዋል፡፡ የግሉ ዘርፍ እና የመንግሥት ጋዜጠኞች በዕለት ተዕለት ሥራቸው ራሳቸውን ሳንሱር ያደርጋሉ፡፡ ብዙ የሀገር ዉስጥም ሆነ የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በተለይ መስከረም 28 የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተከትሎ የራስ በራስ ሳንሱር መጨመሩን ገልጸዋል፡፡ ማስታወቂያ የሚያሠሩ ድርጅቶች መንግሥትን የሚተቹ ኅትመቶች ላይ ማስታወቂያዎቻቸውን እንዳያወጡ ጫና እንደደረሰባቸው የሚያመለከቱ ጥቆማዎች ነበሩ፡፡

__ብሔራዊ ደኅንነት፡__-መንግሥት የሚቀርቡበትን ትችቶች ለማፈን የፀረ-ሽብር አዋጁን ተጠቅሟል፡፡ ፓርላማው በ2003 ዓ.ም. ሽብርተኛ ድርጅቶች ብሎ በፈረጃቸው አምስት ቡድኖች (ግንቦት 7፣ ኦብነግ፣ ኦነግ፣ አል-ቃዒዳ እና አል-ሸባብ) ዙሪያ መዘገብ ይፈራሉ፤ ለዚህም የተጠቀሰው ምክንያት በእነዚህ ቡድኖች ዙሪያ ዘገባዎችን ማቅረብ በህግ የሚያስቀጣ ይሁን አይሁን ግልጽ አለመሆኑ ነው፡፡

## የኢንተርኔት ነፃነት

መንግሥት የኢንተርኔት አገልግሎትን ገድቧል፤አገልግሎቱ እንዲቆራረጥም አድርጓል፡፡ በተለይ የተቃውሞ ሰልፎችን ተከትሎ በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች በየጊዜው የማህበራዊ ሚዲያዎችን ዘግቷል፤ የኢንተርኔት አገልግሎትን አቋርጧል፡፡ መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት የኢንተርኔት አገልግሎት በመላ አገሪቱ እንዲቋረጥ አድርጓል፡፡ መንግሥት ህጋዊ ስልጣን ሳይኖረው ግላዊ የደህረ-ገጽ ልውውጦችን በድብቅ እንደሚከታተል ተጨባጭ ዘገባዎች አሉ፡፡ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው ኢትዮ ቴሌኮም በሀገሪቱ ብቸኛው የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ነው፡፡

ፓርላማዉ ግንቦት 30 የኮምፒውተር ወንጀል አዋጅን አጽድቋል፡፡ አዋጁ እጅግ አሻሚ እና የንግግር እና ሀሳብ የመግለጽ ነፃነትን የሚገድቡ አንቀጾች መካተታቸዉ አሳሳቢ ነበር፡፡ በአዋጁ ከተካተቱት ውስጥበማንኛዉም የኮምፒውተር ዘዴ ጽሑፍን፤ ቪዲዮን፤ ድምጽን ወይም ሌላ ማንኛውንም በሰዎች መካከል አመጽ፤ ብጥብጥ፤ ወይም ግጭት የሚቀሰቅስ ምስል ማሰራጨትን እና በማስፈራራት የተጠረጠሩት ላይ የእስር ጊዜን የሚጥልም አንቀጽ ይገኝበታል፡፡

ሐምሌ ላይ ብሔራዊ ፈተናዎች እስኪጠናቀቁ ድረስባለሥልጣናት በመላው ሀገሪቱ ለቀናት የማህበራዊ ሚዲያ ድረገፆችን አግደዋል፡፡ መንግሥት የማህበራዊ ሚዲያ እገዳው “ሥርዓቱን የጠበቀ የፈተና ሂደት” ለማስፈን አስፈላጊ ነበር ሲል ገልጿል፡፡ ግንቦት ላይ ብሔራዊ ፈተናዎች ማህበራዊ ሚድያ ሾልከዉ መዉጣታቸውን ተከትሎ መንግሥት ፈተናዎችን አራዝሞ ነበር፡፡

ሐምሌ 30 እና ነሐሴ 1፤ መንግሥት በመላው ሃገሪቱ የኢንተርኔት አገልግሎትን አግዷል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ህጎች፤ ፤ አመጽ እና ብጥብጥን በኢንተርኔት፤ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት እና በማኅበራዊ ሚዲያ በመለዋወጥ ቅስቀሳን ጭምር የሚከለክሉ አንቀጾችን አካቷል፡፡

ከጥቅምት መግቢያ ጀምሮ፤ መንግሥት በአዲስ አበባ፤ በአብዛኛው ኦሮሚያ እና ሌሎች አካባቢዎች በሞባይል የኢንተርኔት አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ አቋርጧል፡፡ ብዙ የማህበራዊ ትስስር ድረገፆች እና መገናኛ ዘዴዎች በመደበኛው የኢንተርኔት አገልግሎት ጭምር እንዳይጎበኙ ክልከላ ተደርጎባቸዋል፡፡ በክልከላዉ ፌስቡክ፤ ትዊተር፤ ኢንስታግራም፤ ዩቲዩብ፤ ስካይፐ፤ ዋትስአፐ እና ቫይበርን የመሳሰሉ የማህበራዊ ትስስር ድረገፆች ተካተዋል፡፡ ዋሽንግተን ፖስት እና ኒዉዮርክ ታይምስን የመሳሰሉ የዜና አውታሮቸህን ጨምሮ ሌሎች የውጭ ሀገር ዩኒቨርስቲዎችና አማዞንን የመሳሰሉ የኢንተርኔት ላይ ግብይት ድረገፆችንይጨምራል፡፡

መንግሥት ከጊዜ ወደ ጊዜ በተጠናከረ ሁኔታ በኢንተርኔት ላይ በርካታ ይዘቶች እንዳይታዩ ገደብ የጣለ ሲሆን፤ ብሎጎችን፤ የተቃዋሚ የግንቦት 7፤ ኦነግ፤ ኦብነግ ድረገፆችን እንዲሁም የአልጀዚራ፤ የቢቢሲ እና "RealClearPolitics" የኢንተርኔት ዜና ገፆችን ጨምሮ በርካታ ድረገፆችን አግዷል፡፡ መንግሥትን በሚቃወሙ ዳያስፖራ ቡድኖች የሚተዳደሩ በርካታ የዜና ብሎጎች እና ድረገፆች ተደራሽ አልነበሩም፡፡ ከነዚህም መካከል ኢትዮጵያን ሪቪዉ፤ ናዝሬት፤ ሳይበርኢትዮጵያ፤ ቋጠሮ የአማሪኛ መጽሔት እና የኢትዮጵያ ሚዲያ ፎረም ይገኙበታል፡፡

ባለስልጣናት በዜጎች የስልክ ጥሪዎች፤ አጭር የጽሑፍ መልዕክቶች እና ኢ-ሜይሎችላይ ክትትል ያደርጋሉ፡፡ የኢንተርኔት እና ኢሜይል ተጠቃሚዎች ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ ሆነው አገልግሎቱን እንዲያገኙ የሚያስችለውን "የቨርቹዋል ፕራይቬት ኔትዎርክ" (Virtual Private Network) አቅራቢዎችን የሚያግድ እርምጃም ወስደዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች ለእስር መዳረጋቸውን ሪፖርቶች አመልክተዋል፡፡ በዓለም አቀፉ የቴሌኮሙኒኬሽን ሕብረት መረጃ መሠረት በ2007/08 ዓ.ም. ከአጠቃላዩ የሀገሪቱ ሕዝብ 11.6 በመቶው ኢንተርኔት ተጠቃሚ ነበር፡፡

በመጋቢት 2007 ዓ.ም. "ሲቲዝን ላብ" (Citizen Lab) የተባለ ካናዳ ውስጥ በቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ የሚገኝ የምርምር ማዕከል፤ በ2006 ዓ.ም. መሠረቱን አሜሪካ ያደረገዉን የኢሳት ሠራተኞችን ኮምፒውተሮች በ "Spyware" ስፓይዌር ለመበከል ሙከራ ማድረጉን ዘግቧል፡፡ ኢሳት መሰረቱን በዳያስፖራ ያደረገ የቴለቪዥን እና ሬድዮ ጣቢያ ነው፡፡ "ሲቲዝን ላብ" በጥቃቱ የመንግስት እጅ እንዳለበትና  የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ሰንዝሮት ሊሆን እንደሚችል ገልጿል፡፡

**አካዳሚያዊ  ነፃነትና ባህላዊ ሁነቶች**

መንግሥት የአካዳሚ ነጻነትን ገድቧል፡፡ ይህም በተማሪዎች ቅበላ፣ በመምህራን ምደባዎች እና በሥርዓተ ትምህርት ላይ መወሰንን ይጨምራል፡፡ ባለስልጣናት በዩኒቨርሲቲ እና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመናገር፣ ሐሳብን የመግለጽ እና የመሰብሰብ ነፃነቶችን በተደጋጋሚ ገድበው ነበር፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መመሪያዎች በትምህርት ቤቶች የሚደረጉ ዓድማዎችን፤ የትምህርት ተቋማትን መዝጋትን ወይም በንብረት ላይ አደጋ ማድረስን ይከለክላል፡፡ አዋጁ የትምህርት ተቋማት በአዋጁ የተደነገጉ ክልከላዎችን የሚቃወሙ ማናቸዉም ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ እርምጃ እንዲወስዱ ባለስልጣናት ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉ ስልጣን ይሰጣል፤ ህግ አስከባሪዎች ወደ ትምህርት ተቋማት ቅጽር ግቢ በመግባት ዓድማዎችን ወይም ተቃውሞዎችን የቁጣጠር እርምጃዎችን እንዲወስዱ ስልጣን ይሰጣል፡፡

ገዢው ፓርቲ በትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ምደባ ወቅት ለፓርቲው ታማኝ ለሆኑ ተማሪዎች ቅድሚያ መስጠቱን ቀጥሏል፡፡ በየትኛውም የትምህርት ዘርፍ ከተመረቁ በኋላ ሥራ ለመቀጠር የፓርቲው አባል ለሆኑ ተማሪዎች ቅድሚያ እንደሚሰጥ አንዳንድ የዩኒቨርስቲ መምህራን ተናግረዋል፡፡

መምህራን በይፋ ከሚታወቁ የትምህርት ዕቅዶች ወጣ ብለው እንዳያስተምሩ ባለሥልጣናት ከልክለዋል፡፡ የኢህአዴግ አባላት ያልሆኑ መምህራን ወደማይፈለጉ ቦታዎች የሚዘዋወሩበት ዕድል ሰፊ እንደሆነ እና በደረጃ ዕድገት ወቅትም እንደሚዘለሉ በርካታ ሪፖርቶች ጠቁመዋል፡፡ የኢሕአዴግ አባል ያልሆኑ መምህራን የፓርቲ ስብሰባዎችን አልተካፈላችሁም በሚል ከሥራቸው እንደሚባረሩ የሚገልጹ አንዳንድ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡ የመምህራን የሰው ኃይል ምደባ ግልጽነት የጎደለው ከመሆኑም ሌላ፤ የድርጅት አባልነትን፣ ብሔርን ወይም ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ መድሎዎች እንደሚፈፀሙ በመግለጽ የአካዳሚክ ማኅበረሰቡ አባላት ቅሬታቸውን አሰምተዋል።

የግል ዩኒቨርስቲዎች በሕግ እና በመምህራን ትምህርት ዘርፍ የዲግሪ መርሀ ግብር እንዳይሰጡ ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው መመሪያ ይከለክላል፡፡ በተጨማሪም የግል ዩኒቨርሲቲዎች ሥርዓተ ትምህርታቸውን ሚኒስቴር ቀደም ሲል ካወጣው የተፈጥሮ ሣይንስ እና የማኅበራዊ ሣይንስ የአካዳሚ መርሃ-ግብሮች የ70/30 ድልድል ፖሊሲ ጋር እንዲያጣጥሙ መመሪያው ያዛል። በዚህ የተነሳ በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ማህበራዊ ሳይንስ የሚያጠኑ ተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል፡፡ የግል ዩኒቨርስቲዎች ሥርዓተ-ትምህርት ደግሞ በአመዛኙ በማኅበራዊ ሳይንስ ላይ አተኩሯል፡፡

የኦሮሞ ተማሪዎች በተቃዋሚነት በመጠርጠራቸው ወይም በሰላማዊ ሰልፎች በመሳተፋቸዉ መንግሥትን ይቃወማሉ በሚል ጥርጣሬ ክትትል ይደረግባቸው ነበር፤ በዘፈቀደም ይታሰሩ ነበር፡፡ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት፤ በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢዎች በርካታ የወታደር የደንብ ልብስ እና ሲቪል ልብስ የለበሱ የፀጥታ ሃይሎች በተለይ በኦሮሚያ ክልል ከተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፎች በፊት እና በኋላ ይሰፍራሉ፡፡

## ለ. ሰላማዊ የመሰብሰብና የመደራጀት ነፃነት

### የመሰብሰብ ነፃነት

ምንም እንኳ ህጉና ህገ-መንግሥቱ የመሰብሰብ ነፃነትን ቢፈቅዱም፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በበላይነት ከሚቆጣጠረዉ ኮማንድ ፖስት ፈቃድ እስካልተሰጠ ድረስ አዋጁ ሰልፎችና ህዝባዊ ስብሰባዎች እንዳይካሄዱ አግዷል፡፡ መንግሥት የመሰብሰብ ነፃነትን ካለማክበሩም ሌላ ዓመቱን ሙሉ በርካታ የተቃውሞ ሰልፈኞችን ገድሏል፤ አቁስሏል፤ አስሯል እናም በቁጥጥር ሥር አውሏል (ለተጨማሪክፍል 1.ሀ፣ 1.ለ፤ 1.ሐ፤ 1.መ፤ እና 1.ሠን ይመልከቱ) ፡፡ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ነበሩ፡፡ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ HRW በነሐሴ 7 ዘገባዉ የፀጥታ ሀይሎች ከኅዳር 2008 ወዲህ ከ500 በላይ መንግስትን የተቃወሙ ሰዎችን ገድሏል ሲል ግምቱን አስቀምጧል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ባለሙያዎች ጥር 13 እና መስከረም 30 ባደረጉት ጥሪ መንግስት "በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የሚያደርሰዉን ዓፈና" ያቁም ሲሉ አሳስበዋል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ክልሎችን ለመጎብኘት ያቀረበው ጥያቄ በመንግስት ውድቅ ተደርጓል፡፡ ጥቅምት 29 ቀን አምነስቲ ኢንተርናሽናል የሟቾች ቁጥር 800 እንደምሆን ግምቱን አስቀምጧል፡፡

ሐምሌ 30 እና ነሐሴ 1 በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች በትላልቅ እና አነስተኛ ከተሞች በተመሳሳይ ጊዜ ለተጠራው ሰልፍ በአጸፋዉ የፀጥታ ሃይሎች 100 የሚጠጉ ሰዎችን መግደላቸዉ ተዘግቧል (ክፍል1.ሀን ይመልከቱ) ፡፡

መስከረም 22 በቢሾፍቱ በነበረው የሃይማኖታዊ ስነሥርዓት በርካታ ሰዎች ለሞት እንደተዳረጉ ተዘግቧል፡፡ በበዓሉ ታዳሚዎች ለተቀሰቀሰው ተቃውሞ የፀጥታ ሃይሎች አስለቃሽ ጋዝ እና ወደ ሰማይ ጥይት መተኮስን ጨምሮ የሰጡት ምላሽ በፈጠረው ግርግር በርካታ ሰዎች ተረጋግጠው ሞተዋል፡፡ መስከረም 27 የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ቢሮ(OHCHR)፤ ምርመራ እንዲደረግና መንግሥት ገለልተኛ ታዛቢዎች ወደ ኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች እንዲገቡ እንዲፈቀ ድላቸዉ አሳስቧል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ባለሙያዎች ስብስብ መስከረም 30 ለመንግሥት ባደረጉት ጥሪ፤ የመስከረም 22ቱን ክስተት አጽንኦት የሰጡት ሲሆን፤ አለም ዓቀፍ የምርመራ ኮሚሽን ተቃውሞዎችንና ከህዳር 2007 ጀምሮ በተቃዋሚ ሰልፈኞች ላይ ያነጣጠረውን የሀይል እርምጃ ላይ ምርመራ ማካሄድ እንዲችል ፈቃድ እንዲሰጠዉ ጥሪ አድርጓል፡፡ በመንግሥት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በሁኔታው ላይ ምርመራ ያደረገ ሲሆን የምርመራው ውጤት እስካሁን አይታወቅም፡፡

ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አስቀድሞ፤ ከሁለት በላይ ሰዎችን የሚያሳትፉ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ወይም ሰልፎችን የሚያዘጋጁ አካላት፤ ለመንግሥት ከ48 ሰዓት በፊት ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

ባለሥልጣናት ፈቃድ መከልከል አይችሉም፡፡ ነገር ግን ለሕዝብ ደህንነትና ሰላማዊ እንቅስቃሴን ላለመገደብ ሲባል የስብሰባ ሰዓትና ቦታ ማስተካከያ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ባለሥልጣናት ስብሰባዎቹ በተለዋጭ ጊዜ እና ቦታ መካሄድ አለባቸው ብለው ካመኑ፤ አዘጋጆቹ የፈቃድ ጥያቄ ባስገቡ በ12 ሰዓታት ውስጥ በጽሑፍ ማሳወቅ እንዳለባቸው ህጉ ያስገድዳል፡፡ ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በኋላ፤ ቀደም ብለው የተሰጡ ፈቃዶች ዋጋ አልነበራቸውም፡፡

ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ድንጋጌ አስቀድሞ፤ መንግሥት ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የቀረቡ አንዳንድ የተቃውሞ ሰልፍ ጥያቄዎችን ውድቅ ያደረገ ሲሆን፤ ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ይሁንታን አግኝተዋል፡፡ የተቃውሞ ሰልፍ አዘጋጆች ተደጋጋሚ የመንግሥት ጣልቃ ገብነትን ሲኮንኑ፤ ባለሥልጣናት በበኩላቸው፤ በርካታ ለተቃውሞ የተቆረጡ ቀናትና ቦታዎች ላይ ለውጥ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ የተቃውሞ አዘጋጆች መንግሥት ለሕዝብ ደህንነት በሚል ሰበብ የተቃውሞ ጥያቄዎች በተለዋጭ ቦታና ሰዓት እንዲካሄዱ መፈለጉ አሳማኝ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

የታችኛው እረከን መስተዳድር ባለሥልጣናት ሁሉም ማለት ይቻላል የኢሕአዴግ ወገንተኛ በመሆናቸው፣ በየከተማው የሚገኙ የማዘጋጃ ቤት አዳራሾችን ይቆጣጠራሉ፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሕጋዊ የፖለቲካ ስብሰባ አዳራሾችን በሚጠይቁበት ወቅት እነዚህ የአካባቢ ባለሥልጣናት እንደሚከለክሏቸው አልያም የስብሰባውን መርሀ ግብር እንደሚያስተጓጉሉባቸው ጠቅሰው በርካታ ስሞታዎችን አቅርበዋል፡፡ የሆቴሎች እና የትልልቅ አዳራሾች ባለቤቶች በግልጽ የማይታወቁ ውስጣዊ ደንቦችን በመጥቀስ የፖለቲካ ፓርቲዎች አዳራሾቻቸውን እንዳይጠቀሙ ስለመከልከላቸው በርካታ ተአማኒ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ የክልል መስተዳድሮች ለትልልቅ ስብሰባዎች ፈቃድ ለመስጠትም ሆነ አስፈላጊውን የፀጥታ ኃይል ለመመደብ ያንገራግሩ ነበር። ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መውጣት በኋላ፤ ፈቃድ በሌለዉ ሰልፍ ወይም ትልልቅ ስብሰባዎች ላይ የተደረው ክልከላ በስብሰባዎች፤ ስልጠናዎች እና ሌሎች ጉባኤዎች ላይ ገደብ አስቀምጧል፡፡ ለምሳሌ በትንሹ፤ የአንድ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላት፤ አራት ሰዎች ብቻ የሚሳተፉበት ስብሰባ ለማድረግ እንደተከለከሉ አሳውቀዋል፡፡

### የመደራጀት ነፃነት

ምንም እንኳ ሕጉ የመደራጀት ነፃነትን እና በሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመሳተፍ ያልተገደበ መብትን ቢደነግግም መንግሥት ይህን መብት በከፍተኛ ሁኔታ ገድቧል (ክፍል3እና 5ን ይመልከቱ) ።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እና ተጓዳኝ ህጎች የማህበራት እንቅስቃሴን ገድቧል (ክፍል 5 በተጨማሪ ይመልከቱ) ፡፡ ግንኙነትን የሚመለከቱ ክልከላዎች እንዲሁም መቻቻልንና አንድነትን የሚጎዱ ድርጊቶች፤ ዘገባዎች እና ህዝባዊ መግለጫዎች ላይ የራስ በራስ ሳንሱር እንዲደረግባቸው አድርጓል፡፡ በህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የተጣለው ዕገዳ፤ ስብሰባዎች፤ የስልጠና ክፍለ ጊዜያት እና ሌሎች ጉባኤዎች እንዳይዘጋጁ ገድቧል፡፡ ከውጭ መንግሥት ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሀገርን ሉዓላዊነትን እና ብሔራዊ ደህንነትን አደጋ ላይ በሚጥል አኳኋን የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ወይም ግንኙነት ላይ የተደረገው ክልከላ፤ በሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መካከል እንዲሁም ከሌሎች ጋር የሚደረግን ግንኙነትን ቀንሷል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መመሪያዎች ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት "ኢ-ህገመንግሥታዊ ወይም የሀገርን ሉዓላዊነት እና ደህንነት በሚጎዳ አኳኋን ለሀገር ውስጥ ወይም ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች መግለጫ መስጠት" እንዳይችል ክልከላ አድርጓል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ምንጫቸው ያልተገለጸ ዕርዳታን ማድረግን ይከለክላል፡፡ በዚህም ምክንያት ለጋሾች በሙሉ ስማቸው ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን

ተገንዝበዋል፡፡ ይኸው አሠራር ለፖለቲካ ፓርቲዎች በሚደረጉ ልገሳዎች ሁሉ ላይ በተመሳሳይ መልኩ ተፈፃሚ ነበር፡፡

ከተባበሩት መንግሥታት ሰላማዊ የመሰብሰብ እና የመደራጀት መብት ልዩ ራፖርተር በ2004 ዓ.ም. የወጣ ሪፖርት እንደሚያመለክተው፤ "የእነዚህ ሕጎች [የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ] በሥራ ላይ መዋል ማህበራትን በማቋቋም እና ሥራ በመሥራት ላይ የከፋ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

በአገሪቱ ለመሥራት የሚፈልጉ ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማመልከቻቸውን በውጭ አገራት በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በኩል ማቅረብ ነበረባቸው፡፡ በመቀጠልም ማመልከቻው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ ይቀርባል።

**ሐ. የሃይማኖት ነፃነት**

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ያወጣውን *ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ሪፖርት* www.state.gov/religiousfreedomreport/ ድረገጽ ያገኛሉ።

**መ. የመንቀሳቀስ ነፃነት፣ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች ጥበቃ እና ሀገር አልባ ሰዎች**

ምንም እንኳ ሕጉ በአገር ውስጥ የመንቀሳቀስ፣ ወደ ውጭ አገር የመጓዝ፣ የመሰደድ፣ እና ወደ ሀገር የመመለስ ነፃነትን ቢያጎናፅፍም፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ህጎች በአገር ውስጥ ከቦታ ቦታ ዝውውርን ገድበዋል። በተጨማሪም መንግሥት የሀገር ውስጥ የመንቀሳቀስ ነፃነትን እና የውጭ ጉዞን ገድቧል፡፡

መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR) ጽ/ቤት እና ከሌሎች የረድኤት ድርጅቶች ጋር በመተባበር በአገር ውስጥ ለተፈናቀሉ ሰዎች፣ ለስደተኞችና ከስደት ተመላሾች፣ ለጥገኝነት ጠያቂዎች፣ለአገር አልባ ሰዎች እና ለሌሎች ስጋት ውስጥ የገቡ ሰዎች ከለላ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ባለስልጣናት እና ታጣቂ ቡድኖች አንዳንድ ጊዜ ፤በተለይም የፀጥታ ችግር ባሉባቸው የድንበር አካባቢዎች፤ የረድኤት ድርጅቶችን የመሥራት አቅም ውስን እንዲሆን አድርገዋል፡፡

<u>**የሀገር ውስጥ እንቅስቃሴ፡-**</u> የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ህጎች ዲፕሎማቶች ለኮማንድ ፖስቱ ቀድመው ሳያሳውቁና ፈቃድ ሳያገኙ ከአዲስ አበባ ውጭ ከ25 ማይሎች በላይ መጓዝ እንዳይችሉ ከልክሏል፡፡ መንግሥት ይህንን ክልከላ በህዳር ወር መጀመሪያ አንስቷል፡፡ በአማራ እና ኦሮሚያ በተወሰኑ አካባቢዎች የተከሰተዉ የፀጥታ ችግር የምግብ እና ሌሎች ሰብዓዊ ድጋፎች በጊዜያዊነት እንዳይቀርቡ አስተጓጉሏል፡፡

<u>**የውጭ ጉዞ፡-**</u> በ2005 ዓ.ም. መንግሥት ከህሎት አልባ ዜጎች ለሥራ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገራት እንዳይጓዙ በጊዜያዊነት የጣለው ዕገዳ ቀጥሏል፡፡ ክልከላው ለኢንቨስትመንት ወይም ለንግድ ጉዳዮች የሚጓዙ ዜጎች ላይ ተጽዕኖ አላሳደረም፡፡ መንግሥት ክልከላ ያደረገበትን ምክንያት ሲገልጽ በውጭ አገራት በተለይም በመካከለኛው ምሥራቅ በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው በሚሠሩ ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ወከባ፣ ማስፈራራት እና አሰቃቂ ጉዳት ለመከላከል ነው ብሏል፡፡

ባለስልጣናት የውጭ ጉዞ ስለመከልከላቸው በርካታ ዘገባዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ መጋቢት 14 የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ባለሥልጣናት በአዲስ አበባው ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ የኦፌኮ ሊቀመንበር የሆኑትን መረራ ጉዲናን ከሀገር እንዳይወጡ ከልክለዋቸዋል፡፡ በኋላም ሰኔ 8 መረራ ከሀገር እንዲወጡ የተፈቀደላቸው ሲሆን ባለሥልጣናት ሕዳር 21 በቁጥጥር ስር አውለዋቸዋል፡፡

ባለሥልጣናት ከዞን9 ጦማሪያን ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሰዎች ከሀገር እንዳይወጡ ከልክለዋል፡፡ ለምሳሌ፤ ባለሥልጣናት በህዳር 2007 የጦማሪ ዘላለም ክብረትን ፓስፖርት ነጥቀው የአለም ዓቀፍ ጉዞውን እንዳያደርግ ከልክለዋል፡፡ የአየር ማረፊያ የደህንነት ባለሥልጣናት እስረኛ የነበረ መሆኑን በማስታወስ ከሀገር መውጣት እንደማይችል ተናግረዋል፡፡ ባለሥልጣናት ግንቦት 24 ፓስፖርቱን የመለሱለት ሲሆን፤ በኋላም የውጭ ጉዞ ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡

**ስደት፡**- ልክ እንደ ቀደሙ ጊዜያት፤ ጋዜጠኞችን ጨምሮ ሌሎች ዜጎች ወደ ሀገር ቢመለሱ የመንግሥት ቂም በቀል መወጣጫ እንደሚሆኑ በመፍራት በራሳቸዉ ፍላጎት በውጭ ሀገር ኑሮአቸውን አድርገዋል፡፡

**በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች**

እንደ ዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ከሆነ፣ ከነሐሴ 2015 እስከ ነሐሴ 2016 ድረስ ባብዛኛዉ በኤል ኒ ኖ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የቆዩና አዲስ ተፈናቃዮችን ጨምሮ 684,064 በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ ይህ ቁጥር ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ብልጫ ያሳየ ነበር፡፡

በአገር ውስጥ ከተፈናቀሉት ውስጥ፤ 397, 296 በጎርፍ እና በግጭት ምክንያት ሲፈናቀሉ፤ 188,244 ኤል ኒኖ ባስከተለው ድርቅ የተፈናቀሉ ናቸው፡፡ ሌሎች 33,300 ደግሞ በተፈጥሮ ሀብት ቅርምት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው፡፡ በኤል ኒኖ ጉዳት ከደረሰባቸዉ አብዛኛዎቹ ወደ መኖሪያ ቀያቸው ተመልሰዋል፡፡

እንደ ዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ግምት፤ 657,224 ሰዎች ከአከባቢው ማኅበረሰብ ጋር የመቀላቀል፤ በሀገር ውስጥ መልሶ ሰፈራ ወይም ወደመኖሪያ ቀዬያቸዉ መመለስን የመሳሰሉ ዘላቂ መፍትሔ ያልተሰጣቸዉ ነባር ተፈናቃዮች ናቸው፡፡ የጎሳ እና የድርንበር ዘለል ግጭት፤ የተፈጥሮ አደጋ፤ በተፈናቃዮች መልሶ ሰፈራ ጊዜ የሚታዩ የፖለቲካ ወገንተኝነት ወይም ጎሰኝነት፤ እና መልሶ ለማስፈር የሚያስችል ሀብት እጦት ለተራዘመ መፈናቀል በምክንያትነት ይነሳሉ፡፡ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መካከል፤ 283,092 በሶማሌ፤ 148,482 በአፋር፤ 144,295 በኦሮሚያ፤ 47,950 በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና 13.245 በአማራ ክልሎች እንዲሁም 2.290 በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እና 2.055 በሐረሪ ክልል ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም፤ በጎርፍ ምክንያት የተፈናቀሉ 15.815 ሰዎች በእንቅስቃሴ ላይ ስለነበሩ በየትኛዉም ክልል መጠቃለል አልቻሉም፡፡

IOM በነሐሴ ሪፖርቱ 41,316 ሰዎች ወይም 7844 አባወራዎች በአማራ፤ ኦሮሚያ እና ሶማሌ ክልሎች በግጭት እና ጎርፍ ምክንያት እንደተፈናቀሉ ገልጿል፡፡ ከነሐሴ 18 እስከ መስከረም አጋማሽ ድረስ በግምት 8,000 ሰዎች ከአማራ ክልል ወደ ሰሜናዊ-ምሥራቅ ትግራይ ክልል ተንቀሳቅሰዋል፡፡ በርካታ ተፈናቃዮች በቅርቡ በክልሉ የተከሰተውን ግጭት ለመፈናቀላቸው በምክንያትነት ጠቅሰው-ብሔርን መሠረት ያደረገ (ትግሬ በመሆናቸዉ) የጥቃት ሰለባም እንዳይሆኑም አጠቃላይ ስጋት ነበራቸው፡፡ የፌደራል መንግሥት ተፈናቃዮችን ለማቋቋም ለትግራይ ክልል ስድስት ሚሊዮን ብር ($266,361) መድቧል፡፡ ገንዘቡ በርካታ የተፈናቃዮች ፍሰትን ላስተናገዱት ለሁመራ፤ አክሱም፤ መቀሌ እና ሽሬ ከተሞች ተከፋፍሏል፡፡ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ተፈናቃዮች ያስተናገደው ሽሬ ከተማ ለክልሉ ከተመደበው አጠቃላይ በጀት ላይ 2.6 ሚሊዮን ብር ($115,423) ተቀብሏል፡፡ የፌደራል መንግሥት ተፈናቃዮችን በዘላቂነት የማሰባጠር አማራጭን የሚያጠና በትግራይ ክልል የግብርና ቢሮ የሚመራ ኮሚቴ አቋቁሟል፡፡

እንደ IOM ግምት፤ ከደቡብ ሱዳን የመጡ የሙርሌ ጎሳ አባላት በጋምቤላ ክልል ሚያዝያ 7 በሰነዘሩት ጥቃት፤ ከ21,000 በላይ ሰዎች ተፈናቅለዋል (ክፍል6፤ ሌላ ማኅበራዊ ጥቃት እና አድልዎ ይመልከቱ) ፡፡

መንግሥት በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር የምግብ ዋስትና ዘርፍ (DRMFSS) አማካይነት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብዓዊ ድጋፍ በመስጠት ረገድ ንቁ ሚና መጫወቱን ቀጥሏል፡፡ ተፈናቃዮችን በመከታተል ረገድ በፌደራል እና ክልል የሚገኙ የDRMFSS ኃላፊዎች ከ IOM እና አጋሮቹ ጋር በትብብር ይሰራሉ፡፡

**የስደተኞች ጥበቃ**

**<u>ጥገኝነት ስለማግኘት፡</u>** የአገሪቱ ሕግ ጥገኝነት መስጠትን ወይም ስደተኞችን መቀበልን በሚመለከት ደንግጓል፤ መንግሥትም ለስደተኞች ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ያለቪዛ ወደ ሀገር መግባትን ከልክሏል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ሪፖርት መሠረት፣ አገሪቱ እስከ ነሐሴ ወር ድረስ 743,732 ስደተኞችን ተቀብላ አስተናግዳለች፡፡ ከስደተኞቹ ውስጥ አብዛኛዎቹ ከደቡብ ሱዳን (281,612) የመጡ ሲሆን፣ ከሶማሊያ (254,277) ፣ ከኤርትራ (161,615) ፣ ከሱዳን (39,317) እና ከሌሎች ሀገራት ይገኙበታል፡፡ 1,554 የየመን ዜጎችጥገኝነት ፍለጋ ተመዝግበው  ነበር፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) ፣ የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር ባለሥልጣን እና የሰብዓዊ ረድኤት ድርጅቶች በሱዳን የብሉናይል ክፍለሀገር የሚካሄደውን ግጭት በመሸሽ ወደ ኢትዮጵያ ለገቡ የሱዳን ስደተኞች እንክብካቤ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል፡፡ UNHCR እንዳስታወቀው፤ ከብሉ ናይል ክፍለሀገር በወርበአማካይ  1,500 አዳዲስ ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ ይገባሉ፡፡ በተጨማሪም ከደቡብ ሱዳን የላይኛው ናይል እና ዩኒቲ ግዛቶች ለመጡ እና ጥገኝነት ለጠየቁ ደቡብ ሱዳናውያን መንግሥት ድጋፍ አድርጓል፡፡ የማያባራ ግጭትና የምግብ እጥረት ደቡብ ሱዳናውያውያን ስደተኞች ወደ ሀገሪቱ የሚያደርጉትን ፍልሰት በማባባሱ፤ በነሐሴ በግምት 2,712 አዳዲስ ስደተኞች ወደሀገሪቱ እንደገቡ ታውቋል፡፡

ኤርትራውያን ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ አገሪቱ መግባታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ከነዚህም መካከል 23 በመቶ የሚሆኑት ብቻቸውን የሚሰደዱ ታዳጊዎች ነበሩ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከሚሰደዱት አብዛኛዎቹ በግብጽና ሱዳን አድርገው ለሁለተኛ ዙር ስደት ወደ አውሮፓ እና ሌሎች መዳረሻ ሃገሮች ይሰደዳሉ፡፡

**ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ነፃነት፡**- የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌዎች፤ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ከስደተኛ ካምፖች መውጣትን ከልክሏል፡፡ መንግሥት አንዳንድ የኤርትራ ስደተኞች ከካምፑ ውጭ እንዲኖሩ የሚፈቅደውን ፖሊሲ ቀጥሎበታል፡፡ መንግሥት በዋናነት ይህን ፈቃድ የሚሰጠው፤ በተለይ የከፍተኛ ትምህርት ለሚከታተሉ፤ ህክምና ለሚከታተሉ ወይም በካምፖች የፀጥታ ስጋትን ለማስወገድ ነው፡፡

***ሥራ የመቀጠር ዕድል፡***- መንግሥት ለስደተኞች የሥራ ፈቃድ አይሰጥም፡፡

**ዘላቂ መፍትሔዎች፡** መንግሥት ስደተኞች በቋሚነት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖሩ ቢፈቅድም፣ ዜግነት ማግኘት ወይም ከሕዝቡ መቀላቀል የሚችሉበትን ዕድል ግን አልሰጣቸውም፡፡ መንግሥት የተወሰኑ ስደተኞች ኢ-መደበኛ በሆነ የአኗኗር ዘይቤ ከካምፑ ውጭ የሚኖሩበትን ፖሊሲ ደግፏል፡፡ በተጨማሪም መንግሥትና የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን የትምህርት ክፍያ እየሸፈኑላቸው ተገቢውን ፈተና በማለፍ ዩኒቨርስቲ የሚገቡ ስደተኛ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፡፡

## ክፍል 3. ዜጎች በፖለቲካ ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸው ነፃነት

ዜጎች መንግሥታቸውን በሚስጢር በሚካሄድ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ባለው እና እኩል የመምረጥ መብት በሚከበርበት ነፃ፤ ፍትሐዊ እና ወቅቱን ጠብቆ በሚደረግ ምርጫ መሳተፍ እንዲችሉ ህገመንግሥቱ እና ህጉ ይፈቅዳል፡፡ ነገር ግን ገዢው ፓርቲ በምርጫ ረገድ ያለው ሰፊ የማሸነፍ ዕድል ይህንን መብት ገድቦታል፡፡

### ምርጫ እና የፖለቲካ ተሳትፎ

**በቅርቡ የተካሄዱ ምርጫዎች፡-** ግንቦት 2007 የሀገሪቱ ፓርላማ ለሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የተመረጡበት ብሔራዊ ምርጫ ተካሂዷል፡፡ በመስከረም 2008 ፓርላማው ኃይለማርያም ደሳለኝን በድጋሚ በጠቅላይ ሚኒስትርነት መርጧል፡፡

በግንቦት 2007 በተካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብ እንደራሴዎች ምርጫ፣ ኢሕአዴግ እና አጋር ድርጅቶች ያሉትን 547 መቀመጫዎች ሙሉ በሙሉ አሸነፉ፡፡ ይህም ፓርቲው በተከታታይ ለአምስተኛ ጊዜ ለአምስት ዓመታት በሥልጣን ላይ እንዲቆይ ያደርገዋል፡፡ የመንግሥት ክልከላ ድምጽ አሰጣጡን ገለልተኛ አካላት እንዳይታዘቡ በእጅጉ ገድቧል፡፡ የአፍሪካ ሕብረት ምርጫውን እንዲታዘብ የተፈቀደለት ብቸኛው ዓለም አቀፍ ድርጅት ነበር፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲ ታዛቢዎች ፖሊስን በጣልቃ-ገብነት፣ በማዋከብና በሕገ-ወጥ እስር ከሰዋል፡፡ የግል ጋዜጠኞች ምርጫውን ከምርጫ ጣቢያዎች ሲዘግቡ ጭምር መለስተኛ ችግሮች እንዳጋጠሟቸው ገልጸዋል፡፡ አንዳንዶቹም ወቅቱን ጠብቀው ፈቃድ ለማግኘት ቢያመለክቱም፤ ልክ ምርጫው አንድ ቀን ሲቀረው እንደተሰጣቸው ጠቁመዋል፡፡ ምርጫው ከመካሄዱ አስቀድሞ በስድስት ዙር የተካሄዱ የምርጫ ክርክሮች ከመጠነኛ አርትኦት ጋር ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚቻል ደረጃ በመገናኛ ብዙሃን ተላልፈዋል፤ ፡፡ በክርክሮቹ ዋና ዋና የሚባሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተካተዋል፡፡ ከ1997 አገራዊ ምርጫ ወዲህ በሥራ ላይ የዋሉ በርካታ ሕግጋት፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ስርዓቶች በጠቅላላው የምርጫ ሒደት ለኢሕአዴግ ግልጽ የተጠቃሚነት ዕድሎችን ፈጥረውለታል፡፡ ህገመንግሥቱ እንደሚደነግገው 50 በመቶ ሲደመር አንድ ድምፅ በሚል ቀመር የተዋቀረው የምርጫ ሥርዓት ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግን ጠቅሞታል፡፡ የተቃዋሚ ዕጩዎችን እና ደጋፊዎችን ማስፈራራትን ጨምሮ መንግሥት የተጠቀመባቸው ኢ-ፍትኃዊ ስልቶች ሪፖርት ተደርገዋል። ምርጫው ከመካሄዱ አስቀድሞና ምርጫውን ተከትሎ ስድስት ከምርጫ ጋር የተያያዙ ግድያዎች መፈፀማቸው ሪፖርት ተደርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በፖለቲካዊ ቁመናው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥገኛ በመሆኑ ከገዥው ፓርቲ ውጭ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በቦርዱ በሚተላለፉ የፓርቲዎች ምዝገባና የዕጩዎች መምረጫ መስፈርቶችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ ሀሳብ የመስጠት ዕድል አይኖራቸውም፡፡ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለመራጮች ትምህርት መስጠትን ጨምሮ፣ በምርጫ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የሬዲዮ መልዕክቶችን በማዘጋጀትና መመሪያዎችን አትሞ በተለያዩ ቋንቋዎች የማሰራጨት ኃላፊነት የተሰጠው ብቸኛው አካል ነው፡፡

ምርጫው ከመካሄዱ ቀደም ብሎ በነበረው ግምገማ የአፍሪካ ሕብረት መንግሥት የምዝገባ ሂደቱን በተሳካ መንገድ ማከናወኑን አድንቆ፤ ምርጫው "የተረጋጋ፣ሰላማዊና ተአማኒ" መሆኑን አመልክቷል፡፡ ይሁንና ምርጫው የተከናወነበትን ህጋዊ ማዕቀፍ በተመለከተ የሚያሳስቡት ጉዳዮች እንደነበሩም ገልጿል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከ35 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ መራጮችን የመዘገበ ቢሆንም፤ በምዝገባ ሂደቱ ምንም ዓይነት ፍትሐዊነት የጎደለው አሠራር ስለመኖሩ ሪፖርት አላደረገም፡፡

**<u>የፖለቲካ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ተሳትፎ፡</u> -** በኢህአዴግ ቁጥጥር ስር የሚገኘው መንግሥት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎችና በፌደራል መንግሥት ተገቢውን የፖለቲካ ውክልና አላገኘንም የሚሉ በተለይም የአማራ እና ኦሮሞ ብሔር አባላትን እንቅስቃሴ በኃይል ገድቧል፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌዎች የፖለቲካ

ፓርቲዎችን የስራ እንቅስቃሴዎች ገድቧል፡፡ ለምሳሌ፤ ህጎቹ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ "ኢ-ህገመንግሥታዊ እና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እና ደህንነት አደጋ ላይ በሚጥል አኳኋን ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች መግለጫ መስጠት" እንዳይችሉ ከልክሏል፡፡ ባለስልጣናት የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላትን በሽብር ድርጊት ተሳትፈዋል በሚል ውንጀላ ጭምር በቁጥጥር ስር አውለዋል፤ ለፍርድ አቅርበዋል (ክፍል 1፤ ሠ- "የፖለቲካ እስረኞች"ን ይመልከቱ) ፡፡የመንግሥት ባለሥልጣናት በህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የኦሮሞ ተቃዋሚ ድርጅቶች በርካታ አባላት በምስጢር የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አባላት ናቸው በማለት የሚወነጅሉ ሲሆን፣ በተጨማሪም ሰፋ ባለ ደረጃ የበርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት አላቸው በማለት ይከሰሳሉ፡፡

ባለስልጣናት የአፌኮ ዋና ፀሃፊ የሆነው አቶ በቀለ ነጋ ከታህሳስ 21፤2008 ዓ.ም. ጀምሮ በቁም እስር ላይ እንደሚገኝ አፌኮ ገልጿል፡፡ የፀጥታ ሰዎች በአዲስ አበባ ያለውን ቤቱን ለቆ እንዳይወጣ፤ ስልኩን እንዳይጠቀም ወይም ለመገናኛ ብዙሃን ምንም ዓይነት መግለጫ እንዳይሰጥ እንደነገሩት ተዘግቧል፡፡ ኃላፊዎች መረራ ጉዲናን እና በቀለ ገርባን ጨምሮ ሌሎች የአፌኮ መሪዎችን በቁጥጥር ስር አድርገዋል (ክፍል 1፤ሠ፡-የፖለቲካ እስረኞች እና በቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎች፤ ፍትሃዊ የፍርድ ሂደት መነፈግ ይመልከቱ)

ጥቅምት 1 ቀን ባለስልጣናት ብሌን መስፍንን እና ሌሎች ሦስት የሰማያዊ ፓርቲ አባላትን በቁጥጥር ሥር አውለዋል፡፡ ብሌን መስፍን "በሐሰተኛ ወሬ ህዝቡን አነሳስታለች" የሚል ክስ የቀረበባት ሲሆን ባለስልጣናት በዋስ እንዲትፈታ ትዕዛዝ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን የዋስትና መብቷ ተከብሮላት ከእስር በምትፈታበት ቀን፤ መልሰው በቁጥጥር ሥር በማዋል ክስ ሳይቀርብባት አስረዋታል፡፡ በኋላ በታሕሳስ 12 ከእስር የተፈታች ቢሆንም የቀረበባት ክስ ስለ መነሳት አለመነሳቱ በግልጽ አይታወቅም፡፡

የኢሕአዴግ አባል የፖለቲካ ፓርቲዎች ለአባሎቻቸው ጥቅሞችን ያስገኛሉ፤ አባል ፓርቲዎቹ በርካታ የንግድ ድርጅቶች ያሏቸው ሲሆን፣ የሥራ ዕድልና የንግድ ውሎችን ለታማኝ ደጋፊዎቻቸው ይሰጣሉ ተብሎ በሰፊው ይታመናል፡፡ በርካታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የቤቶች ወይም የሕንፃ ባለቤቶች ንብረታቸውን ለእነርሱ እንዳያከራዩ የኢህአዴግ አባላት ጫና እንደሚፈጥሩ ወይም እንደሚያስፈራሯቸው በመጥቀስ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶች አልያም ሕንፃዎችን ለመከራየት መቸገራቸውን ተናግረዋል፡፡ መምህራን እና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባል በመሆናቸው ከሥራ እንደታገዱ የሚገልጹ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን፣ በተለይም መምህራንን፣ ከሥራ እንደሚያባርራቸው በመዛት ያስፈራራቸው እንደነበር የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተናግረዋል፡፡ የገዢው ፓርቲ አባላት ያልሆኑ ሥራ ፈላጊ ወጣቶች፣ ሥራ መፈለጊያ የድጋፍ ደብዳቤ ከቀበሌያቸው እና ከአካባቢ አስተዳደር መዋቅሮች በቀላሉ እንደማያገኙ ሪፖርቶች ጠቁመዋል፡፡

በምርጫ ቦርድ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአካባቢ ጽሕፈት ቤቶችን ለመክፈትና ለመጠቀም የግድ ከክልል መንግሥታት ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች የክልል ጽሕፈት ቤቶቻቸውን ለመክፈት ፈቃድ ለማግኘት በመቸገራቸው ለመደራጀትና ቅስቀሳዎችን ለማካሄድ መቸገራቸውን ገልጸዋል፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሕዝባዊ ስብሰባዎችንና ቅስቀሳዎችን ለማካሄድ ፈቃድ ማግኘት እንዳሚኖርባቸው የሚደነግጉ ህግጋት የተቃዋሚ ፓርቲ እንቅስቃሴዎችን ለመግታት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

**<u>የሴቶች እና የህዳጣን ተሳትፎ፡-</u>** ሴቶች ወይም ህዳጣን የሆኑ ማህበረሰቦችን ድምጽ ከመስጠት አልያም በፖለቲካ ከመሳተፍ የሚከለክሉ ሕጎች የሌሉ ቢሆንም፤ በከፍተኛ ሁኔታ የወንዶች የበላይነት የሚታይበት ማኅበረሰብ መኖሪያ የሆኑ አንዳንድ ክልሎች ውስጥ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ተገድቧል፡፡ ሴቶች በተመራጭነትም ሆነ በሹመት ያላቸው ውክልና እጅግ አናሳ ነው፡፡ ከጥቅምቱ የካቢኔ ሹምሽር በኋላ፤ ከሦስቱ አንዱን የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታዎች ጨምሮ፤ ሴቶች ካሉት 22 የፌደራል መንግሥት

ሚኒስትር ቦታዎች 3ቱን ይዘዋል፡፡ ፓርላማው ካሉት 547 መቀመጫዎች 212ቱ በሴቶች ተይዘዋል፡፡ በመላ አገሪቱ ካሉ ምክር ቤቶች ከፍተኛ የሴቶች ቁጥር ያለው የትግራይ ክልል ምክር ቤት ነው፡፡ ከአባላቱ 50 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው (ከ152 መቀመጫዎች 76ቱ በሴት አባላት የተያዙ ነበሩ) ፡፡

ብሄርን መሰረት ያደረገው ፌደራላዊ አወቃቀር በሀገሪቱ ያሉ ዋና ዋና ብሔረሰቦች በፌደሬሽን ምክር ቤት (ከሁለቱ ምክር ቤቶች አንዱ በሆነው) ውክልና እንዲኖራቸው አድርጓል  በሀገሪቱ ከ80 በላይ ብሔረሰቦች ያሉ ሲሆን፤ ህዳጣን ብሔረሰቦች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውክልና አልነበራቸውም።

## ክፍል 4. ሙስና እና በመንግሥት አሰራር የግልጽነት አለመኖር

ሕጉ በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ለሚፈፀም ሙስና የወንጀል ቅጣት ደንግጓል፡፡ ምንም እንኳ መንግሥት አንዳንድ የሥራ ኃላፊዎችን ለፍርድ ቢያቀርብም፣ በርካታ ባለሥልጣናት የሙስና ተግባራትን እየፈጸሙ ክስ ሳይመሰረትባቸው ቀጥለዋል፡፡ መንግሥት ሙስናን መዋጋት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን በህዝባዊ መግለጫዎች ቢጠቅስም፤ በመንግሥት ውስጥ ሙስና መስፋፋቱን የሚጠቁሙ አመለካከቶች አሉ፡፡

***ሙስና፡-*** በፖሊስ እና በፍርድ ቤት አካባቢ የሚፈፀሙ በጉቦ የመደለል  ተግባራት ያልተቀረፉ ችግሮች ሆነው ቀጥለዋል፡፡ አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት የመሬት አቅርቦት ሂደትን መጠቀሚያ እንደሚያደርጉት የሚታሰብ ሲሆን፤ በመንግሥት እና በፓርቲ የተያዙ ድርጅቶች የመሬት ሊዝ እና ብድር በማግኘት ረገድ የቅድሚያ ተጠቃሚነት ዕድል ነበራቸው። የፌደራል አቃቤ ህግ የሙስና ጉዳዮችን የመመርመር እና ለፍርድ የማቅረብ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

መንግሥት በኦሮሚያ ለተከሰቱት አንዳንድ አለመረጋጋቶች ሙስናን በምክንያትነት ጠቅሷል፡፡ ለምሳሌ፤ ፤ ባለስልጣናት ሰኔ 2 በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ የነበሩትን አቶ ዘላለም ጀማነህን በሙስና ጠርጥረው በቁጥጥር ስር አውለዋል፡፡

በከባድ ሙስናና የሕዝብና የመንግሥት ገንዘብ በመበዝበዝ ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር የዋሉት የቀድሞ የኦሮሚያ ክልል የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ የነበሩት የአቶ ወንድሙ ቢራቱ ቀነዓ የክስ ሂደት በዓመቱ መጨረሻም መሰማቱን ቀጥሏል፡፡

ግንቦት 9 ከፍተኛው ፍርድ ቤት በዋለው ችሎት፤ በ2005 ዓ.ም. በቁጥጥር ሥር የዋሉትን የቀድሞ ምክትል የደህንነት ኃላፊ የሆኑትን ወልደሥላሴ ወልደሚካኤልን ስልጣንን ያለአገባብ በመጠቀም እና ምንጩ የማይታወቅ ሀብት በማፍራት በሚል የጥፋተኝነት ውሳኔ የ10 ዓመት እስራት እና የ50,000 ብር ($2,220) የገንዘብ ቅጣት አስተላልፏል፡፡

***ሀብትን ማሳወቅ፡-*** ሕጉ ሁሉም የመንግሥት ባለሥልጣናት እና ሠራተኞች ሀብታቸውን እና የግል ንብረታቸውን በይፋ እንዲያስመዘግቡ ይጠይቃል፡፡ ይህንን ደንብ በማይፈጽሙ ላይ የገንዘብ እና በወንጀል ተጠያቂነት ቅጣቶች እንደሚጣለባቸው ሕጉ ያትታል፡፡ ፕሬዚዳንቱና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀብታቸውን አስመዝግበዋል፡፡  በ ሚያዚያ እና ሐምሌ 2007 መካከል የፌደራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ26.584 ተሿሚዎችን፤ ባለሥልጣናትን እና ተቀጣሪዎችን ሀብት መመዝገቡን አስታውቋል፡፡ ኮሚሽኑ በተጨማሪም በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ ዳግም የሀብት ምዝገባ አድርጓል፡፡ እስከ ህዳር ወር 2008 ዓ.ም. ድረስ 95,000 የሚሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሕጉ በሚያዘው መሠረት ሃብታቸውን አስመዝግበዋል፡፡

የሀብት መጠን የተመዘገበባቸው ሰነዶች በፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይዞታ ሥር ይገኛሉ፡፡ በሕጉ መሰረት እነዚህን ሰነዶች መመልከት የፈለገ ግለሰብ ጥያቄውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ ሆኖም የፌዴራል ስነምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አስፈላጊ ነው ብሎ ካላመነ በቀር የቤተሰብን ሃብት የተመለከተ መረጃ ማግኘት አይቻልም፡፡

***<u>መረጃን ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ፡-</u>*** ህዝብ ስለ መንግሥት አሠራር መረጃዎችን የማግኘት መብት እንዳለው ህጉ ቢደነግግም፣ የመረጃ ተደራሽነት በአብዛኛው ተገድቧል። ሕጉ መረጃ ይፋ የማይደረግባቸውን ጥቂት ሁኔታዎች ከነምክንያታቸው ይዘረዝራል፡፡ በአጠቃላይ የመረጃ ጥያቄ በጽሁፍ በቀረበ 30 ቀናት ውስጥ ምላሽ መሰጠት ያለበት ሲሆን፤ ክፍያውም ለጥያቄው ምላሽ በመስጠት ከሚወጣው ወጪ መብለጥ የለበትም፡፡ ይህን ህግ በማያከብሩ ባለስልጣናት ላይ ቅጣት ስለሚጣልበት አግባብ እና የመረጃ መከልከልን ተከትሎ ይግባኝ የሚጠየቅባቸው ሁኔታዎች በህጉ ተካተዋል፡፡ በዓመቱ ውስጥ መረጃ መስጠትን ወይም መከልከልን የተመለከተ መረጃ አልተገኘም።

መንግሥት ሕግጋትና ደንቦች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙ ያደርጋል። የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ከመንግሥት፣ ከመገናኛ ብዙኃን እና ከሕዝብ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን ይመራል፡፡ የግሉ ፕሬስ አባላት ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መንግሥት ብዙ ጊዜ ምላሽ አይሰጥም ሲሉ ሪፖርት አድረገዋል፡፡

## ክፍል 5. በዓለም አቀፍ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚካሄድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምርመራን በተመለከተ የመንግሥት አመለካከት

ምንም እንኳ በመንግሥት ከፍተኛ ገደብ ቢጣልባቸውም፣ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ አገር በቀል የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እንቅስቃሴ አድርገዋል። በአጠቃላይ መንግሥት አገር በቀል የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን እና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ታዛቢዎችን እንቅስቃሴ በጥርጣሬና በጥንቃቄ ይመለከታል። በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉ መገናኛ ብዙኃን ሂዩማን ራይትስ ዋችን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን ይነቅፋሉ።

የበጎ-አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ፤ ከሚሰበስቡት ገንዘብ ከ10 ከመቶ በላይ ከውጭ ምንጮች የሚያገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ "ሶሳይቲዎች" እና ማኅበራት (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማኅበረሰብ ደርጅቶች) ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብትን፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትን፣ ሥርዓተ-ፆታን፣ ሃይማኖትን፤ የሕፃናት እና የአካል ጉዳተኞች መብቶችን፣ የግጭት አፈታት ወይም እርቅን፤ እንዲሁም የፍትህ አገልግሎት እና የሕግ አስፈፃሚ አካላት ብቃት ጉዳዮችን ለሚያራምድ ዓላማ መንቀሳቀስ የማይችሉ መሆኑን ደንግጓል። ህጉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መልካም አስተዳደር፣ ሰብዓዊ መብቶች፣ ሙስና፣ ግልፅ አሠራር ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በአስከፊ ሁኔታ ከመገደቡም በላይ፤ በርካታ በመልካም አስተዳደርና በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጉዳዮቹ ዙሪያ የሚሠሩትን ሥራ አቁመዋል ወይም በአዲሱ ህግ አማካይነት እንደ አዲስ ምዝገባ በማካሄድ ከመብቶች ጋር ተያያዥነት በሌላቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ለማተኮር ተገደዋል፡፡

አንዳንድ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ከገቢያቸው ከ10 በመቶ በላይ ከውጭ ለጋሾች ማሰባሰብ በማይችሉበት፣ ማለትም ተለይተው በተጠቀሱት ዘርፎች ለመንቀሳቀስ በሚያስችለው አገር-በቀል ማኅበርነት፣ አልያም ከገቢያቸው ከ10 በመቶ የበለጠውን ከውጭ ለጋሾች መሰብሰብ በሚፈቅደው፣ ነገር ግን ተለይተው በተጠቀሱት ዘርፎች መንቀሳቀስን በሚከለክለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ማኅበርነት መመዝገብ ቀጥለዋል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እና እሱን ተከትሎ የወጡ ድንጋጌዎች የማህበራትን የመሥራት አቅም ገድቧል፡፡ ግንኙነትን እንዲሁም መቻቻልን እና አንድነትን የሚሸረሽሩ ተግባራት ላይ የተጣለው ክልከላ፤ ዘገባዎች እና ህዝባዊ መግለጫዎች የራስ በራስ ሳንሱር እንዲደረግባቸው አድርጓል፡፡ ፍቃድ የሌላቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የተጣለው እገዳ፤ ስብሰባዎች፤ የሥልጠና ጊዜያት እና ሌሎች የመሰብሰብ አጋጣሚዎችን ገድቧል፡፡ ከውጭ መንግሥት ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሀገርን ሉዓላዊነት እና ደህንነት ጎጂ በሆነ አኳኋን በሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ወይም ግንኙነት ላይ የተጣለው ዕገዳ፤ ሀቀር-በቀል እና ዓለም አቀፍ ማህበራት እንዲሁም ሌሎችም ያላቸውን ግንኙነት አኮስሷል፡፡ በተወሰኑ ቦታዎች ተግባራዊ የሆነው የሰዓት ዕላፊ፤ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን የተመለከቱ ምርመራዎችን አስተጓጉሏል፡፡ ሁሉም ተቋማት በህግ አስከባሪ አካላት ሲጠየቁ መረጃ እንዲሰጡ የተጣለባቸው ግዴታ፤ የመረጃ ምስጢራዊነት ላይ ስጋትን ፈጥሯል፡፡

ባለሥልጣናት በሐምሌ፤ ነሐሴ እና ጥቅምት ሰባት የኢሰመጉ አባላትን በቁጥጥር ሥር አውለዋል፡፡ በጥቅምት 13፤ ባለሥልጣናት የኢሰመጉን 25ኛ ዓመት የምስረታ በዓልን ምክንያት በማድረግ እየተካሄደ የነበረውን የገቢ ማሰባሰብያ ዝግጅት በትነዋል፡፡ ምንም እንኳ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ዝግጅቱን ለማካሄድ ጠይቆ ፈቃድ ያገኘ ቢሆንም፤ ድርጅቱ ከኮማንድ ፖስቱ (command post)ተጨማሪ ፈቃድ አላገኘም ብለዋል፡፡ ከሕዳር 18 ጀምሮ በትንሹ ሦስት የኢሰመጉ አባላት በእስር ይገኛሉ፡፡

መንግሥት አብዛኞቹ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፌደራል ማረሚያ ቤቶችን፣ ፖሊስ ጣቢያዎችን እና አድራሻቸው የማይታወቅ እስር ቤቶችን እንዳይጎበኙ ከልክሏል። መንግሥት ከሀገር ውጭ ገንዘብ የማሰባሰብ ክልከላው የሚመለከተው አንድ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅትን ያለገደብ ገንዘብ ከውጭ ምንጮች በማሰባሰብ የታሳሪዎችን ጥየቃ መሠረት ባደረገ የሰብዓዊ መብቶች ጥብቅና እንዲሰማራ ፈቅዷል፡፡ አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ታራሚዎች ምህረት የሚያገኙበትን ዕድል በማመቻቸት አዎንታዊ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ባለሥልጣናት፤ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፣ መገናኛ ብዙሃን፣ የረድኤት ድርጅቶች እና የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ወደ ተወሰኑ አካባቢዎች እንዳይሄዱ ገደብ ጥለዋል፡፡

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ችግር ወዳለባቸው አካባቢዎች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዙሪያ መንግሥት የጠራ ፖሊሲ የለውም፡፡ ይህም የክልል መንግሥታት የሥራ ኃላፊዎችና ወታደራዊ መኮንኖች ወደ እነዚህ አካባቢዎች ለመግባት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ወደ ፌደራል መንግሥት እንዲመሩ አድርጓቸዋል፡፡ ባለስልጣናት ጋዜጠኞችን ወደተወሰኑ አካባቢዎች ከመግባታቸው በፊት እንዲመዘገቡ ጠይቀዋል ወይም መግቢያ ከልክለዋል፡፡ የክልል ፖሊስ ወይም የአካባቢ ሚሊሽያዎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተወሰኑ ቀናትና በተወሰኑ ቦታዎች ሊያደርጉት የነበረውን እንቅስቃሴ፣ የፀጥታ ችግርን እንደ ምክንያት በመጥቀስ፣ እንደገደቡ ሪፖርቶች አመልክተዋል፡፡

**<u>የተባበሩት መንግሥታት ወይም ሌሎች ዓለምአቀፍ አካላት፡-</u>** የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሺነር ቢሮ ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ባለሞያዎች ምርመራ ለማካሄድ ያቀረቡትን ጥያቄ ለመቀበል መንግሥት አልተባበረም፡፡ በነሐሴ ወር ኮሚሽነሩ መንግሥት ገለልተኛ ታዛቢዎችን ወደ ኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች እንዲገቡ ፈቃድ እንዲሰጣቸው አሳስቧል፡፡ ኮሚሽነሩ በሁለቱ ክልሎች ተፈጽሟል የተባለው ከመጠን ያለፈ የኃይል አጠቃቀም መጣራት እንዳለበት አሳስበው ነበር፡፡ መንግሥት ነሐሴ 5 በቃል አቀባዩ በኩል ለአንድ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በሰጠው መግለጫ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የራሱን ሀሳብ የማንጸባረቅ መብት ቢኖረውም፤ መንግሥት የዜጎቹን

ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን ይወጣል በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ቃል አቀባዩ መንግሥት የራሱን ምርመራ እንደሚያካሂድ ገልጸዋልል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሺነር ቢሮ በቢሾፍቱ ሀይማኖታዊ ክብረበዓል ላይ የተከሰተውን ሞት ተከትሎ ገለልተኛ ታዛቢዎች በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች መግባት የሚያስችላቸውን ፈቃድ እንዲሰጣቸው መስከረም 27 ለመንግሥት በድጋሚ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ መስከረም 30 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ባለሙያዎች መንግሥት ለዓለም አቀፍ የመርማሪ ቡድን ፈቃድ እንዲሰጥ አሳስበዋል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የማሰቃየት እና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው ኢሰብዓዊ ወይም አዋራጅ አያያዞች እና ቅጣቶችን የሚከታተሉ ልዩ ራፖርተር አገሪቱን ለመጎብኘት ያቀረቡት ጥያቄ ምላሽ አላገኘም፡፡

<u>**የመንግሥት የሰብዓዊ መብት አካላት፡-**</u> የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በመቶዎች የሚቆጠሩ የሰብዓዊ መብት ጥሰት አቤቱታዎችን እንደመረመረ፤ የመስክ ምርመራ እንዳደረገ፤ የማረሚያ ቤቶችን ይዞታ ለማሻሻል የሚረዳ  ሀሳብ ለማቅረብ በሚል በማረሚያ ቤቶች ጉብኝት እንዳደረገ፤ እንዲሁም ዓመታዊ እና  ወቅታዊ ዘገባዎችን እንዳወጣ ተገልጿል፡፡ ኮሚሽኑ ሰኔ 3 ለፓርላማው ባቀረበው ሪፖርት፤ በኦሮሚያ 28 የፀጥታ ኃይል አባላትን እና ባለሥልጣናትን ጨምሮ የ173 ሚቾችን አስከሬን መቁጠሩንና የፀጥታ አካላት በወቅቱ የወሰዱት እርምጃ ተመጣጣኝ እንደሆነ ገልጿል፡፡ ኮሚሽኑ የአማራ ክልል ልዩ የፀጥታ ኃይል በቅማንት ማኅበረሰብ ላይ ከመጠን ያለፈ ኃይል መጠቀሙን አረጋግጫለሁ ብሏል፡፡  ነገር ግን ኮሚሽኑ ሪፖርቱን ለህዝብ ይፋ አላደረገም፡፡ ኮሚሽኑ ነሐሴ 28 በቅሊንጦ ማረሚያ ቤት የተከሰተውን የእሳት አደጋም መርምሯል፡፡ ኮሚሽኑ ከ22 ዩኒቨርሲቲዎች እና ከሁለት የሲቪክ ማህበራት ማለትም ከኢትጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር እና ከኢትዮጵያ ክርስቲያን ጠበቆች ፌሎሽፕ ጋር በመተባበር 112 የሕግ ድጋፍ የሚሰጡ ማዕከላትን አንቀሳቅሷል፡፡

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በአስፈጻሚው አካል ሥር ባሉ መሥሪያ ቤቶች ተፈጽመዋል የሚባሉ ከአስተዳደራዊ በደሎች ጋር የተያያዙ አቤቱታዎችን ተቀብሎ የመመርመር ሥልጣን አለው። ከሐምሌ 2007 እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም. ተቋሙ 2,849 ያህል አቤቱታዎችን ተቀብሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ (ከቀደመው ዓመት የተላለፉ 209 ጉዳዮችን ጨምሮ) በ1,231 አቤቱታዎች ላይ ምርመራ ያካሄደ ሲሆን፤ ከሥልጣን ወሰኑ ውጭ የሆኑ 1.827 ጉዳዮችን ወደ ሌሎች ቢሮዎች መርቷል፡፡ ቢሮው ምርመራ ካካሄደባቸው 1.231 አቤቱታዎች ውስጥ የ1.010 (82% ) እልባት እንደሰጠ ርፖርት አድርጓል፡፡ 221 በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡አብዛኛዎቹ አቤቱታዎች ከመሬት፣ ከሕዝባዊ አገልግሎቶች አስተዳደር፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ መጓተት፣ ፣ ኢፍትሐዊ ውሳኔዎች፤ እንዲሁም ከማኅበራዊ ዋስትና እና የመረጃ ነጻነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነበሩ፡፡

## ክፍል 6. አድልዎ፣ ማኅበራዊ ጥቃት እና ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

## ሴቶች

<u>**አስገድዶ መድፈርና የቤት ውስጥ ጥቃት፡-**</u> አስገድዶ መድፈር በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል ሲሆን፤ እንደ ድርጊቱ ክብደት ከ5 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል። ሆኖም በትዳር ውስጥ ስለሚፈፀም አስገድዶ መድፈር  በህጉ በግልጽ የተቀመጠ ነገር የለም። መንግሥት ሕጉን በተሟላ ሁኔታ ተፈጻሚ አላደረገውም፤ የዚህም አንዱ ምክንያት ድርጊቱን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያለማድረግ መጠነ-ሰፊ የሆነ ችግር ስላለ ነው፡፡ ወንጀል ከፈፀሙ ግለሰቦች መካከል ምን ያህሉ ክስ እንደተመሠረተባቸው፣ እንደተፈረደባቸው አልያም እንደተቀጡ የሚጠቁም የተጠናቀረመረጃ አልተገኘም።

የቤት ውስጥ ጥቃት ሕገ-ወጥ ሆኖ ሳለ፣ በአስገድዶ መድፈር እና በቤት ውስጥ ጥቃት ላይ በመንግስት የተወሰደው የሕግ እርምጃ ወጥነት የጎደለው ነበር፡፡ በትዳር ውስጥ የሚፈፀም ጥቃትን ጨምሮ የቤት ውስጥ ትቃት በስፋት የሚከሰት ማኅበራዊ ችግር ነው፡፡ ወንጀል ፈጻሚዎቹ እንዳደረሱት ጉዳት አስከፊነት፣ ከአነስተኛ የገንዘብ መቀጮ ጀምሮ እስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣሉ።

ምንም እንኳ ሴቶች ለፖሊስና ለፍርድ ቤቶች በማመልከት የሕግ ከለላ ማግኘት ቢችሉም፣ በተለይ በገጠር አካባቢዎች ያለው ማኅበረሰብ አመለካከት እና የመሠረተ ልማት አለመስፋፋት ብዙ ሴቶች ጉዳያቸውን ወደ ሕግ እንዳይወስዱ ገድቧቸዋል። በዚህ ረገድ መንግሥት ክስ የመሠረተባቸው አጥፊዎች ቁጥር ውሱን ነበር።

የቤት ውስጥ ጥቃት እና የአስገድዶ መድፈር ክሶች ብዙ ጊዜ ከመጓተታቸውም ሌላ ቅድሚያ አልተሰጣቸውም። ጾታን መሠረት ካደረገ ጥቃት አኳያ በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ከፍተኛ ክፍተት መታየቱ ቀጥሏል፤ የዚህም ምክንያት ደካማ የመረጃ አያያዝ እና ምርመራ ነበር። በሴቶች እና በወጣት ሴቶች ላይ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተፈጽሟል፤ ነገር ግን ከባህላዊ ተቀባይነት፣ ከኃፍረት፣ ከፍርሃት ወይም የሕግ ጥበቃ እንዳለ ካለማወቅ የተነሳ ከትክክለኛ አሃዙ ያነሰ ሪፖርት ተደርጓል።

“ለሕፃናት ተስማሚ” የሆኑ ችሎቶች በተለይ ሕፃናት እና ሴቶች ላይ የተፈፀሙ የጥቃት ወንጀሎችን ይዳኛሉ፡፡ የፖሊስ አባላት በሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች እና በሴቶችና ሕጻናት ሚኒስቴር አማካኝነት የቤት ውስጥ ጥቃትን በተመለከተ ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በውስጡ የሴቶችና የሕፃናት መብቶች ኮሚሽነር አለው።

<u>**የሴት ልጅ ግርዛት/ብልት ትልተላ፡-**</u> የሴት ልጅ ግርዛት/ብልት ትልተላ ሕገ-ወጥ መሆኑ ቢደነገግም፤ መንግሥት ሕጉን አላስፈፀመም፤ ጥፋተኞችንም አልቀጣም፡፡ አንድ የተባበሩት መንግሥታት የህጻናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) ጥናት እንዳመለከተው 74 በመቶ የሚሆኑ ሴቶችና ልጃገረዶች ግርዛት ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሴት ልጅን በከፊል የገረዘ በሦስት ወራት እሥራት ወይም በ500 ብር መቀጣት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሙሉ ግርዛት ከ5 እስከ 10 ዓመት እስራት ያስቀጣል፡፡ ይሁን እንጂ በሴት ልጅ ግርዛት ዙሪያ የተመሠረቱ ክሶች አልነበሩም፡፡

የሴት ልጅ ግርዛት እየቀነሰ ቢሆንም የተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት አድን ድርጅት በ2003 ዓ.ም. ዌልፌር ሞንተሪንግ ሰርቬይ (Welfare Monitoring Survey) ያካሄደውን የዳሰሳ ጥናት በመጥቀስ እንደገለጸው ከውልደት እስከ 14 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉ ልጃገረዶች 23 በመቶው ግርዛት ተፈጽሞባቸዋል፡፡ የሴት ልጅ ግርዛትን በሚመለከት የሚወጡ አሃዞች ልዩነት ቢያሳዩም፤ በ2005 የወጣ አንድ ሪፖርት ልማዱ በአፋር እና ሶማሌ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በስፋት እንደሚዘወተር ይገልፃል፡፡ በከተሞች አካባቢ የሴት ልጅ ግርዛት እምብዛም ጎልቶ የታየ ችግር አልነበረም፡፡

አንዲት ሴት ልጅ የምትገረዝበት የዕድሜ ክልል እንደየብሔረሰቡ፣እንደሚፈጸመው የግርዛት ዓይነት፤ እንዲሁም እንደየክልሉ ይለያያል፡፡ በሰሜኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሴት ልጅ የምትገረዘው እንደተወለደች ሲሆን፤በደቡቡ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሥነ ሥርዓቱ ከኃብቻ ጋር ስለሚያያዝ፤ተግባሩ የሚፈጸመው ሴት ልጅ ዕድሜዋ ከፍ ሲል ነው፡፡ ሴት ሕጻናት ተወልደው ሰባት ቀን ሲሞላቸው “ቂንጥር” የተሰኘው የብልታቸው አካል ወይም የብልታቸው የውጪኛው ክፍል ይቆረጣል፡፡ ለአቅመ ሔዋን የደረሱ ሴቶች ደግሞ ብልታቸው ተተልትሎ የሚሰፋበት የመጨረሻውና እጅግ አደገኛ የሆነው የግርዛት አይነት ይፈጸምባቸዋል፡፡ መንግሥት አጥፊዎችን ወደ ሕግ ከማምጣት ይልቅ ችግሩን በመንግሥት ትምህርት ቤቶች በሚሰጡ አጫጭር ትምህርቶች፣በጤና ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር፣ በመገናኛ ብዙሃን ዘመቻዎች የመግታት እስትራቴጂ ይከተላል፡፡ መንግሥት የወሰደውን የግንዛቤ ማስጨበጫና አጥፊዎችን ወደ ሕግ

ያለማቅረብ አካሄድ በመከተል የተለያዩ ዓለም አቀፍ ለጋሾችና የግል ድርጅቶች የሴት ልጅ ግርዛት ችግርን ለመቅረፍ ማኅበረሰቡን በማስተማር ረገድ አመርቂ እንቅስቃሴዎችን አድርገዋል፡፡

**ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፡-** በጠለፋ ማግባት ሕገ-ወጥ ድርጊት ቢሆንም፣ መንግሥትም ጠለፋን ለማስቀረት ሙከራዎች ቢያደርግም፣ ድርጊቱ ግን በአንዳንድ ክልሎች ቀጥሏል ። በጠለፋ የሚከናወኑ አብዛኛዎቹ ጋብቻዎች በኃይል የሚፈፀሙ ወሲባዊ ግንኙነቶችን የሚያካተቱ ሲሆን በአብዛኛው ጠለፋ በሚከናወንበት ጊዜ ሴቶች አካላዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡ የጠለፋ ድርጊቶች በቤተሰቦች፣ በማኅበረሰቦች እና በጎሳ ቡድኖች መካከል ግጭቶችን ይቀሰቅሳሉ፡፡ ጠለፋን መሠረት ባደረገ ጋብቻ ተጎጂዋ ከጠላፊዋ ጋር ለመጋባት ከተስማማች ጠላፊው አይቀጣም።

**ወሲባዊ ትንኮሳ፡-** ወሲባዊ ትንኮሳ በስፋት ተስተውሏል፡፡ የወንጀል ሕጉ ድርጊቱን በሚፈፅሙ ላይ ከ18 እስከ 24 ወራት የሚደርስ የእስራት ቅጣት ይደነግጋል። ነገር ግን፣ ባለሥልጣናት ከትንኮሳ ጋር የተያያዙ ሕጎችን ተፈጻሚ አላደረጉም።

**የሥነ-ተዋልዶ መብቶች፡-** ግለሰቦች እና ጥንዶች የልጆቻቸውን ብዛት፣ በምን ያህል ጊዜ አራርቀው መውለድ እንዳለባቸው እና የሚወልዱበትን ጊዜ በነፃነት እና በኃላፊነት ስሜት የመወሰን እና ከአድልዎ፣ ከግዳጅ ነፃ በሆነ መንፈስ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ እና ዘዴዎቹን የማወቅ መብት አላቸው፡፡ ነገር ግን የግዳጅ ወሲብ የሚፈፀምበት የጠለፋ ጋብቻን የመሳሰሉ ባህላዊ ልማዶች የዚህን መብት ትግበራ ገድበዋል፡፡ በ2008 ዓ.ም. የተካሄደው የሥነ ሕዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናት እንዳመለከተው ከሆነ የእናቶች ሞት መጠን ከ100,000 ወላዶች ወደ 412 (ከ420) ዝቅ ብሏል፡፡ ከ1992 እስከ 2004 ባለው ጊዜ የእናቶች ሞት ላይ ዳሰሳ ያደረገ አንድ ጽሑፍ እንዳመለከተው የምጥ መራዘም እና ተከትሎት የሚመጣ በተፈጥሮ መንገድ ለመውለድ ያለመቻል ሁኔታ፤ የማህፀን መቀደድ፤ በወሊድ ሠዐት የሚከሰት ከፍተኛ የደም መፍሰስ፤ ከዕርግዝና ጋር ተያይዞ የሚከሰት የደም ግፊት እና በሰዉነት ውስጥ የሚሠራጭ ኢንፌክሽን አራቱ ዋነኛ የእናቶች ሞት መንስዔዎች እንደሆኑ ጠቅሷል፡፡ በ2008 በተካሄደ የሥነ ሕዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናት መሠረት ዘመናዊ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ 35 በመቶ በሚሆኑ ያገቡ ሴቶች የሚዘወተር ሲሆን፤ ስርጭቱ ባላገቡ ሴቶች 55 በመቶ ደርሷል፡፡ ካለፉት የዳሰሳ ጥናቶች ጋር ሲነጻጸር ያገቡ ሴቶች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚነት ጭማሪ አሳይቷል፡፡ የዳሰሳ ጥናቱ በሰለጠነ ባለሙያ የታገዘ የወሊድ መጠን የ28 በመቶ ጭማሪ ሲያሳይ፤ በጤና ተቋማት የሚደረግ ወሊድ በ26 በመቶ ጨምሯል፡፡ ጽንስ ማቋረጥ ሕገ-ወጥ ድርጊት ቢሆንም፤ በርካታ ያላካተታቸው ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ ሕገ-ወጥና ጥንቃቄ በጎደለው አኳኋን ጽንስ በማስወረድ ዙሪያ ከተደረገው የሕግ ለውጥ ወዲህ፤ለበርካታ እናቶች ሞት መንስኤ ይሆን የነበረው ይህ ድርጊት መቀነሱ ተስተውሏል፡፡ በሁሉም የመንግሥት የጤና ተቋማት የእናቶችና የህፃናት ጤና አገልግሎቶች በነፃ የሚሰጡ ቢሆንም፤ ከከተማ ራቅ ብለው ባሉ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሚያጋጥመው የመጓጓዣ ችግር የተነሣ አሁንም ጥራት ያለው አገልግሎት ተደራሽነት ሊረጋገጥ አልቻለም፡፡

**መድልዎ፡-** በሴቶች ላይ የሚፈፀም መድልዎ የነበረ ችግር ሲሆን፤ በተለይም በግምት 80 ከመቶ ያህል የአገሪቱ ሕዝብ በሚኖርበት የገጠሩ ክፍል የጎላ ነበር። ሕጉም ቢሆን መድልዎን የሚያንፀባረቁ ደንቦችን ይዟል፡፡ ባልን ሕጋዊ የቤተሰብ ኃላፊ አድርጎ እውቅና መስጠቱ፣ እንዲሁም ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በላይ ለሆኑ ሕፃናት ብቸኛ ሞግዚት ወይም አሳዳጊ አድርጎ መሰየሙ ለአብነት ይጠቀሳሉ። ፍርድ ቤቶች የቤት ውስጥ ጥቃትን ለፍች በቂ ምክንያት አድርገው አይወስዱትም። የቱንም ያህል ረጅም ዓመታት ያስቆጠረ ትዳር ቢሆን፣ ብዙ ልጆች ቢወልዱም፣ በርካታ ንብረቶችን በጋራ ቢያፈሩም፣ ትዳር የሚፈርስበት ሁኔታ ከተፈጠረ ሕጉ ለሴቶች ያስቀመጠው ለሦስት ወራት ብቻ የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት መብትን ነው፡፡ በልማዳዊ ሕግ ለተፈፀመ ጋብቻ የሚሰጠው የሕግ ዕውቅና ውሱን ነበር፡፡ ልማዳዊ ሕግ ባል ለቤተሰቡ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግ የሚያስገድደው የሕግ አግባብ ስለሌለው ሴቶችና ሕፃናት

አንዳንዴ ችግር ላይ የወደቁበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ ባህላዊ ሕጎችን መተግበር እንደቀጠሉ ናቸው።

ሕገ-መንግሥቱ መንግሥትና ሕዝብ ብቸኛ የመሬትና የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤቶች እንደሆኑ ይደነግጋል። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በውርስ ሊያስተላልፉ የሚችሉት በመሬት የመጠቀም መብት አላቸው። የመሬት ሕግ ከክልል ክልል ይለያያል። ሁሉም የፌደራል እና የክልል የመሬት ሕጎች ሴቶች የመንግሥት መሬት ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎችን አመቻችተዋል። የውርስ ሕጎችም ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች በትዳር አብረው ሲኖሩ ያፈሩትን የጋራ ንብረት መውረስ እንደሚችሉ ደንግገዋል።

በከተሞች አካባቢ ሴቶች ሥራ የማግኘት ዕድላቸው ከወንዶች አንፃር አናሳ ሲሆን፣ ባሉት የሥራ ዘርፎችም ለተመሳሳይ ሥራዎች ተመሳሳይ ክፍያ አይሰጣቸውም ነበር። በተጨማሪም ሴቶች ባላቸው ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ እና ሥልጠና፤ እንዲሁም ባለው ልማዳዊ አመለካከት የተነሳ በጥሩ ደመወዝ እንዳይቀጠሩ፣ ብድር እንዳያገኙና የራሳቸውን የንግድ ሥራ እንዳይሰሩ ወይም እንዳይመሩ ተገድበዋል።

## ሕፃናት

**<u>የልደት ምዝገባ፡-</u>** ሕጻናት ዜግነታቸውን የሚያገኙት ከወላጆቻቸው ነው። ሁሉም ሕፃናት ሲወለዱ መመዝገብ እንዳለባቸው ሕጉ ይደነግጋል። በሆስፒታል የተወለዱ ሕፃናት የተመዘገቡ ሲሆን፤ ከሆስፒታል ውጪ የተወለዱ አብዛኞቹ ሕፃናት ግን አልተመዘገቡም። ብዙዎቹ ሕፃናት በተለይ በገጠር አካባቢ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ይወለዳሉ፡፡ በዓመቱ መንግሥት የልደት ምዝገባ የማስፋፋት ዘመቻ አካሂዷል፡፡

**<u>ትምህርት፡-</u>** ህጉ ትምህርትን አስገዳጅ አላደረገም፡፡ በፖሊሲ ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዕድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ሕፃናት በነፃ እንደሚሰጥ ተደንግጓል። ሆኖም ግን የአገሪቱን ወጣቶች ተቀብለው የሚያስተምሩ በቂ ትምህርት ቤቶች በተለይ በገጠር አካባቢዎች አልነበሩም። ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ብዙ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዳይልኩ መሰናክል ሆኗል። ትምህርት ለመከታተል የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከሰለጠኑ መምህራን ቁጥር በላይ በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል። የመጀመሪያ ደረጃ  የትምህርት ቅበላ መጠን የወንዶች 90 በመቶ ሲሆን ሴቶች 84 በመቶ ነበር፡፡

**<u>በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ጥቃት፡-</u>** በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ጥቃት በስፋት ተስተውሏል፡፡ ግግ ማስቧጠጥ፣ እንጥል መቁረጥ እና የወተት ጥርስ መንቀል በስፋት ከሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የአፍሪካ ሕፃናት ፖሊሲ መድረክ በ2005 ዓ.ም. ያካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው፤ በሕፃናት ላይ ወሲባዊ ጥቃቶችን የሚፈጽሙ ጥፋተኞች ላይ በመንግሥት የሚጣሉ ቅጣቶች ጨምረዋል። ለሕፃናት ምቹ የሆኑ በተለይም በሕፃናት እና በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የሚዳኙ ችሎቶች ተቋቁመዋል። በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሴቶች እና ሕጻናት ጉዳዮች ኮሚሽነር ጽ/ቤት አለው፡፡

**<u>ያለዕድሜና የግዳጅ ጋብቻ፡-</u>** ሕጋዊ ጋብቻ ለመፈፀም ወንዶችና ሴቶች ዕድሜያቸው 18 ዓመት መድረስ እንደሚገባው ሕጉ ይደነግጋል፣ ይሁን እንጂ ህጉ ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ አልተደረገም። አንዳንድ በገጠር የሚገኙ ቤተሰቦች ስለ ህጉ ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡ በበርካታ ክልሎች በዕድሜ የገፉ ወንዶች ወጣት ሴቶችን የማግባት ሁኔታ ያለ ሲሆን፤በዚህ ልማዳዊ ድርጊት ላይም ከፍተኛ ተቃውሞና ትችት እንደቀጠለ ነው። መንግሥት ያለዕድሜ ጋብቻ ችግርን ለመቅረፍ ጥፋተኞችን ከመቅጣት ይልቅ በማስተማርና በሽምግልና ነገሮችን በመፍታት ላይ አተኩሯል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የህጻናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) በ2007 ዓ.ም. ባቀረበው ሪፖርት፤ከ20-24 የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ሴቶች16 በመቶ የሚሆኑት ዕድሜአቸው 15 ዓመት ሳይሞሉ የተዳሩ ሲሆን፤ 41 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ዕድሜአቸው 18 ዓመት ሳይሞላ ባል ያገቡ ነበሩ፡፡ በ2003ቱ የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት መሰረት ዕድሜያቸው ከ 20-49 የሆኑ ሴቶች አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጽሙበት ዕድሜ 17.1 ዓመት ነበር፡፡ ይህ አሃዝ በ1997 ዓ.ም. በተደረገው ጥናት 16.5 ዓመት ነበር፡፡

ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ሕፃናት በተለይ በአማራና ትግራይ ክልሎች በሰባት ዓመታቸው ሳይቀር ጋብቻ ፈጽመዋል። በሕፃናት ጋብቻ አማራ ክልል ቀዳሚ ሲሆን ፤ 45 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች 18ኛ ዓመታቸውን ሳይደፍኑ ጋብቻ ፈፅመዋል፡፡ በክልሉ በተደረገ የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት በ1997 ዓ.ም 14.7 ዓመት የነበረው አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ በ 2003 ወደ 15.1 ዓመት ከፍ ብሏል፡፡ የአማራ እና በመጠኑም ቢሆን የትግራይ ክልላዊ መንግሥታት ካለዕድሜ ጋብቻ ጋር ተያይዘው በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ልጃገረዶችን፣ ወጣት ሴቶችን፣ ወላጆችን፣ የማኅበረሰብ መሪዎችን፣ እንዲሁም የጤና ባለሙያዎችን ለማስተማር ፕሮግራም ዘርግተዋል።

**የሴት ልጅ ግርዛት/ብልት ትልተላ፡-** ከላይ በሴቶች ጉዳይ ላይ ያተኮረውን ክፍል ይመልከቱ፡፡

**<u>የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ፡-</u>** በፈቃደኝነት ወሲባዊ ግንኙነት ለመፈፀም ዝቅተኛው የዕድሜ ገደብ 18 ዓመት ቢሆንም፣ ባለስልጣናት ሕጉን ተፈጻሚ አላደረጉም። ለአቅመ አዳም/ሄዋን ካልደረሰ/ች ህፃን ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ከ3 እስከ 15 ዓመት የሚደርስ ቅጣት እንደሚያስከትል በሕግ ተደንግጓል። ለአቅመ አዳም/ሔዋን ባልደረሱ ሕፃናት ላይ አስጸያፊ ወሲባዊ ድርጊት ሲፈፀም የሚያሳዩ ምስሎችን ያሰራጨ ሰው በአንድ ዓመት እስራትና በ10,000 ብር (444 የአሜሪካን ዶላር) የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል። በተጨማሪም ሕጉ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ሕፃናትን ለወሲብ ድርጊት ማሰማራትና የወሲብ ንግድ እንዲጀምሩ መገፋፋትን ይከለክላል። ነገር ግን የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ፣ በተለይ በከተሞች አካባቢ ይዘወተራል።ዕድሜያቸው 11 ዓመት የሆኑ ወጣት ሴቶች ለወሲብ ንግድ እንዲሰማሩ መመልመላቸው ተነግሯል። ደንበኞች ከእነዚህ ወጣት ሴቶች ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም የሚፈልጉት ወጣት ሴቶቹ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ነው። ወጣት ሴቶችን ከገጠር ወደ ከተማ በማስኮብለል በሆቴሎች፣ ቡና ቤቶች፣ በመዝናኛ ስፍራዎች እና ገጠር በሚገኙ የከባድ መኪና ማቆሚያ ጣቢያዎች በወሲብ ንግድ ተበዝብዘዋል። አንዳንድ ወጣት ሴቶች በራሳቸው ቤተሰቦች ተገፋፍተው ወደ ወሲብ ንግድ እንደገቡ ሪፖርቶች አመልክተዋል።

**<u>ሕፃናትን ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሕጻናት መግደል፡-</u>** በዘልማድናባዕድ አምልኮ ምክንያት ሕፃናትን፤ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ህፃናትን ጨምሮ መግደል በደቡብ ኦሞ  አካባቢ ባሉ ጎሳዎች መተግበሩ ቀጥሏል። የአካባቢ መስተዳድሮች ማኅበረሰቡን በማስተማር ድርጊቱን ለማስቀም ጥረት አድርገዋል።

**<u>የተፈናቀሉ ሕፃናት፡-</u>** የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የ2002 ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ በግምት 150,000 ሕፃናት በጎዳና ላይ የሚኖሩ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 60,000 የሚሆኑት በዋና ከተማዋ ይገኛሉ። እንደ ሚኒስቴሩ ሪፖርት ከሆነ በወላጆች ህመም እንዲሁም በቤተሰብ የገቢ አነስተኛነት ምክንያት ቤተሰቦች ልጆቻቸውን መርዳት አለመቻላቸው ችግሩን አባብሶታል። በ2006 ዓ.ም. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያካሄደው ሌላ ጥናት እንዳመለከተው ፈጣን የከተሞች መስፋፋት፣ ሕገ-ወጥ ደላሎች፣ በከተሞች የተሻለ ሕይወት አለ የሚል አስተሳሰብ እና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት ችግሩን አባብሰውታል፡፡ እነዚህ ሕፃናት በቡድን ሆነው ይለምናሉ፤ ወይም መደበኛ ባልሆነ ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በርካታ ረዳት አልባ ሕፃናት ከኤርትራ ወደ ሀገሪቱ መግባታቸውን ቀጥለዋል፡፡ (ክፍል 2፤መ ይመልከቱ)

**<u>በተቋማት የሚረዱ ሕፃናት፡-</u>** በተባበሩት መንግሥታ የሕፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) የ2004 ሪፖርት መሠረት በሀገሪቱ ውስጥ በግምት 4.5 ሚሊዮን ወላጅ አልባ ሕፃናት ይገኛሉ። አብዛኛዎቹ ከዘመዶቻቸው ጋር ይኖሩ ነበር። በመንግሥት እና በግል የሚተዳደሩ የወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የተጨናነቁ እና ንጽህና የጎደላቸው ነበሩ። ከፍተኛ ከሆነ የገንዘብ እጥረት የተነሳ ሆስፒታሎችና የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለደጋፊ አልባ ሕፃናት ትኩረት አልሰጡም። በተቋማት የሚረዱ ሕፃናት በቂ የጤና ክብካቤ አላገኙም።

**ዓለም አቀፍ የሕፃናት ጠለፋ፡-** አገሪቱ የ1972ቱ ዓለም አቀፍ የሕፃናት ጠለፋ የሲቪል ገጽታዎች የሔግ ስምምነት አባል አይደለችም። ኢትዮጵያን በሚመለከት ያለውን ሙሉ መረጃ ለማግኘት ቀጥሎ የተመለከተውን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የድረገፅ አድራሻ ይመልከቱ፡- travel.state.gov/content/childabduction/en/legal/compliance.html.

ሚያዝያ 7፤ ከደቡብ ሱዳን የመጡ የሙርሌ ጎሳ አባላት በጋምቤላ ክልል ጥቃት በማድረስ ከ100 በላይ ሕፃናትን ጠልፈው ወስደዋል (ክፍል 6፤ ሌላ ማኅበራዊ ነውጥ ወይም መድልዎ ይመልከቱ) ፡፡

**ፀረ-ሴማዊነት**

የአይሁድ ማኅበረሰብ አባላት ቁጥር በግምት 2000 የነበረ ሲሆን ፀረ-ሴማዊ የሆኑ ድርጊቶችን የሚመለከቱ ሪፖርቶች አልነበሩም።

**ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር**

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሚያወጣውን ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሪፖርት በwww.state.gov/j/tip/rls/tiprpt/ ድረ-ገጽ ላይ ይመልከቱ።

**አካል ጉዳተኞች**

ሕገ መንግሥቱ ለአካል ጉዳተኞች እኩል መብት አይሰጥም። የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞች በሥራ ቅጥር ወቅትና ህንፃዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ መድልዎ እንዳይደረግባቸው ሕጉ ይከለክላል። አእምሮአዊና የሳንሱር ጉዳተኞችን ግን በግልፅ አይጠቅስም፡፡ መስማት ለተሳናቸው ሰዎች መኪና ማሽከርከር በሕግ የተከለከለ ነው፡፡ በቅጥር ወቅት አካል ጉዳትን መሠረት ያደረገ መድልዎ እንዳይፈጸም ሕጉ ይከለክላል። በተጨማሪም ቀጣሪ መሥሪያ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሥራ ወይም የሥልጠና ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚገባቸው ይደነግጋል። በተለይ በሴት የአካል ጉዳተኞች ላይ ያለውን ተደራራቢ ጫናም ሕጉ ከግምት አስገብቷል። መንግሥት ሕጉን ለማስፈጸም የወሰዳቸው እርምጃዎች ውስን ነበሩ። ለምሳሌ ያህል መስማት ለተሳናቸው የመንግሥት ሠራተኞች አስተርጓሚዎችን መመደብ (ክፍል 7 "መ" ን ይመልከቱ)። የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን ይህንን የአካል ጉዳተኞችን የቅጥር መብቶች በማስከበር ላይ ያተኮሩ መብቶችን የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ምንም እንኳ የህንፃዎችን የተደራሽነት ደረጃ የተመለከቱ ዝርዝር ደንቦች ባይወጡም፣ የሚገነቡ ህንፃዎች እና የመፀዳጃ ክፍሎች ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ በሆነ መልኩ እንዲገነቡ ሕጉ ደንግጓል። ይሁን እንጂ ህንፃዎችና የመጸዳጃ ክፍሎች በአብዛኛው ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አልነበሩም። የቤት አከራዮች አካል ጉዳተኞች የመጀመሪያ ወለል ላይ እንዲከራዩ ማስመረጥ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ተግባራዊ ሆኗል።

በትምህርትና በሥራ ቅጥር ሴት የአካል ጉዳተኞች ከወንዶቹ የበለጠ ተጎጂዎች ነበሩ። “ፖፑሌሽን ካውንስል ያንግ አዳልትስ ሰርቬይ” (Population Council Young Adult Survey) በ2002 በወጣቶች ላይ ባደረገው ጥናት የወጣት አካል ጉዳተኞች የትምህርት ተሳትፎ የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣቶች ዝቅተኛ እንደነበር አመልክቷል፡፡ በጥናቱ መሠረት የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች የትምህርት ተሳታትፎ ከወንድ አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ያነሰ ነበር። የአካል ጉዳት ካለባቸው ወጣት ሴቶች መካከል 23 በመቶ የሚሆኑት ትምርት ቤት የገቡ ሲሆን የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣት ሴቶች መካከል 48 በመቶ እንዲሁም ከወንዶች 55 በመቶ ትምህርት ቤት ገብተዋል፡፡ በጥቅል ሲታይ ጥናቱ ካካተታቸው የአካል ጉዳተኛ ወጣቶች መካከል 48 በመቶ ያህሉ በአካል ጉዳት ሳቢያ ትምህርት ቤት መግባት እንዳልቻሉ ተናግረዋል፡፡ የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣት ሴቶች ይበልጥ ለአካላዊና ወሲባዊ ጥቃት ተጋላጭ ናቸው፡፡ ወሲብ ከፈጸሙ የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች መካከል 33 በመቶ ያህሉ የግዳጅ ወሲብ እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል፡፡ በዚሁ ጥናት መሰረት ከወንድ የአካል ጉዳተኞች መካከል 6 በመቶ ያህሉ ጥናቱ ከመደረጉ ሶስት ወራት በፊት ባለው ጊዜ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ በአንጻሩ ጥናቱ ካካተታቸው የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣት ወንዶች መካከል 2 በመቶ ያህሉ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡

መስማትና ማየት ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች የተቋቋሙ በርካታ ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም የአእምሮ ዕድገት ውሱንነት ችግር ላለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች የሥልጠና ማዕከላት ተዘጋጅተዋል። ከዘጠኙ የክልል መንግሥታት በአምስቱ ሰው ሰራሽ የአካል ጉዳተኞች መርጃ መሳሪያዎች ማምረቻ ማዕከላት ነበሩ።

የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተያይዘው በሚነሱ ችግሮች ላይ ያተኮሩ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ እንደሌሎች ሲቪክ ማህበራት ሁሉ ብሔራዊ ማየት የተሳናቸው ማህበር፣ ብሔራዊ መስማት የተሳናቸው ማኅበር እና ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማኅበር በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ ምክንያት አሉታዊ ተጽዕኖ ማድረሱን ቀጥሏል። ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና አንዳንድ ሀገር በቀል ሲቪክ ማኅበራት ከአካል ጉዳተኞች ጋር በተያያዘ፤በተለይም ተደራሽነትንና የሙያ ሥልጠናን በሚመለከት ከፍተኛ እንቅስቃሴዎችን አድርገዋል፡፡

ምንም እንኳን የአካል ጉዳተኞች በምርጫና ሌሎች የዜግነት ጉዳዮች እንዳይሳተፉ በሕግ ባይከለከልም፤የተደራሽነት አለመኖር የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ በእጅጉ ሊገድበው ይችላል፡፡ በግንቦት 2007 ብሔራዊ ምርጫ በተካሄደበት ወቅት የአፍሪካ ሕብረት ታዛቢዎች እርዳታ ያስፈለጋቸው መራጮች በሙሉ እነሱ በሚመርጡት ሰው አልያም በምርጫ ጣቢያው ሠራተኞች አስፈላጊው ሁሉ ትብብር እንደተደረገላቸው አመልክተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ የነበሩ ሲሆን፤አዛውንቶች፣ነፍሰጡሮች፣እመጫቶችና አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ እየተሰጣቸው ተስተናግደዋል፡፡

**ብሔር/ዘር/ እናናሳ ጎሳዎች**

በአገሪቱ ከ80 በላይ ብሔሮች/ብሔረሰቦች አሉ። ከጠቅላላው ህዝብ ወደ 35 በመቶ የሚሆነውና ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው የኦሮሞ ብሔረሰብ ነው። የፌዴራል ሥርዓቱ ድንበሮችን የዋና ዋና ብሔረሰቦችን አሰፋፈር መሠረት በማድረግ የለየ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዋናነት ብሔረሰብን መሠረት ያደረጉ ነበሩ። ገዢው ፓርቲና አንድ ዋና ተቃዋሚ ፓርቲ ብሔርን መሠረት ያደረጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምረት ናቸው፡፡

በታህሳስ 3 2007 ዓ.ም. ጥቂት የኦሮሞ ተቃዋሚዎች በኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በአመያ የአማራ ብሔር ተወላጆች መኖሪያ ቤቶች እና ንብረቶችን እንዳቃጠሉ  የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) ሪፖርት አድርጓል፡፡ እንደ ሰመጉ ሪፖርት ጥቃቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችን ከቀያቸው

አፈናቅሏል፤ ከ800 በላይ መኖሪያ ቤቶችን አውድሟል፡፡ በርካታ የአማራ ብሔር አርሶ አደሮች 96 የኦሮሞ አርሶ አደሮችን መኖሪያ በማቃጠል የበቀል ጥቃት ፈጽመዋል፡፡ ሁለቱ ማኅበረሰቦች የጋራ ስብሰባ በማድረግ በሁለቱም በኩል የተፈፀሙ ጥቃቶቹን በማውገዝ፤ በጥቃቱ የወደሙ መኖሪያ ቤቶችን መልሶ የመገንባት ሥራ በጋራ ሰርተዋል፡፡

## ጾታዊ ማንነትን እና ወሲባዊ ዝንባሌን መሠረት ያደረጉ የበደል ድርጊቶች፣ መድልዎ፣ እና ጥቃቶች

በአገሪቱ ሕግ መሠረት በፈቃደኝነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ጾታ ወሲባዊ ግንኙነት ሕገ-ወጥና ከሦስት እስከ 15 ዓመት እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው። የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ባላቸው ግለሰቦች ላይ መድልዎ እንዳይፈጸም የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ ባላቸው ግለሰቦች ላይ ጥቃቶች መፈፀማቸውን የሚገልጹ አንዳንድ ሪፖርቶች ነበሩ። ሆኖም እነዚህን ጥቃቶች ከፍርሃት የተነሳ ወይም በቀል፣ መድልዎና መገለል ይደርስብናል በሚል ስጋት በተጎጂዎች የቀረቡ ሪፖርቶች ውስን ነበሩ። የጥላቻ ወንጀልን የሚመለከቱ ሕግጋት ወይም የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ባላቸው ግለሰቦች ላይ ጥቃቶች ሲፈጸሙ አስፈላጊውን ዕርዳታ ለማድረግ የሚያስችል በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስተ ያለ አሠራር የለም፡፡ በተመሳሳይ ፆታ መካከል የሚደረግ የወሲብ ግንኙነት በሀገሪቱ ህገ-ወጥ በመሆኑና ሊደርስባቸው የሚችለውን የከፋ ማሕበራዊ መገለል በማሰብ መሰል ወሲባዊ ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች ራሳቸውን ይፋ አያደርጉም። የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት የሚፈጽሙ ማኅበረሰብ አባላት መብት ተሟጋቾች ክትትል እንደሚደረግባቸው እና አልፎ አልፎም ለደህንነታቸው እንደሚሰጉ ተናግረዋል፡፡ ጾታዊ ግንኙነት ከተመሳሳይ ጾታ ጋር ፈጽመዋል ተብለው ለእስር ስለተዳረጉ ሰዎች የሚወጡ አዳዲስ መረጃዎች የሉም፡፡

አዲስ አበባ የሚገኘው የኤድስ መረጃ ማዕከል የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ያላቸው ሴቶችና በርካታ ወንዶች ማንነታቸውን በመግለጽ የሚደርስባቸውን መገለል ለመሸሽ እንዴት ጾታዊ ዝንባሌያቸውን መቀየር እንደሚችሉ ምክር በመሻት ስልክ ይደወሉ እንደነበር ሪፖርት አድርጓል። በርካታ የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ያላቸው ወንዶች ስጋት፣ ግራ መጋባት፣ የማንነት ቀውስ፣ ድብርት፣ ራስን ማግለል፣ የሃይማኖት ግጭት እና ራስን ለማጥፋት የመሞከር ስሜት እንደተሰማቸው ተናግረዋል።

## ኤች.አይ.ቪ ኤድስ እና ማኅበራዊ መድሎ

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለ ወይም በበሽታው የተጎዱ ዜጎች በትምህርት፣ በሥራ እንዲሁም በማህበራዊ ኑሮ የሚደርስባቸው መድልዎ እና መገለል ቀጥሏል። እነዚህ ግለሰቦች አገልግሎት ለማግኘት መቸገራቸውን ተናግረዋል፡፡ የችግሩን ስፋት የሚያሳይ ስታቲስቲካዊ መረጃ አልተገኘም።

## ሌሎች ማኅበራዊ ጥቃቶች ወይም መድሎዎች

የተቃውሞ ሰልፎች በተካሄዱበት ጊዜያት ጋመቤላ ክልልን ጨምሮ ጥቃቶች ተሰንዝረዋል፡፡ ሚያዝያ 7፤ ከደቡብ ሱዳን ሰርገው የገቡ የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች በጋምቤላ ክልል ኑዌር ዞን ሦስት ወረዳዎች ባደረሱት ጥቃት ከ200 በላይ ሴቶችና ሕጻናትን ገድለዋል፡፡ ጥቃት ፈጻሚዎቹ በተጨማሪም ከ100 በላይ ሕጻናትን ጠልፈው ወስደዋል፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ከብቶችን ዘርፈዋል፡፡ በሙርሌ ታጣቂዎች የተሰነዘረው ጥቃት ወትሮውንም በኑዌር እና አኙዋክ ጎሳዎች መካከል ጥር 11 በተቀሰቀሰ የጎሳ ግጭት ውጥረት ውስጥ ለነበረው አካባቢ ተጨማሪ አለመረጋጋትን ፈጥሯል፡፡

ሚያዝያ 13፤ በጋምቤላ ክልል በሚገኘው በጃዊ የስደተኞች መጠለያ የተጠለሉ የደቡብ ሱዳን ስደተኞች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ በአንድ ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት የተቀጠሩ 10 ኢትዮጵያውያንን ገድለዋል፡፡ ግጭቱ የተቀሰቀሰው አንድ የድርጅቱ ተሽከርካሪ ሁለት የስደተኞች ህጻናትን

ገጭቶ ከገደለ በኋላ ነበር፡፡ ባለሥልጣናት በግድያው የተጠረጠሩ 53 ስደተኞችን ያሰሩ ሲሆን፤ ከእነኚህም ውስጥ በ23ቱ ላይ ነሐሴ 9 የወንጀል ክስ መስርተዋል፡፡ ስደኞች እና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር እንዳስታወቀው፤ መንግሥት ለተከሳሽ ስደተኞች ሁለት የተከላካይ ጠበቆች አቁሟል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን የደህንነት ክፍል እና ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማኅበር በእስር የሚገኙ ስደተኞችን የጎበኙ ሲሆን የፍርድ ሂደቱንም ተከታትለዋል፡፡

ሰኔ 22 የአድስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪዎችን በኃይል የማንሳት እንቅስቃሴ በጀመረበት ወቅት፤ በነፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የሐና ማሪያም፤ ፉሪ እና ማንጎ ጨፌ አካባቢ ነዋሪዎች ከፖሊስ ጋር ተጋጭተው ሁለት የፖሊስ መኮንኖችን ጨምሮ አንድ ባለሥልጣን ገድለዋል፡፡ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን እና የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስቴር ግድያው መፈጸሙን አረጋግጠዋል፡፡

## ክፍል 7. የሠራተኛ መብቶች

### ሀ. የመደራጀት ነፃነት እና በኅብረት የመደራደር መብት

ከመንግሥት ሠራተኞች በስተቀር የሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞች በሠራተኛ ማህበራት እንዲደራጁ፣በማህበራት እንዲታቀፉ፣ህጋዊ የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ፣ በኅብረት እንዲደራደሩ ሕገ-መንግስቱም ሆነ ሕጉ ይፈቅዳል። እነዚህ መብቶች አገሪቱ ባወጣቻቸው ሌሎች ሕግጋት ምክንያት ተግባራዊ እንዳይሆኑ ተገድበዋል፡፡ ሕጉ በተለይ በሥራ አስኪያጅ ደረጃ ያሉ ተቀጣሪዎች፣ መምህራን፣ የጤና ክብካቤ ሠራተኞች፣ ዳኞች፣ ዐቃቤያን ህጎች፣ የደህንነት አገልግሎት ሠራተኞችን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበር እንዲያቋቁሙ አይፈቅድላቸውም፡፡ የቤት ሠራተኞች፣ ጊዜያዊ ተቀጣሪዎች፣ እና የትርፍ ጊዜ የግብርና ሠራተኞችም እንዲሁ ማህበር እንዲያቋቁሙ ሕጉ አይፈቅድላቸውም፡፡

የሠራተኛ ማህበር ለመመሥረት ቢያንስ አሥር አባላት ያስፈልጋሉ። ምንም እንኳ ሁሉም ማህበራት የመመዝገበ መብት እንዳላቸው ሕጉ ቢደነግግም፤ መንግሥት ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች ያላሟሉ ማህበራትን ላይመዘግብ ይችላል። ሠራተኞች በቅጥራቸው ከአንድ በላይ የሠራተኛ ማኅበር አባል እንዲሆኑ አይፈቀድም፡፡ አንድ የሠራተኛ ማኅበር ግልጽ በሆነ ሁኔታ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማራመድ እንደሌለበት ህጉ ይደነግጋል። የአስተዳደር ኃላፊዎች አንድ የሠራተኛ ማህበር ፖለቲካን በመሰሉ የተከለከሉ ተግባራት መሳተፉን ጠቅሰው ምዝገባው እንዲሰረዝ ለፍርድ ቤት እንዲያመለክቱ ሕጉ ይፈቅዳል፡፡

ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሠራተኞችን በነጻነት የመደራጀት መብት የሚገድቡ ወይም የመገደብ አቅም ያላቸው ሌሎች ሕግጋትና ደንቦች፤ የበጎ አድራጎትና ሲቪክ ማኅበራት አዋጅ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001 (የበጎ አድራጎትና ሲቪክ ማኅበራት አዋጅን ለማጠናከር የወጣ) እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 652/2001 (የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጅ) ናቸው፡፡ በዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት የ"ኮንቬንሽኖች" እና ምክረ-ሃሳቦች ትግበራ ኮሚቴ የበጎ አድራጎት እና ማህበራት አዋጁ መንግሥት በሠራተኞች የመደራጀት፣ የመመዝገብ፣ የውስጥ አስተዳደርና ማኅበርን የማፍረስ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ሥልጣን ይሰጣል ሲል ገልጿል፡፡

በኅብረት የመደራደር መብት እንዲከበር ሕጉ ጥበቃ ቢያድርግም፤ ይህ መብት በከፍተኛ ደረጃ ተገድቧል። የኅብረት ስምምነትን ለማሻሻል ወይም በአዲስ ለመተካት የሚደረግ ድርድር ስምምነቱ ከማብቃቱ ከ3 ወራት በፊት ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ህጉ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ የመንግሥት ትምህርት ቤት መምህራንን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞች የሙያ ማኅበራትን

መመሥረት፣ እንዲሁም አባል መሆን ይችላሉ፤ ነገር ግን ለተሻለ ክፍያና የሥራ ሁኔታ መደራደር አይችሉም፡፡ በተጨማሪም የመንግሥት ዘርፍ የአሠሪና ሠራተኛ ግጭት አፈታት በግሉ ዘርፍ ካለው የበለጠ ገዳቢ ነው፡፡ ሕጉ በሠራተኞችም ሆነ በአሠሪዎች የውስጥ አደረጃጀት፣ አሠራርና አስተዳደር ጉዳዮች ጣልቃገብነት በቂ ከለላ አያደርግም፡፡

ሠራተኞች መብታቸውን ለማስጠበቅ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ እንደሚችሉ በሕገ መንግሥቱና በሕግ የተደነገገ ቢሆንም፤ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ውስብስብና ጊዜ ወሳጅ ሥነ-ሥርዓቶች አሉ። ተበዳይ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በፊት ከቀጣሪው መሥሪያ ቤት ጋር በድርድር ጉዳዩን በእርቅ እንዲፈቱ ቢደነገግም፤ ሂደቱ ጊዜ ወሳጅ ነው። ሆኖም እነዚህ ድንጋጌዎች ቀጣሪው ድርጅት ሠራተኛውን ከሥራው እንዲያግድ መብት ይሰጡታል፡፡ የሥራ ማቆም አድማ ለማድረግ የሠራተኛውን 2/3ኛ ድጋፍ ማግኘት ያስፈልጋል። ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ወይም የሠራተኛ ማህበርን ለሚመለከት ቦርድ ካልቀረበ ሠራተኛው ከላይ የተጠቀሱትን አማራጮች ሳይከተል የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ መብት አለው። ይህ የሚሆነው ግን ቢያንስ ከአስር ቀናት በፊት ለሌላኛው ወገንና ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲያሳውቅ እንዲሁም ጉዳዩን በድርድር ለመፍታት ጥረት ሲያደርግ ነው።

በአየር ትራንስፖርት፣ በከተማ አውቶቡስ፣ በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ በነዳጅ ማደያ፣ በሆስፒታልና መድሃኒት ቤቶች፣ በእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን እና በከተማ ጽዳት በመሳሰሉት እጅግ ወሳኝ ማህበራዊ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ እንደማይችሉ በሕግ ተደንግጓል። ነገር ግን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች በዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት ወሳኝ ማህበራዊ አገልግሎቶች  ትርጓሜ ብሎ ካሰቀመጣቸው መዘርዝሮች ይበዛሉ፡፡ አድማ ባደረጉ ሠራተኞች ላይ የሚደረግ የበቀል እርምጃን ሕጉ ይከለክላል። ሆኖም ግን በህገወጥ የሥራ ማቆም አድማ ላይ የሚሳተፉ ማኅበራትና ሠራተኞች በፍትሐ ብሔር ወይም በወንጀለኛ ህግ ሊጠየቁ እንደሚችሉ ሕጉ ይደነግጋል፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ካስቀመጣቸው ሌሎች የቅጣት እርምጃዎች ባሻገር፤ ይህንን ድንጋጌ የጣሰ የሠራተኛ ማኅበር በ1,200፤ ግለሰብ ከሆነ ደግሞ 300 ብር የገንዘብ ቅጣት እንዲጣልባቸው ሕጉ ያዛል፡፡ እጅግ ወሳኝ ማኅበራዊ አገልግሎት በሚሰጡ ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ ያስተባበሩ የሠራተኛ ማኅበራት እንዲፈርሱ ሊወሰን ይችላል፡፡

የቤት ሠራተኞችን ጨምሮ መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት በማኅበር ሊደራጁ አይችሉም፡፡ መንግሥት ባጋጠመው የሰው ኃይል እጥረት ሳቢያ ሕግጋትን በሚፈለገው ደረጃ ተፈጻሚ ማድረግ አልቻለም፡፡ የክስ ሂደቶችም መዘግየትና ይግባኝ የበዛባቸው ነበሩ፡፡

የመደራጀትና በኅብረት የመደራደር መብቶች የተከበሩ ቢሆንም ያልተፈቱ አንዳንድ ህጋዊ ችግሮች አሉ፡፡ መንግሥት የታገዱ ማኅበራትና ስብሰባዎች ቀንደኛ ጠንሳሾችን፤ አዘጋጆችን ወይም ትዕዛዝ አስተላላፊዎችን ለመቅጣት የፀረ-ሽብር ህጉን መጠቀሙን የዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት ነቅፏል፡፡ መንግሥት ላለፉት አራት በላይ ዓመታት እንዳደረገው ሁሉ፤ ብሔራዊ የመምህራን ማህበር ያቀረበውን የምዝገባ ጥያቄ ተመሳሳይ ማኅበር መኖሩን እንደምክንያት በማቅረብ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ ከዚህ ሌላ መምህራን ማህበር ያቀረበው የምዝገባ ማመልከቻ የበጎ አድራጎትና ሲቪክ ማሕበራት አዋጅን መሰረት ያላደረገ ነው ሲል ገልጿል፡፡ በ2005 ዓ.ም. የዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት ልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ የሥራ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት መንግሥት ብሔራዊ የመምህራን ማኅበርን በሲቪክ ማኅበራት አዋጅ አማካይነት እንደሚመዘግበው ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የጋራ መግባባት ላይ መድረሳቸውንና በመንግሥት በኩል ቀርጠኝነትና ዝግጁነት መታየቱን ገልጿል፡፡ የዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ቢሮ ያንኑ መልዕክት አጠናክሮ ያስተላለፈ ሲሆን፤ በመንግሥትና በማኅበሩ መካከል ያለው ውዝግብ የስያሜና በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የአባልነት ጉዳይ መሆኑን አመልክቷል፡፡

ምንም እንኳን ዜጎች በኅብረት የመደራደር መብትን በነፃነት እንዲተገብሩ መንግሥት የፈቀደ ቢሆንም፤ የኢንተርፕራይዝ ህብረቶች ተወካዮች የክፍያ ድርድር የሚያደርጉት በተቋም ደረጃ ብቻ ነበር፡፡ በመደበኛ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ያሉ የሠራተኛ ማኅበራት የአሠሪና ሠራተኛ ህግን ሥራ ላይ ለማዋል የተወሰነ ጥረት አድርገዋል፡፡

በማኅበራት መደራጀትን የሚያደናቅፉ የተለያዩ እንቅስሴዎች ቢኖሩም መኖራቸው እምብዛም አልተዘገበም፡፡ መንግሥት በማህበራት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞች መገለል እንዳይደርስባቸው የሚከለክል ቢሆንም፤ ቀጣሪዎች በሠራተኛ ማኅበር ውስጥ በንቃት የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞችን ከሥራ እንደሚያባርሯቸው ማህበራቱ ሪፖርት አድርገዋል። የውጭ ሀገራት ባለሀብት ቀጣሪዎች በአጠቃላይ ሠራተኞች ማኅበር እንዲያቋቁሙ አልፈቀዱም፡፡ አልፎ አልፎም የሠራተኛ ማኅበር መሪዎችን ከመደበኛ ሥራቸው አዛውረዋል፣ ከሥራ አባርረዋል እንዲሁም የማኅበራት መሪዎችን በማስፈራራት ወይም አባላት ከማኅበሩ እንዲወጡ ጫና አድርገዋል የሚሉ ያልተረጋገጡ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡ ሠራተኞች አለአግባብ ከሥራ መባረራቸውን በመግለጽ በፍርድ ቤት የሚመሰረቱት ክሶች ፍርድ ቤቶች ባለባቸው የሥራ ጫና የተነሳ ጉዳዮቻቸው እልባት የሚያገኙት ከዓመታት በኋላ ነበር። በሠራተኛ ማኅበራት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞችን ያላግባብ ከሥራ ያባረሩ ቀጣሪዎች ሠራተኞቹን ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመልሷቸው የታዘዙ ሲሆን፤ በተግባርም ሠራተኞቹን ወደሥራ መልሰዋል። የሥራ ማቆም አድማ አድራጊዎች ላይ የሚወሰደውን የበቀል እርምጃ ህግ የሚከለክል ሲሆን፤ የተዘገበ የበቀል እርምጃም አልነበረም። በሀገሪቱ ካለው ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግር፤ የበቀል እርምጃና በፍርድ ቤት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች የሚወስዱትን ረጅም ጊዜ ከግምት በማስገባት  ሠራተኞች በሥራ ማቆም አድማዎች ወይም በሌሎች የሠራተኛ አድማዎች ላይ ለመሳተፍ እንደሚፈሩ የሠራተኛ ማህበራት ኃላፊዎች ተናግረዋል።

## ለ. የግዳጅ ሥራ ክልከላ

በነሐሴ 2007 የፌዴራሉ መንግሥት በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን በማዘዋወር ወንጀል ተጠያቂ በሚሆኑ ግለሰቦች ላይ በሚጣለው የቅጣት ዓይነትና ደረጃ ላይ አዋጅ አጽድቋል፡፡ በተሻሻለው ሕግ መሠረት ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ያዘዋወረ፣ለጉልበት ብዝበዛ፣ለባርነት፣በዕዳ ለመያዝ፣እንዲሁም ለግዳጅ የወሲብ ንግድ የዳረገ ከዕድሜ ልክ እስራት እስከ 500,000 ብር ቅጣት እንደሚጠብቀው ይደነግጋል፡፡

ወደ አረብ ሀገራት ለሥራ ፍለጋ የሚደረግ ጉዞ ላይ የተጣለው ዕገዳ እንደፀና ቢሆንም፤ መንግሥት ዕገዳውን ለማንሳት እንደ ዋና ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠውን የተሻሻለ የውጭ ሀገራት የስራ ሥምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2016 በየካቲት ወር አፅድቋል፡፡

ሕጉ የግዳጅ ሥራዎችን ይከለክላል። ነገር ግን ፍርድ ቤቶች የግዳጅ ሥራን እንደ ቅጣት እርምጃ እንዲወስዱ ይፈቅዳል። ባርነት፤ በድብቅ የሚከናወነውንም ጨምሮ፤ ከ5 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ እስራትና መቀጮ ያስቀጣል፡፡ የግዳጅ ሥራ ክልከላን መንግሥት በበቂ ሁኔታ ተፈፃሚ አላደረገም። ምንም እንኳን ፖሊስ በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውርና በጉልበት ብዝበዛ ላይ ያተረኮሩ ሥልጠናዎችን ያገኘ ቢሆንም፤ የግዳጅ ሥራ በተግባር ተፈጽሟል። አዋቂዎችና ሕፃናት በጎዳና ላይ ንግድ፣ በልመና፣ በሽመና ሥራ ወይም በግብርና ሥራ በግድ እንዲሠማሩ ተደርገዋል። ከዚህ ሌላ ሕፃናት በግዳጅ የቤት ውስጥ ሠራተኛ ሆነው እንዲሠሩ ተደርገዋል። በተለይ በገጠር አካባቢዎች ሰዎች ለተበደሩት ገንዘብ ምትክ በግዳጅ የሽመናና የሸክላ ሥራዎችን በመሥራት፣ በእረኝነት፣ እንዲሁም ሌሎች የግብርና ሥራዎችን በማከናወን ለአበዳሪዎች የሚሰሩበት ሁኔታ ተስተውሏል። በጎረቤት የአፍሪካ ሀገራት ልጃገረዶች በቤት ውስጥ ባርነት እና ሴተኛ አዳሪነት ብዝበዛ ተጋልጠዋል፡፡ በውጭ ሀገር ሥራ የተሰማሩ ወይም በመካከለኛው ምሥራቅ ከከፉ አሰሪዎቻቸው ያመለጡ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የወሲብ ህገወጥ

አዘዋዋሪዎች ተጋላጭ ናቸው፡፡ አንዳንድ ወደ አረብ ሀገራት እና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የተሰደዱ ወንዶች ለግዳጅ የጉልበት ሥራ ተዳርገዋል፡፡

መንግሥት አንዳንድ ጊዜ እስረኞችን ከማረሚያ ቦታዎች ውጭ ለግል ሥራ አሰማርቷል፡፡ ዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት ይህ ተግባር አስገዳጅ የጉልበት ብዝበዛ አካል ሊሆን ይችላል ሲል ገልጿል፡፡

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ያወጣውን ሪፖርት በwww.state.gov/j/tip/rls/tiprpt/ላይ ይመልከቱ፡፡

## ሐ. የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ማስቀረት እና የሥራ ቅጥር ዝቅተኛ ዕድሜ

ለቀን ሥራ ወይም ደመወዝ ለሚከፈልበት ሥራ የቅጥር ዝቅተኛ (የመነሻ) ዕድሜ 14 ዓመት እንደሆነ በሕግ ተደንግጓል። ይህ ዝቅተኛ የመነሻ ዕድሜ ግን በኮንትራት ቅጥር እንጂ በራሳቸው የተቀጠሩ ሕፃናት ወይም ያለክፍያ በሚሠሩ ሕጻናት ላይ ተፈፃሚነት የለውም። ዕድሜያቸው ከ14 እስከ 18 ዓመት የሆኑ ታዳጊዎች አደገኛ በሆኑ እና ሌሊት መሥራት በሚጠይቁ ሥራዎች ላይ መሰማራት እንደሌለባቸው ህጉ ይደነግጋል፡፡ ሕጉ የህፃናትን የጤና ሁኔታ በአደጋ ላይ የሚጥልን ሥራ አደገኛ ሥራ ይለዋል፡፡ አደገኛ ሥራዎች ተብለው ከተከለከሉት የሥራ ዘርፎች መካከል የመንገደኞች ትራንስፖርት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ የፋብሪካ ሥራ፣ የከርሰምደር ሥራዎች፣ የመንገድ ጽዳት እና ሌሎች በርካታ ዘርፎች ይገኙባቸዋል። ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች አደገና በሚባሉ ስራች ላይ እንዳይሰማሩ በማሰብ በሙያ ት/ቤቶች እንዳማሩበግልጽ ይገድባል፡፡  በ14 እና በ18 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ልጆች በቀን ከሰባት ሰዓታት በላይ እንዳይሠሩ እንዲሁም ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት፣ በህዝብ በዓላት፣ በእረፍት ቀናት ወይም የትርፍ ሰዓት ሥራዎችን መሥራት እንደሌለባቸው ህጉ ይደነግጋል።

የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከባድ ችግር ሆኖ ቀጥሏል። በዘርፉ ሠልጥነው በጉዳዩ ላይ ምርመራ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ቁጥር አናሳ መሆንና የሚፈለጉ ግብዓቶች አለመኖር ጥሰቶች እንዲበራከቱ አድርጓል፡፡ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ እርምጃዎች በሚገባ ባለመተግበራቸው፤ በርካታ ህፃናት በተለይም በግንባታው ዘርፍ ያላንዳች ክልከላ ተሳትፈዋል፡፡

የትምህርት ተሳትፎ በተለይም በገጠር እጅግ አነስተኛ ነበር፡፡ የትምህርትን አስፈላጊነት ለማጉላት ህፃናት በብዛት በግብርና ሥራ ላይ በሚያሰማሩ ማኅበረሰቦች ላይ ያተኮሩ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተሠሩ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራዎች ነበሩ፡፡ መንግሥት የእርሻ ሥራን ዘመናዊ በማድረግ ዙሪያ በርካታ ሥራዎችን በመሥራትና ትምህርት ቤቶችን በመገንባት በግብርናው ዘርፍ የሚስተዋለውን የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ችግር የመግታት ጥረት አድርጓል፡፡

በገጠርም ይሁን በከተማ ሕፃናት ሥራ የሚጀምሩት ገና በልጅነታቸው ነው፡፡ ሕፃናት በተለይ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የእርሻ ሥራ፣ በባሕላዊ ሽመና፣ በዓሳ ማስገር፣ በቤት ውስጥ ሰራተኝነት ተሰማርተዋል፡፡ በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ህጻናት ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፡፡ በገጠር ያሉ ሕፃናት በተለይ ወንዶቹ በእረኝነት፣ በጥቃቅን ንግድ፣ በእርሻ ሥራ፣ በአረም እና በሰብል መሰብሰብ ሥራዎች ተሰማርተው የነበረ ሲሆን፣ ሴት ሕጻናት ደግሞ በማገዶ ለቀማና በውሃ መቅዳት ሥራዎች ተሳትፈዋል። ሕፃናት በወርቅ ማምረትም ተሰማርተው ነበር፡፡ በአነስተኛ የወርቅ ማዕድን ቁፋሮ የሚሰሩ ሕጻናት  ጉድጓድ ቆፍረዋል፤ ብዛት ያለው ውሃ ተሸክመዋል፡፡ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ጨምሮ በከተማ ያሉ ልጆች በቤት ውስጥ ሥራዎች ለረጅም ሰዓታት እንዲሰሩ ስለሚደረግ ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል አልቻሉም። ሕፃናት በተጨማሪም በማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ በጫማ መጥረግ፣ በልብስ ስፌት፣ በመኪና ጥበቃ፣

በሕዝብ ማመላለሻዎች፤ በጥቃቅን ንግዶች፤ በሸክም ሥራ እንዲሁም በታክሲ ረዳትነት ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር። አንዳንድ ሕፃናት በጥቂት ክፍያ ወይም ያለክፍያ ወይንም አስተማማኝ የስራ ላይ ደህንነት ጥበቃ በሌለበት አደገኛ አካባቢ ለረዥም ሰዓታት እንዲሰሩ ተደርገዋል፡፡ የጉልበት ሥራ የሚሠሩ ሕፃናት ብዙውን ጊዜ በአሰሪዎቻቸው የአካል፣ የወሲብና የሞራል ጥቃት ደርሶባቸዋል።

ተጨማሪ መረጃ አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ጥናት ግኝቶች የሚለውን የሥራ ሚኒስቴር (Department of Labor) ሪፖርት ከwww.dol.gov/ilab/reports/child-labor/findings/ማግኘት ይችላሉ፡፡

## መ. ከሥራ ሁኔታ ወይም ከሙያ ጋር ተያያዥ የሆነ መድሎ

ዘርን፣ብሔርን፣ዜግነትን፣ጾታን፣የጋብቻ ሁኔታን፣ሃይማኖትን፣የፖለቲካ አቋምን፣የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለምን፣ነፍሰጡርነትን፣ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን፣አካል ጉዳተኝነትን አልያም "ሌሎች ሁኔታዎችን" መሠረት ያደረገ መድሎ እንዳይኖር ሕጉ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ሕጉ በነፍሰጡር ሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ ተጨማሪ ጫና መኖሩን ይገልጻል (ክፍል 6 ላይ ይመልከቱ)፡፡ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ጾታዊ ማንነትና፣ከኤች አይ ቪ ጋር መኖር ልዩ ከለላ አልተደረገላቸውም፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከቱ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ መድልዎ የሚፈጽም አካል 1,200 ብር እንደሚቀጣ ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ሕጉን ለመተግበር መንግሥት የወሰደው እርምጃ ውሱን ነበር፡፡

ሴቶች የሥራና የሙያ መድልዎ ተደርጎባቸዋል፡፡ ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ሴቶች አነስተኛ የሥራ ዕድሎች ነበሯቸው፡፡ ያሉትም የሥራ መደቦች ሴቶች ለተመሳሳይ የሥራ መስክ የሚያገኙት ክፍያ ለወንድ ሠራተኞች ከሚከፈለው ያነሰ ነው፡፡

ስደተኛ የሆኑ ሠራተኞችም መድልዎ ተፈጽሞባቸዋል (ክፍል 7 "ሠን ይመልከቱ) ፡፡

## ሠ. ተቀባይነት ያላቸው የሥራ ሁኔታዎች

በሀገር አቀፍ ደረጃ ዝቅተኛ የደመወዝ ክፍያ መጠን ድንጋጌ የለም። አንዳንድ የመንግሥትና ሕዝባዊ ተቋማት የራሳቸውን ዝቅተኛ የደመወዝ መጠን አውጥተዋል፡፡ ትልቁን ቁጥር የያዙት የመንግሥት ሠራተኞች ሲሆኑ፣ ዝቅተኛው የወር ደመወዛቸው 420 ብር (19 የአሜሪካን ዶላር) ነበር። የመጨረሻው ዝቅተኛ የገቢ መጠን 315 ብር (14 የአሜሪካን ዶላር) መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ከአጠቃላይ ህዝቡ አነስተኛ ቁጥር ያለው የወር ደመወዝተኛ ሲሆን፤ የሚኖረውም በከተሞች አካባቢ ነው፡፡ መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የሚከፈለው ወርሃዊ ደመወዝ ለሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ከሚያስፈልገው በታች ነበር፡፡

አንድ ሠራተኛ በሳምንት ውስጥ ቢበዛ ለ48 ሰዓታት መሥራት እንዳለበት፣ እንዲሁም በሳምንት የ24 ሰዓታት እረፍት፣ የትርፍ ጊዜ ክፍያና አስገዳጅ ከመጠን ያለፈ የትርፍ ሰዓት ሥራ ማሠራትን የሠራተኛ ህጉ ይከለክላል። በሀገሪቱ በዓመት ውስጥ ደመወዝ የሚከፈልባቸው 13 የህዝብ በዓላት አሉ። በልማት ድርጅቶችና በመንግሥት የፋይናንስ ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የማግኘት መብት፣ እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞች ትርፍ ሰዓት የሠሩበትን የማካካሻ ሰዓት የማግኘት መብት እንዳላቸው ተቀምጧል። መንግሥት፣ ኢንዱስትሪዎችና የሠራተኛ ማኅበራት የሥራ አካባቢ ጤናና

ደህንነት መስፈርቶች ላይ ተደራድረዋል። መሠረታዊ የሠራተኛ ማኅበር እንዲያቋቁሙ ያልተፈቀደላቸው የቤት ሠራተኞች፣ ወቅታዊና ጊዜያዊ የእርሻ ዘርፍ ሠራተኞች የሥራ አካባቢ ጤናና ደህንነት ጥበቃ አላገኙም፡፡

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የቁጥጥር መምሪያ የስራ ላይ ጤናና ደህንነት መስፈርቶች ተግባራዊ መሆናቸውን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ በ2007/2008 ዓ.ም. በሀገሪቱ 423 የሥራ ተቆጣጣሪዎች የነበሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዓመት 37,500 ቁጥጥሮችን እነዳደረጉ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጠቁሟል። ነገር ግን እነዚህ ተቆጣጣሪዎች መመሪያዎችን በሚገባ አላስፈጸሙም፡፡ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለበት ውሱን የአስተዳደር አቅም፤የመብት ጥሰት አቤቱታዎችን የመቀበል፤ የመመርመርና የመከታተል ድክመት እና ዝርዝር የሆነ የሥራ አካባቢ ጤናና ደህንነት ክትትል መመሪያዎች አለመኖር፣ መስፈርቶቹ በተግባር እንዳይውሉ መሰናክል ሆኗል፡፡ የተለያዩ ጥሰቶችን በፈጸሙ አካላት ላይ የሚጣለው ከፍተኛው መቀጮ ከ300 እስከ 1000 ብር ነው፡፡ ይህም ጥሰጦች እንዳይፈጸሙ ለመከላከል አላስቻለም፡፡

ለጊዜያዊ የግብርና ሠራተኞች የሚከፈለው ካሳ፣ ጥቅማጥቅሞችና የሥራ ሁኔታ በሠራተኛ ማኅበር ከታቀፉ ቋሚ የግብርና ሠራተኞች እጅግ ያነሰ ነበር፡፡ መንግሥት ሕጉን ተፈጻሚ ለማድረግ ብዙ አልተንቀሳቀሰም፡፡ በመደበኛው ዘርፍ የሚሠሩት አብዛኛዎቹ ሠራተኞች በሳምንት 39 ሰዓታት ይሠራሉ። ነገር ግን፣ በርካታ የውጭ ዜጎች፣ ስደተኞች እና መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የሚሰሩ ሠራተኞች በሳምንት ከ48 ሰዓታት በላይ ሠርተዋል።

ምንም እንኳን ሠራተኞች ሥራቸውን በማይጎዳ መልኩ አደገኛ ከሆኑ የሥራ ሁኔታዎች ራሳቸውን የማራቅ መብት ቢኖራቸውም፤ ሠራተኞች ይህንን መብት ስለመጠቀማቸው የቀረበ ሪፖርት አልነበረም፡፡ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሠረት በሆነው የግብርና ዘርፍ ውስጥ ለአደጋ አጋላጭ የሥራ ላይ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። በኢንዱስትሪ እና በኮንስትራክሽን ዘርፎች በተመሳሳይ አደገኛ የሥራ ሁኔታዎች እና የጉልበት ብዝበዛዎች እንደተስተዋሉ የቀረቡ ሪፖርቶች ቢኖሩም፤ሞት ወይም የአካል ጉዳት መኖሩን የሚጠቁም መረጃ አልተገኘም፡፡